# ዲሞክራሲያዊ የለውጥ እርምጃዎች፣ እንድምታዎች እና አማራጮቻቸው በኢትዮጵያ

ቅፅ ሦስት

## ኢትዮጵያ ከአካባቢ አገራት ጋር ያላት ግንኙነት እና የዓባይ ውኃ ጉዳይ

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies

# ዲሞክራሲያዊ የለውጥ እርምጃዎች፣

# እንድምታዎች እና አማራጮቻቸው በኢትዮጵያ

ቅፅ ሦስት

## ኢትዮጵያ ከአካባቢ አገራት ጋር ያላት ግንኙነት እና የዓባይ ውኃ ጉዳይ

**አርታኢ**

**ዘሪሁን መሐመድ**

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ

FORUM FOR SOCIAL STUDIES (FSS)

© 2012 ዓ.ም ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
አዲስ አበባ

ማንኛውም የአሳታሚው መብቶች በሕግ የተጠበቁ ናቸው

ISBN: 978-99944-50-73-1

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
ፖ.ሳ.ቁ. 25864 ኮድ 1000
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ኢሜይል፡ fss@ethionet.et

ድረ-ገጽ፡ www.fssethiopia.org.et

ይህ መጽሐፍ የታተመው በናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዲሞክራሲ (National Endowment for Democracy) የገንዘብ ድጋፍ ነው:: በዚህ ህትመት ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የሥራ አመራር ቦርዱን፣ የድርጅቱን አጋሮችና የገንዘብ ድጋፍ የሠጠውን ናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዲሞክራሲ አቋምና አመለካከት ላያንጸባርቅ ይችላል::

# ማውጫ

*መቅድም* .......... I

*መግቢያ* .......... III

*የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲና ከጎረቤትና ከአረብ ባሕረ-ሰላጤ አገራት ጋር ያላት ግንኙነት* .......... 1

*አስናቀ ከፋለ*

*የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ አቅጣጫና በቀይ ባህር እና በባህረ ሠላጤው አካባቢ ያለን ወቅታዊ ግንኙነት* .......... 33

*ኀሩይ አማኑኤል*

*የዓባይ ወንዝና የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ* .......... 45

*ያዕቆብ አርሳኖ*

*የናይል ተፋሰስ ተለዋዋጭ የውኃ ፖለቲካና ተቋማዊ ገፅታዎች* .......... 65

*ተስፋዬ ታፈሰ*

## መቅድም

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (Forum for Social Studies-FSS) በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ልማታዊ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ጠለቅ ያለ ጥናትና ምርምር የሚያካሂድ፤ በአገራዊ ጉዳዮች ላይ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውይይት እንዲያደርጉ መድረኮችን የሚያዘጋጅ መንግስታዊ ያልሆነና ለትርፍ ያልተቋቋመ ሀገር በቀል የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅት ነው። የድርጅቱ እንቅስቃሴ በመንግስት ፖሊሲ አውጪዎች፣ አስፈጻሚ የመንግስት አካላት፣ ምሁራንና ተመራማሪዎች፣ የሲቪል ማኅበራትና በአጠቃላይ በህብረተሰቡ መካከል በአገራዊ ጉዳዮች ላይ በትክክለኛ መረጃ ላይ የተመሠረተ፣ ግልጽና ቀና ውይይት ማድረግ ጤናማ የውይይት ባህልን ከማዳበርና ግልጽና አሳታፊ የፖሊሲ ቀረፃና ትግበራ ስርዓትን ለማስፈን ከማስቻሉ ባሻገር ለአገር ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት፣ ለዴሞክራሲ መዳበርና ለዜጎች ዕኩልነት መስፈን ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል በሚል ዕምነትና መርህ ላይ የተመሠረተ ነው።

ድርጅቱ ከሚያካሂዳቸው የጥናትና ምርምር ስራዎች በተጨማሪ ተከታታይ ሕዝባዊ የውይይት መድረኮችን የሚያዘጋጅ ሲሆን፤ በመድረኮቹም የመንግስት ፖሊሲ አውጪዎችና አስፈጻሚዎች፣ የሲቪል ማኅበረሠብ አካላትና ተመራማሪዎችን ጨምሮ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በወቅታዊ አገራዊ የልማት ጉዳዮች ላይ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ግልጽ፣ ገንቢና አሳታፊ ውይይቶች ያደርጋሉ።

ድርጅቱ ባለፉት ሁለት አስርተ-ዓመታት ብዛት ያላቸው ተከታታይ ሕዝባዊ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ሕብረተሰቡን ሲያሳትፍ የቆየ ሲሆን፤ የነዚህን የውይይት ውጤቶች በተለያዩ ህትመቶችና የብዙሀን መገናኛ ዘዴዎች አማካኝነት ለህዝብ ተደራሽ ሲያደረግ ቆይቷል። ይሁን እንጂ በ2001 የወጣው የኢትዮጵያ በጎ አድራጎትና ማኅበራት አዋጅ በጣለው ገደብ ሳቢያ ድርጅቱ በአገራችን የፖለቲካና ፖለቲካ ነክ ጉዳዮች ላይ የሚያደርገው የጥናት፣ ምርምርና ሕዝባዊ የውይይት መድረክ ስራዎች ተቀዛቅዘቀው መቆየታቸው ይታወሳል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት በአገሪቱ በመካሄድ ላይ የሚገኘው የፖለቲካ ሪፎርምና በመንግስት የተወሰዱ እርምጃዎች ይህንን ተቀዛቅዞ የነበረ ስራ ዳግም በመመለስ ረገድ በሁለት በኩል አስተዋፅዖ እንዳደረጉ ይታመናል። የመጀመሪያው እርምጃ በሲቪል ማኅበራት እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ገደብ አስቀምጦ የነበረው አዋጅ መሻሻል ሲሆን፣ አሁን ተሻሽሎ በወጣው የሲቪል ማኅበራት አዋጅ (ቁጥር 113/2011) ቀደም ሲል የነበሩት ስራ መስኮች ገደብ

ተነስቶ ማንኛውም የሲቪል ድርጅት በየትኛውም ሕጋዊ ሥራ ላይ የመሠማራት ሙሉ መብት ሰጥቷል። በዚህ ምክንያት በፖለቲካና ፖለቲካ ነክ ጉዳዮች የምናደርገውን የጥናት፣ ምርምርና ሕዝባዊ የውይይት መድረክ እንቅስቃሴዎች ለመቀጠል ችለናል። በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ከ2010 ጀምሮ ዘርፈ-ብዙ በሆነ የፖለቲካ ሪፎርም ሂደት ውስጥ ያለች ከመሆኗ አንፃር ሪፎርሙ ቀደም ሲል ያልተነሱ ውይይትና ክርክር የሚያስፈልጋቸው ወቅታዊ ሁኔታዎችን ይዞ መምጣቱ የፖለቲካና ፖለቲካ ነክ ጉዳዮች ላይ የሚደረገውን ሕዝባዊ የውይይት መድረክ ዳግም ለማንሰራራት ጥሩ አጋጣሚ ፈጥሯል።

በመሆኑም ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ወቅታዊውን የአገራችን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሁኔታን በሚመለከት ዲሞክራሲያዊ የለውጥ ጉዞ በኢትዮጵያ፦ የለውጥ ዕርምጃዎች፣ አንድምታዎቻቸውና አማራጮች በተሠኘ ርዕስ ሕዝባዊ የውይይት መድረኮችን ቀርጾ አካሂዷል። የውይይት መድረኮቹ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተገኝተው በተመረጡ ወቅታዊ ርዕሶች ላይ የሚነጋገሩበት፣ ሀሳብ የሚለዋወጡበትና አማራጮችን የሚፈልጉበት መድረክ ለመፍጠር አስችሏል። በእያንዳንዱ የውይይት መድረክ ላይም ለውይይቶቹ በመነሻነት የሚያገለግሉ ጥናታዊ ጽሑፎች በየመስኩ በተሰማሩ ባለሙያዎች የቀረቡ ሲሆን፤ በነዚሁ ጥናታዊ ወረቀቶቹ ላይ ተመርኩዘው ተሳታፊዎች ሰፊ ውይይቶችን አካሂደዋል። የተካሄዱት ውይይቶችም በተለያዩ የሬድዮ ጣቢያዎችና ማኅበራዊ ሚዲያ አማካይነት ለሕዝብ እንዲደርሱ ተደርጓል።

ከዚህ በተጨማሪ ጥናታዊ ጽሑፎቹን በሕትመት ለህዝብ ለማድረስ ባለን ዕቅድ መሠረት ከተካሄዱት የውይይት መድረኮች መካከል የጀመሪያዎቹ ሁለቱ ሕገ-መንግስት፣ ብሔር-ተኮር ፌደራሊዝም፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ሕዝባዊ ምርጫ ላይ የሚያጠነጥኑት በቅፅ አንድ፣ በክፍል ሦስት እና አራት የቀረቡት በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ያተኮሩት ውይይቶች ደግሞ በቅፅ ሁለት ታትመው መቅረባቸው ይታወሳል። የመጨረሻዎቹ በዓባይ ውኃ እና በኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ላይ ያተኮሩት ሁለቱ የውይይት መድረኮች ደግሞ በዚህ በሶስተኛው ቅፅ ታትመው የቀረቡ ሲሆን፣ በእነዚህ መድረኮች ላይ ጥናታዊ ጽሑፎችን በማቅረብ፣ በአወያይነትና በተሳታፊነት የተሳተፉትን ባለድርሻ አካላትን በሙሉ ለማመስገን እወዳለሁ። በተለይ ይህን ሕዝባዊ የውይይት መድረክ እና ህትመት ለማዘጋጀት ያስቻለንን ናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዲሞክራሲ (National Endowment for Democracy-NED) የተሰኘውን መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ከልብ አመሠግናለሁ።

የራስወርቅ አድማሴ (ዶ/ር)
ስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር
ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ

# መግቢያ

በኢትዮጵያ በየጊዜው የተለያዩ ስር ነቀል ሊባሉ የሚችሉ የፖለቲካ ለውጦች ተካሂደዋል:: የዘውዳዊውን አገዛዝ ገርስሶ የጣለው የ1966ቱ ሕዝባዊ አብዮት እና ይህን ተከትሎ ስልጣን ላይ የወጣውንና አስራ ሰባት ዓመታት በስልጣን ላይ የቆየውን የደርግ አገዛዝ ያስወገደው የ1983ቱ የፖለቲካዊ ለውጥ በዋናነት ይጠቀሳሉ:: እነዚህ ለውጦች በአገሪቱ ሠፍነው ለነበሩት ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ቅሬታዎች ምላሽ በመስጠት ዕኩልነትን፣ ዕድገትንና ማኅበራዊ ፍትህን ለማስፈን ያለሙ ነበሩ:: ይሁን እንጂ እነዚህ ትልሞች ሁሌም የተሳኩ ነበሩ ማለት አያስደፍርም:: የሶሻሊት ርዕዮተ-ዓለም እከተላለሁ ይል የነበረው ደርግ ወደስልጣን ያመጣውን ሕዝባዊ ብሶት በአብዛኛው መመለስ ተስኖት እንዲያውም አገሪቱን ወደተባባሰ ፖለቲካዊ አዘቅት ከትቶ ከስልጣን ተወግዷል::

ደርግን ያስወገደውና በቦታው ራሱን የተካውና በኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) የሚመራው መንግስትም በተመሳሳይ ስር-ነቀል ለውጦች በማካሄድ ሕዝባዊ ምላሽ ለመስጠት ተስፋ ተጥሎበት ነበር:: እውነትም በተለይ በመጀመሪያ ዓመታት በአገሪቱ አንዳንድ በጎ ለውጦች ታይተው ነበር:: በኢኮኖሚ ረገድ አገሪቱ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ከማስመዝገቧ ባሻገር ከ1998 እስከ 2008 ባሉት አስር ዓመታት የአገሪቱ ኢኮኖሚ የ10.3 ዕድገት ማሳየቱን የተለያዩ መረጃዎች ያመለክታሉ:: በተመሳሳይ ሁኔታ አመርቂ የመሠረተ-ልማት ውጤቶችም ተመዝግበዋል::

ይሁን እንጂ ይህ አመርቂ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ እንዲሁም ሠፊ የመሠረተ- ልማትና የማኅበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋት ኢትዮጵያን በዓለም እጅግ ደሀ ከሚባሉት አገራት ተርታ አላወጧትም:: የአገሪቱ ኢኮኖሚ በኋላ-ቀር የአመራረት ዘዴ፣ በአየር ንብረት መዛባት እና በተለያዩ መዋቅራዊ ችግሮች በተተበተበው የግብርናው ክፍለ-ኢኮኖሚ ላይ ከመንጠልጠል ያላመለጠ ሲሆን፤ ከግማሽ በላይ የሚሆነውን የአገር ውስጥ ምርት (Gross Domestic Product-GDP)፣ 83 ከመቶ የወጪ ምርትና 80 ከመቶ የስራ ዕድል በዚሁ ክፍለ-ኢኮኖሚ የተሸፈነ ነው:: በአሁኑ ጊዜ የእርሻ መሬት ዕጥረት፣ መሬት አልባነት እና አማራጭ የስራ ዕድል አለመኖር በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች በከፍተኛ ደረጃ ይስተዋላል::

የውጭ መዋዕለ ንዋይ በመሳብና የአገር ውስጥ ካፒታልን በማንቀሳቀስ የኢንዱስትሪውን ክፍለ-ኢኮኖሚ ለማሳደግ የተደረገው ጥረት በከፍተኛ ፍጥነት በማደግ ላይ ላለው ስራ ፈላጊ

በቂ ስራ ለመስጠት የሚችልበት ደረጃ ላይ ገና አልደረሰም። በዚህ ሳቢያ ስራ አጥነት በከተማም ሆነ በገጠር በከፍተኛ ደረጃ ይስተዋላል። ከዚህ በተጨማሪ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ አንዳንድ ለልማት ተብለው የተወሰዱ ዕርምጃዎች በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የቅሬታ ምንጭ በመሆን ተቃውሞ አስነስተዋል። ለምሳሌ በከተሞች መስፋፋት፣ በኢንቨስትመንትና በልማት ሰበብ የእርሻ መሬቶቻቸውን የተነጠቁ ገበሬዎች የኑሯቸው መሠረት በነበረው መሬት መወሰድና የተሰጣቸው ካሣ አነስተኛ መሆን በቅርብ ዓመታት ለተነሳው የህዝብ ተቃውሞ አንዱ ዋና ምክንያት እንደነበር መጥቀስ ይቻላል።

በፖለቲካው መስክ አገሪቱን ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ሲያስተዳድር የቆየው ኢህአዴግ በተለይም ገዳቢ ሕጎችን በማውጣት፣ ለተቃዋሚ/ተፎካካሪ ድርጅቶች ማነቆ በመፍጠርና የፖለቲካ ፉክክር መድረኩን በማጥበብ ሲወነጀል መስማት የተለመደ ነበር። እነዚህ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ከፍተኛ ሕዝባዊ ተቃውሞ በማስነሳት በአገሪቱ ከፍተኛ ቀውስ እንዲፈጠር ምክንያት ሆነዋል። የቀውሱ አሳሳቢነት በአስራ ስምንት ወራት ውስጥ ሁለት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲታወጅም ምክንያት ሆኗል። ችግሩ ስር ነቀል ዕርምጃ የሚፈልግና በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ብቻ የሚፈታ ባለመሆኑ ገዢው ፓርቲ የተለያዩ መሠረታዊ የፖሊሲ ዕርምጃዎችን ለመውሰድ ተገድዷል። በሒደቱም የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ በሚያዝያ 2010 ስልጣናቸውን ለቅቀው ዶ/ር ዐቢይ አህመድ በቦታቸው ተተክተዋል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይም ወደስልጣን ከመጡ ጀምሮ የተለያዩ እርምጃዎችን የወሰዱ ሲሆን ቀደም ሲል የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶች ያሏቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ አገር ውስጥ ገብተው እንዲንቀሳቀሱ እርምጃ መወሰዱ፣ ከኤርትራ ጋር የሠላም ስምምነት መደረጉ፣ እንደ ምርጫ ቦርድና ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመሳሰሉት ተቋሞች ላይ ተቋማዊ ማሻሻያዎች መጀመሩ እና የተለያዩ መብት ገዳቢ የነበሩ ሕጎች ላይ ማሻሻያ መደረጋቸው የለውጡ ዓቢይ ዕርምጃዎች ተደርገው ይጠቀሳሉ።

በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ምናልባትም ከዚህ ቀደም ባልተለመደ ሁኔታና መጠን በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ የለውጥ ሒደት ውስጥ ትገኛለች። አገሪቱ ባለፉት ሁለት አስርተ-ዓመታት ያስመዘገበችው ኢኮኖሚያዊ ዕመርታ እንደተጠበቀ ሆኖ በተቃራኒው የመልካም አስተዳደር ዕጦት፣ እየተስፋፋ የመጣው የከተማና የገጠር ስራ አጥነት፣ ፍትኃዊ የሀብት ክፍፍል አለመኖርና የፖለቲካ ምኅዳር መጥበብ የለውጥ ሒደቱ እንዲመጣ ካስገደዱት ምክንያቶች መካከል በዋናነት ይጠቀሳሉ። ይሁን እንጂ ለውጡ ወዴት አቅጣጫና በምን ፍጥነት መጓዝ ይኖርበታል? ምን ምን ጉዳዮችን ማካተት ይገባዋል? እንዲሁም የአገሪቱ የወደፊት ሁኔታስ ምን መምሰል ይኖርበታል? በሚሉ ኃሳቦች ላይ ገና ሙሉ በሙሉ አገራዊ መስማማቶች ላይ ተደርሷል ተብሎ አይገመትም። በመሆኑም የተጀመረው አገራዊ ለውጥ የበለጠ ፍሬያማ እንዲሆን የሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃሳቦች

የሚንጸባረቁባቸው የጋራ መድረኮች የማዘጋጀትና ውይይት የማካሄድ አስፈላጊነት አያጠያይቅም::

በመሆኑም ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በወቅታዊ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ተገናኝተው የሚወያዩባቸው፣ የሚመክሩባቸውና አማራጮች ላይ የሚከራከሩባቸው ሕዝባዊ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀትና በማካሄድ ለአገራዊ የፖለቲካ ሪፎርሙ መሳካት የበኩሉን ለመወጣት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል:: የውይይት መድረኮቹ ከግንቦት ወር 2011 ጀምሮ እስከ ሕዳር ወር 2012 ዓ.ም ድረስ ባሉት ስድስት ወራት የተካሄዱ ሲሆን ውይይቶቹም በሦስት አቢይ ክፍሎች የተከፈሉ ነበሩ:: እነዚህም 1) ፖለቲካ፣ ሕገ-መንግስትና ሕገ-መንግስታዊ ተቋማት ግንባታ፣ 2) አገራዊ ኢኮኖሚ ፖሊሲ እና 3) የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ነበሩ:: በእያንዳንዱ ዓቢይ ርዕስ ስር ሁለት ሁለት የውይይት መድረኮች ተካሂደዋል:: በእያንዳንዱ መድረክም በመስኩ የጠለቀ ዕውቀትና የስራ ልምድ ያላቸው ሁለት ሁለት ምሁራን የውይይት መነሻ ጽሑፎች እንዲያቀርቡ ተደርጓል:: በመድረኮቹ የቀረቡት ጽሑፎችም ከመወያያ አዳራሽ ባሻገር በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ለሕብረተሰቡ እንዲደርሱ ጥረት ተደርጓል:: በተለያዩ የኤሌክትሮኒክ ሚዲያ እና ማኅበራዊ ሚዲያዎች በተከታታይ ከሚቀርበው በተጨማሪ ጥናታዊ ጽሑፎቹ አርትዖት ተደርጎባቸው በሕትመት በየዐቢይ ርዕሶቹ ዘርፍ በሦስት ተከፍለው እንዲቀርቡ ታቅዶ፤ በአንደኛና በሁለተኛ ዐቢይ ርዕሶች ስር የቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፎች በቅፅ አንድ እና በቅፅ ሁለት ታትመው ለሕዝብ መቅረባቸው ይታወሳል::

በዚህ መሠረት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በሚል ዓቢይ ርዕስ የኢትዮጵያ እና የአካባቢ አገራት ግንኙነት እንዲሁም የዓባይ ውኃ ፖሊሲ በሚል በሁለት የውይይት መድረኮ ላይ የቀረቡት ጥናታዊ ፅሁፎች በውይይት ዳብረውና አርትዖት ተደርጎባቸው በዚህ ቅፅ ቀርበዋል:: ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ቀንድና ከአረብ ባሕረ-ሠላጤ አገራት ጋር ያዳበረቻቸውን ዲፕሎማሲዊ ግንኙነቶች፣ ለውጦችና አሁናዊ ሁኔታዎችን በሚመለከት ጥቅምት 13 ቀን 2012 በተካሄደው መድረክ ላይ ዶ/ር አስናቀ ከፋለ እና አምባሳደር ኀሩይ አማኑኤል ጥናታዊ ፅሁፎችን አቅርበዋል:: ዶ/ር አስናቀ ከፋለ ‹‹የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲና ከጎረቤትና ከአረብ ባሕረ-ሰላጤ አገራት ጋር ያላት ግንኙነት›› በሚል ርዕስ ባቀረቡት ፅሁፍ የአንድን አገር የውጭ ግንኙነት የሚወስኑ ነባራዊ ሁኔታዎችን ከዘረዘሩ በኂላ ኢትዮጵያም ከጎረቤት እና ከአረብ ባሕረ-ሠላጤ አገራት ጋር ያላት ግንኙነቶች ላይ ተፅዕኖ ያሳደሩ አገራዊ፣ አካባቢያዊ እና አለማቀፋዊ ሁኔታዎችን በዝርዝር አሳይተዋል:: ፅሑፉ ኢትዮጵያ ድንበር ከምትጋራቸው የአፍሪካ ቀንድ አገራትና ድንበር ከማትጋራቸው ነገር ግን በበጎም ሆነ በክፉ ከተሳሰረቻቸው የአረብ ባሕረ-ሠላጤ አገራት ጋር ባለፉት ዓመታት የፈጠረቻቸውን የግንኙነት ዓይነቶች፣ ግንኙነቶቹ ያሉባቸውን ተግዳሮቶች እንዲሁም በቅርቡ በየአገራቱና

በኢትዮጵያ በተካሄዱ ውስጣዊ ለውጦች ሳቢያ የተፈጠሩ ለውጦችን ይዳስሳል፡፡ በግልጽ ያልተካለሉ ድንበሮች፣ የህዝቦች አሠፋፈር፣ ድንበር አቋራጭ መሠረተ-ልማቶች ሁኔታ እና ድንበር ተሻጋሪ የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም ኢትዮጵያ ከአገራቱ ጋር የሚኖራትን ግንኙነት ላይ ተፅዕኖ የሚፈጥሩ ዋና ዋና ምክንያቶች መሆናቸውን ያመለክታሉ፡፡ በመደምደሚያቸውም ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን የኃይል አሰላለፍ በመመልከት ከአካባቢ አገራት ጋር ያላትን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መቃኘት እንዳለባት ያሳስባሉ፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ አምባሳደር ጎሩይ አማኑኤል ‹‹የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ አቅጣጫና በቀይ ባህር እና በባህረ ሠላጤው አካባቢ ያለን ወቅታዊ ግንኙነት›› በሚለው ፅሑፍ የኢትዮጵያን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ በመግቢያነት በመዳሰስ የቅርብ ዓመታት ፖሊሲን ላይ ትኩረታቸውን ያደርጋሉ፡፡ በዚህም በተለያዩ ጊዜያት ወደስልጣን የመጡት የኃይለ ስላሴ፣ የደርግና የኢህአዴግ መንግስታት የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ላይ ለውጥና ቀጣይነት (change and continuity) ይታይ እንደነበረ መረጃዎች በመጥቀስ ያመለክታሉ፡፡ ፅሑፉ ቀደም ሲል የነበረውን የውጭ ግንኙነት ሠነድ ለመተካት በአሁኑ ጊዜ ተረቅቆ ለመውጣት በሒደት ላይ ያለው የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ቀደም ሲል ከነበሩት ተመሳሳይ ሠነዶች የሚለይባቸውን እና መነሻ ያደረጋቸውን ነጥቦች በዝርዝር ያሳያል፡፡ በመቀጠል አገሪቱ በአሁኑ ጊዜ ከተለያዩ ጎረቤት እና የገልፍ አገራት ጋር ያላትን ግንኙነቶች፣ ግንኙነቶቹ አሁን ያላቸውን መልክ እንዲያዙ ያደረጓቸውን ምክንያቶች በመተንተን በማጠቃለያው የአገሪቱ የውስጥ ሁኔታ ከሌሎች አገራት ጋር የሚኖረውን ግንኙነትና የኃይል ሚዛን በከፍተኛ ደረጃ የሚወሰን በመሆኑ ያሉንን ጠንካራ ጎኖች ይበልጥ በማዳበር የኢኮኖሚ ዕድገትን የሚያጠናክር የዲፕሎማሲ ሁኔታ መፍጠር እንዳለብን ያሳስባል፡፡

‹‹የዓባይ ውኃ አጠቃቀምና የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ›› በሚል ንዑስ ርዕስ ሕዳር 11 ቀን 2012 በተካሄደው የውይይት መድረክ ላይ ለረጅም ጊዜ ካደረጉት ጥናትና ምርምር በመነሳት ‹‹የዓባይ ወንዝና የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ›› በሚል ርዕስ ጥናታዊ ፅሑፋቸውን ያቀረቡት ዶ/ር ያዕቆብ አርሳኖ የኢትዮጵያን ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ባሕሪ፣ የዓባይ ወንዝን ልዩ ሁኔታ፣ ታሪካዊነትና ጥንታዊነት በመዳሰስ፤ የዓባይ ወንዝ ለናይል ያለውን ሚና እንዲሁም የናይልን ጂኦ-ፖለቲካዊ እና የልማት ሚና ይተነትናሉ፡፡ በመቀጠልም ኢትዮጵያ ዓባይን በተመለከተ ከ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ጀምሮ ትከተለው የነበረውን ፖሊሲ እና ከታችኛው ተፋሰስ አገራት (በተለይም ከብሪታኒያ የቅኝ ግዛት መንግስትና ግብፅ) ጋር የነበሩትን የዲፕሎማሲ ንትርኮች፣ በየጊዜው የነበሩትን ሒደቶችና ኢትዮጵያ የወሰደቻቸውን አቋሞች ያስረዳሉ፡፡ በመጨረሻም ኢትዮጵያ ድንበር

ተሻጋሪ ወንዞቿን ለልማቷ በሚገባ ለማዋል ዘላቂ አገራዊ የውኃ ፖሊሲ ማውጣት ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ እንዳልሆነ አበክረው ያሳስባሉ፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ‹‹የናይል ተፋሰስ ተለዋዋጭ የውኃ ፖለቲካና ተቋማዊ ገፅታዎች›› በሚለው ጥናታዊ ፅሁፋቸው ፕሮፌሠር ተስፋዬ ታፈሠ በላይኛው ተፋሰስ ተቋማዊና የውኃ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ በማተኮር የናይል የትብብር ማዕቀፍን ይመረምራሉ፤ ያጋጠሙትን ተግዳሮቶችና የተገኙትን ውጤቶች ይገመግማሉ፡፡ ፅሁፉ የናይል የትብብር ምዕቀፍን አመሠራረት፣ እንዲመሠረት ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች እንዲሁም እንዲያሳካ በዕቅድ የተያዙለትን ግቦች በመዘርዘር በቀጣናው የሚታየው ተለዋዋጭ የውኃ ፖለቲካ በተለይም በኢትዮጵያ ታላቁ ሕዳሴ ግድብ መጀመር ሳቢያ ለውጥ ማሳየቱን፤ በዚህም የላይኛው እና የታችኛው ተፋሰስ አገራት የገቡበትን ሁኔታ ያብራራል፡፡ ፅሁፉ ከሁለቱ የታችኛው አገራት መካከል ሱዳን የግድቡ መሰራት የሚሰጣትን ሁለንተናዊ ጥቅም በመረዳት የመደገፍ አዝማሚያ ስታሳይ፤ ግብፅ ግን ጊዜ ያለፈባቸውን የቅኝ ግዛት ውሎች በማንሳት የግድቡን ግንባታ ለማደናቀፍ የምታደርገውን ጥረት ያመለክታል፡፡ በማጠቃለያውም የናይል ተፋሰስ ኮሚሽን አለመመስረት ተፋሰሱን በሕግ፣ በስርዓትና በዕኩልነት መርሕ ለማስተዳደር አለማስቻሉን በመጥቀስ፤ የተፋሰሱ አገራት የናይል ውኃ የጋራ ሀብት መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ አስገብተው ይህንን የጋራ ሀብት በፍትሐዊነት፣ በምክንያታዊነት እና በቀናነት መርሆዎች ላይ በተመሠረተ ውኃውን ለመጠቀም ቢስማሙ መፍትሔዎቹ ሩቅ እንደማይሆኑ ይገልጻሉ፡፡

ፅሁፎቹ የውይይት መንደርደሪያ እንዲሆኑ ታስበው የተዘጋጁ እንደመሆናቸው መጠን ወደፊት በየመስኮቹ ለሚደረጉ ጥናትና ምርምሮች መነሻና ግብዓት በመሆን ሊያገለግሉ ይችላሉ የሚል ዕምነት አለ፡፡

አርታዒው

# የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ

# በአፍሪካ ቀንድና መካከለኛው ምስራቅ

# የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲና ከጎረቤትና ከአረብ ባሕረ-ሰላጤ አገራት ጋር ያላት ግንኙነት

**አስናቀ ከፋለ**

## 1 መግቢያ

ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ካሉ ጥንታዊ ሀገሮች አንዷ ከመሆኗም በላይ ከአውሮፓውያኑ ቅኝ ግዛት ራሷን በመከላከል ነፃነቷን ጠብቃ ቆይታለች። የአገሪቷ መሪዎች የተከተሉት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲና ዲፕሎማሲ የኢትዮጵያን ነፃነት ለመጠበቅ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አበርክቷል።

የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አገራት ከውጭ መንግሥታትና ሌሎች ዓለም አቀፍ ተዋናዮች ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት አገራዊ ጥቅማቸውን ማዕከል በማድረግ አቅጣጫ የሚሰጥ ማዕቀፍ ነው። የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የአገራትን የውጭ ግንኙነት ስትራቴጂዎችን፣ ስልቶችን እና የማስፈፀሚያ መሣሪያዎችን ያካትታል (Nanjira, 2010)።

የአገራትን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የሚወስኑ ሁኔታዎችን በሦስት ዋና ዋና የትንታኔ ደረጃዎች ማየት ይቻላል። እነርሱም የአገር ውስጥ፣ የአካባቢ (ቀጣና) እና የዓለም አቀፍ ደረጃዎች ናቸው። በመጀመሪያም፣ የአገር ውስጥ የትንታኔ ደረጃ የአንድ አገር ታሪክ፣ መልክዓ-ምድር (ጂኦግራፊ)፣ የሕዝብ ብዛትና ስብጥር እንዲሁም የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሥርዓት በውጭ ፖሊሲ ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ ይገመግማል። በሁለተኛ ደረጃ መታየት የሚገባው አንድ አገር የምትገኝበት አካባቢ (ቀጣና) በውጭ ጉዳይ ፖሊሲዋ ላይ የሚያደርሰውን በጎና ጎጂ ተፅዕኖ ነው። በመጨረሻም ሁሉም በዓለም ላይ የሚገኙ አገራት የዓለም አቀፉ ሥርዓት አባላት እንደ መሆናቸው መጠን ሥርዓቱ በውጭ ግንኙነት ፖሊሲያቸው ላይ የሚደቅነውን በጎና ጎጂ ተፅዕኖ መዳሰስ ተገቢ ነው። አሁናዊው የዓለም አቀፍ ሥርዓት በሽግግር ላይ የሚገኝ ሲሆን ሥርዓቱ በተለይ ኢትዮጵያን ለመሳሰሉ ታዳጊ አገሮች የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መልካም ዕድሎችና ፈተናዎች አሉት። ለምሣሌ ያህል እንደ ቻይና ያሉ ምዕራባዊ ያልሆኑ አገሮች ከኃያላን አገሮች ቡድን መቀላቀል ለታዳጊ አገሮች መልካም ዕድሎችን አምጥቷል።

ኢትዮጵያ በረጅም የነፃነት ታሪኳ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ባህሎችን አዳብራለች። ከእነዚህ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ባህሎች መካከል ዋነኛው የውጭ ጠላት ሲመጣ የውስጥ ልዩነትን ወደ ጎን አድርጎ በአንድነት በመቆም የውጭ ጠላትን መቋቋም ሲሆን ሌላው ደግሞ አንዱን ኃያል አገር በመጠቀም ሌላውን ኃያል አገር መመከት ነበር። ለምሣሌ ያህል ይህን የውጭ ፖሊሲ ስልት በመጠቀም በ1934 የጣልያን የቅኝ ግዛት ኃይል በእንግሊዝና በኢትዮጵያ አርበኞች ከተሸነፈ በኋላ የእንግሊዝ መንግሥት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማዳከም ያደረገውን ሙከራ የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት የአሜሪካንን አጋርነት በመጠቀም አክሽፏል (Marcus, 1995)። ይህ የውጭ ጉዳይ ባህል ሌሎች ነፃነታቸውን ጠብቀው የኖሩ አገራትም ተጠቅመውበታል። ለምሣሌ ኢራን (ፋርስ) ከአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች ነፃነቷን ለመጠበቅ የተጠቀመችበት የውጭ ጉዳይ መሣሪያ ‹‹የአንዱን ኃያል አገር ተፅዕኖ በሌላው ማጣፋት›› የተባለ ስልት ነበር[1]።

የአንዱን ኃያል ተፅዕኖ በሌላው ኃያል ከመመከት በተጨማሪ ኢትዮጵያ ጥቅሟንና ነፃነቷን ለማስጠበቅ ዓለም አቀፍ ሕግጋትንና ተቋማትን ተጠቅማባቸዋለች። ምንም እንኳን እ.ኤ.አ ከ1920-1946 በሥራ ላይ በነበረው የመንግሥታቱ ማህበር (ሊግ ኦፍ ኔሽንስ) አባል መሆኗ አገሪቱን ከጣልያን ወረራ ባይታደጋትም፤ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ ንቁ ተሳታፊና የጋራ ደህንነት መርሆን በማራመድ ትታወቃለች።

ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ገንቢ የሆነ የውጭ ጉዳይ ባህል ብታዳብርም፤ የአገር ጥቅምን የሚጎዳ የፖለቲካ ባህልም እንደነበረ መጠቆሙ ተገቢ ነው። በአገሪቷ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ለሥልጣን የሚሻሙ ግለሰቦች፣ ቡድኖችና ኃይሎች በተደጋጋሚ ከውጭ ሀይሎችን ጋር ሲሰለፉ ወይም መሣሪያ ሲሆኑ ታይቷል። ይህ ሁኔታ እስከ ቅርብ ጊዜም የቀጠለ ነው። የዚህ የፖለቲካ ችግር ዋነኛው ምክንያት በአገር ውስጥ ያለው የፖለቲካ (የዲሞክራሲ ባህል) አለማደጉና የፖለቲካ ፉክክርን በሠላም ለማስተናገድ የሚያስችል ሥርዓት አለመዳበሩ ነበር። ይህ ተግባር ለኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ከፍ ያለ ተግዳሮት እንደነበረ ማስመር ይገባል። የዲሞክራሲ ሥርዓት መጠናከርና ተያይዞም የሚመጣው የመንግሥት ቅቡልነት ማደግ ይህን ችግር ለመቅረፍ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ያደርጋል። በኢትዮጵያ ከ2010 ጀምሮ በመካሄድ ላይ ያለው የፖለቲካ ለውጥ የአገሪቱን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲንና ግንኙነትን በተመለከተ መልካም ዕድሎችንና ሥጋቶችን ማምጣቱ አሌ የማይባል ነው። የዚህ ፅሁፍ ዓላማም አገሪቱ ከጎረቤት እና ከአረብ ባሕረ-ሠላጤ አገራት ጋር ያላት ግንኙነት ምን

[1] ይህ በእንግሊዝኛ “Negative equilibrium” የተባለው ነው። ስለዚህ የበለጠ ማብራሪያ ለማግኘት የሚከተለውን ፅሁፍ ይመልከቱ። R. K. Ramazani (1989) "Iran’s Foreign Policy: Contending Orientations". Middle East Journal. 43 (2): 202-217.

እንደሚመስል መዳሰስና የፖለቲካ ለውጡ ለውጭ ግንኙነት ያለውን አንድምታ መዳሰስ ነው።

## 2 የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ እና አገራዊ፣ አካባቢያዊና የዓለም አቀፉ ሥርዓት ተፅዕኖዎቹ

የኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ዋና ዋና ዓላማዎች የአገሪቱን ደህንነት፣ የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት ማስጠበቅ ነበር (Berouk, 2004)። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና የደርግ መንግሥታት የአገር ውስጥ እና የውጭ የደህንነት ሥጋት ተጋርጦባቸው ስለ ነበር የውጭ ጉዳይ ፖሊሲዎቻቸውም ለሉዓላዊነት እና ለግዛት አንድነት ከፍ ያለ ትኩረት ይሰጡ ነበር። የኢሕአዴግ መንግሥት በ1983[2] ሥልጣን ከያዘ በኋላ ሁለት ጊዜ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ሠነዶችን አትሞ አሰራጭቷል። የመጀመሪያው 1989 በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀደቀው "የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ" ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በ1994 በማስታወቂያ ሚኒስቴር ታትሞ የተሰራጨው "የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ እና የብሔራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ" ነው።

የ1989 ፖሊሲ ዋናው ዓላማ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲን በአገሪቱ ከተደረገው የፖለቲካ ለውጥና በ1987 ከወጣው የፌዴራል ሕገ-መንግሥት ጋር ማጣጣም ነበር። በዚህም መሠረት ፖሊሲው የኢትዮጵያን የውጭ ጉዳይ መርሆዎችና ዓላማዎች ያካተተ ሲሆን፤ ከነዚህም መካከል የኢትዮጵያንና ሕዝቦቿዋን ሉዓላዊነት፣ ነጻነትና ክብር ማስጠበቅ፣ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መጠናከር እና ፈጣን የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ዕድገትን በማረጋገጡ ሂደት የጎላ አስተዋጽኦ ማድረግ የሚሉ ዓላማዎች ይገኙበታል (የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ 1989)።

በ1994 የወጣው የውጭ ጉዳይና እና የብሔራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ብሔራዊ የደህንነት ሥጋት ምንጭን ቀድሞ ከነበረው አስተሳሰብ በተለየ መልኩ ለአገር ውስጥ ሁኔታዎች ትኩረት (ቅድሚያ) ሰጥቷል። በዚህም መሠረት ሠነዱ አገሪቱ ዋና የደህንነት ሥጋት ምንጮች ድህነትና ኋላ ቀርነት ናቸው ሲል ከመደምደሙም በላይ እነዚህን የሥጋት ምንጮት ለመመከትና የአገሪቱን ቀጣይ ህልውና ለማረጋገጥ የልማት እና ዲሞክራሲን አስፈላጊነት ላይ አፅንዖት ይሰጣል። ይህ የፖሊሲ ሠነድ በውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ሠነዶች ባልተለመደ መልኩ ከኢትዮጵያ ጋር የቀረበ ግንኙነት ያላቸውን አገራት ሁኔታ ከመገምገሙም በላይ ኢትዮጵያ በአገራቱ አንፃር ልተከተል ስለሚገባው ፖሊሲ አቅጣጫ ይጠቁማል (Ministry of Information, 2002)። በአሁኑ ጊዜ በሠነዱ ላይ ያሉትን

[2] በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የተጠቀሱት ዓመታት በተለይ ካልተጠቀሰ በስተቀር በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ናቸው።

ድክመቶች ለማረምና የአገሪቱን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ከወቅቱ ሁኔታ ጋር ለማዛመድ በሚል መንግሥት በዚህ ሠነድ ላይ ክለሳ እያካሄደ ይገኛል።

የአገራት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲዎች ምንም እንኳን ከጊዜ ወደ ጊዜ፣ ከመንግሥት መንግሥት ቢቀያየሩም፤ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ መርሆዎችና ዓላማዎች ለውጥና መወራረስ ይታይባቸዋል። የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ዓላማዎችና አተገባበር ላይ ተፅዕኖ የሚያመጡ ሁኔታዎችን በሦስት ዋና ዋና ደረጃዎች መተንተን ይቻላል። እነርሱም አገራዊ፣ አካባቢያዊ (ቀጣና) እና የዓለም አቀፉ ሥርዓት ናቸው።

## 2.1 አገራዊ ሁኔታዎች

የውጭ ግንኙነትን በተመለከተ የአንድ አገር ውስጣዊ ሁኔታ ሲገመገም የሚከተሉት ጉዳዮች መታየት ይኖርባቸዋል። የመጀመሪያው የአገሪቱ መልክዓ-ምድር (ጂኦግራፊ) ነው። ኢትዮጵያ በግምት 1,127,127 ካሬ ኪ.ሜ የቆዳ ስፋት ሲኖራት 5,311 ኪ.ሜ ርዝመት ያላቸው ድንበሮችን ከጎረቤት አገራት ጋር ትጋራለች። አገሪቱ በልዩ ልዩ መልክዓ-ምድር አይነቶች የታደለች ናት። እነዚህም ከፍ ያሉ ተራሮች፣ በተራሮች ላይ የሚገኙ ሜዳማ ቦታዎች (ፕሌቶዎች)፣ ሸለቆዎችና ዝቅ ያሉ ቦታዎች ናቸው።

የአገሪቷ የመልክዓ-ምድር አቀማመጥ በውጭ ግንኙነት ላይ ጉልህ ተፅዕኖ ያሳድራል። በመጀመሪያ፣ ኢትዮጵያ የምትገኘው እጅግም ባልተረጋጋውና ኤስያና አውሮፓን እንደ ድልድይ በማገናኘት ከፍ ያለ ጂኦ-ስትራቴጂክ ዋጋ ባለው በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ነው። በተጨማሪም ከ1983ቱ የኤርትራ መገንጠል በኋላ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ስትሆን፤ ይህ ወደብ አልባነት ከ100 ሚሊዮን በላይ ሕዝብና ሰፊ የቆዳ ስፋት ባላት ኢትዮጵያ ላይ ከፍ ያለ ኢኮኖሚያዊና ጂኦ-ፖለቲካዊ ተግዳሮቶች አሳድሯል። በተጨማሪም ከአገሪቷ መንጭተው ወደ ጎረቤት አገራት የሚፈሱት ወንዞች በአገሪቷ የውጭ ግንኙነት ላይ ተፅዕኖ የሚፈጥሩ የተፈጥሮ ስጦታዎች ናቸው።

ከጂኦግራፊ በተጨማሪ ሌላው በአገሪቷ የውጭ ግንኙነት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር የአገር ውስጥ ሁኔታ የሕዝብ ብዛት ነው። በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ከ100 ሚሊዮን በላይ የህዝብ ብዛት በመያዝ ከናይጄሪያ በመቀጠል በአፍሪካ ከፍ ያለ የሕዝብ ብዛት ያላት አገር ሆናለች። በአገሪቱ ባለው ከፍተኛ (2.6 ከመቶ) የሕዝብ ዕድገት ምጣኔ ሳቢያ ከአጠቃላዩ የአገሪቱ ሕዝብ መካከል ወጣቶች ከፍ ያለውን ድርሻ ይወስዳሉ (CSA, 2013)። በዚህም ምክንያት በየዓመቱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወጣቶች ሥራ ፈላጊ ይሆናሉ (CSA, 2013b)። ኢኮኖሚው የሚፈጥረው የሥራ ዕድል ውስን በመሆኑ ከፍ ያለ የወጣት ሥራ አጥነት ችግር በአገሪቱ ይታያል። ለምሳሌም በ2002 የወጣት ሥራ አጥነት ምጣኔ 23.7 ከመቶ እንደነበር ተገምቷል

(CSA, 2013b)። ሥራ-አጥ ወጣቶች ዓለም አቀፍ ፍልሠትን እንደ አማራጭ በመውሰዳቸው በየዓመቱ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ወጣት ኢትዮጵያውያን ወደ አረብ ባሕረ-ሰላጤ አገራት፣ ወደ ደቡብ አፍሪካና አውሮፓ ይፈልሳሉ። አብዛኛው ፍልሠት የሚካሄደው ኢ-መደበኛ በሆነ መልኩ በመሆኑ፤ ሂደቱ ኢትዮጵያ ከተቀባይ አገሮች ጋር ባላት የውጭ ግንኙነት ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ አልቀረም።

ሌላው የውጭ ግንኙነት ላይ አንድምታ የሚያሳድረው የአገር ውስጥ ጉዳይ የኢኮኖሚ ሁኔታ ነው። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በግብርና ላይ የተመሠረተ ሲሆን ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነው የአገሪቱ ሕዝብ የሚተዳደረው በግብርና ሥራ ነው። የተባበሩት መንግሥታት የልማት ድርጅት በ2010 ባወጣው የሠብዓዊ ልማት ሪፖርት መሠረት፤ አገሪቱ ከ189 አገራት እና ግዛቶች ውስጥ 173ኛ ሆናለች (UNDP, 2019)። ያም ሆኖ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ጠንካራ ዕድገት አሳይቷል። ኢኮኖሚን በተመለከተ የኢትዮጵያ የውጭ ፖሊሲ ዓላማ ከልማት አጋሮች በተለያዩ መንገዶች ለልማት የሚውል ሀብት ማሰባሰብ የሚለውን የሚያካትት ሲሆን በዚህ ረገድ ባለፉት 27 ዓመታት የኢትዮጵያ መንግሥት ስኬታማ ሆኗል። በዚህም መሠረት አገሪቷ በአማካይ ከሶስት ቢሊዮን ዶላር በላይ በየዓመቱ በዕርዳታ እና በድጋፍ ስታገኝ ነበር (Ben *et al,* 2010)። ከብድርና ዕርዳታ ከማሰባሰብ በተጨማሪ አገሪቱ የውጭ ቀጥተኛ መዋዕለ-ንዋይ ለመሳብ ከፍ ያለ ጥረት አድርጋለች። በመሆኑም በ2009 ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት 4 ቢሊዮን ዶላር ደርሶ ነበር (UNCTD, 2019)።

በመጨረሻም በአንድ አገር ውስጥ ያለ የፖለቲካ ሥርዓት በውጭ ጉዳይ ፖሊሲና አተገባበር ላይ ተፅዕኖ ያደርጋል። በግንቦት 1983 በኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማሪያም ይመራ የነበረውን ወታደራዊ መንግሥት በትጥቅ ትግል አስወግዶ ሥልጣኑን የተቆጣጠረው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) የአገሪቱን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ጨምሮ ሌሎች በርካታ ፖሊሲዎችን የቀየሩ እርምጃዎች ወስዷል።

ኢሕአዴግ በሐምሌ 1983 ባዘጋጀው የሠላምና ዴሞክራሲ ጉባዔ የጸደቀው የሽግግር ቻርተር የኤርትራን መገንጠል ከማረጋገጡም በላይ የ"ብሔሮች እና ብሔረሰቦች" መብቶችን እስከ መገንጠል የሚለውን መርህ ተቀብሏል። የቻርተሩን መርሆዎች በመከተል በ1984 ቋንቋንና የብሔር ማንነትን መሠረት ያደረጉ 14 የክልል አስተዳደሮች ተቋቁመዋል። በ1987 የጸደቀው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢፌዴሪ) ሕገ-መንግሥት ልክ እንደ ቻርተሩ ሁሉ የብሔር ብሔረሰቦችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል ዕውቅና ከመስጠቱም በተጨማሪ በብሔር ማንነት ላይ የተመረኮዘ የፌዴራል ሥርዓት መሠረተ። የፌደራል ሥርዓቱ በብሔር ማንነት ላይ መመስረቱ እና ከአንድነት

ይልቅ ለልዩነት ከፍ ያለ ቦታ መስጠቱ ለተለያዩ በአገር ውስጥ ለሚከሰቱ ግጭቶች ምክንያት ሆኗል።

ሕገ-መንግሥቱ ዓለም አቀፍ የሠብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ከማካተቱ በተጨማሪ ፓርላመንታዊ ሥርዓተ-መንግሥት አቋቁሟል። ከ1983 እስከ 2010 ባሉት ዓመታት ውስጥ አገሪቱ የተረጋጋች ነበረች። የፖለቲካ መረጋጋትና የኢሕአዴግ መንግሥት የተከተላቸው ፖሊሲዎች ከ1992 ጀምሮ ለታየው የኢኮኖሚ ዕድገት እንደ ዋና ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ። በነዚህ ዓመታት ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ካሉ ፈጣን ዕድገት ካሳዩ 10 አገሮች ውስጥ አንዷ ለመሆን ችላለች። ባለፉት ሁለት አስርተ-ዓመታት በተደረገው ጥረት የመሠረተ-ልማት እና የማኀበራዊ አገልግሎት አቅርቦት በከፍተኛ ሁኔታ ተሻሽሏል።

በተቃራኒው ግን የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታን በተመለከተ ከፍ ያለ ተግዳሮቶች ገጥመውታል። በአንድ በኩል የፖለቲካው ምህዳሩ እያደር በመጥበቡ ምክንያት ምንም እንኳን በኦፊሴል አገሪቱ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት የምትከተል ብትሆንም በተግባር ግን ኢሕአዴግ ብቸኛ ፓርቲ ለመሆን በቅቶ ነበር። ለዚህ ሁነት ዋና ማሳያው በ2007 በተካሄደው አምስተኛው ጠቅላላ አገራዊ ምርጫ ኢሕአዴግና አጋሮቹ በፌዴራል ፓርላማ ውስጥ የሚገኙትን ሁሉንም መቀመጫዎች መቆጣጠራቸው ነበር። በሌላ በኩል የኢሕአዴግ መንግሥት በተለይም ከ1997 ምርጫ በኋላ በወሰዳቸው ሀሳብን በነፃነት የመግለጽና የመደራጀት መብቶችን የመገደብ እርምጃዎችና የኢኮኖሚ ዕድገቱ ያመጣው ሀብት ክፍፍል ፍትሀዊነት ይጎድለዋል የሚለው አስተሳሰብ መጠናከር ምክንያት በሕዝብና በመንግሥት መካከል ያለው ክፍተት እየጎላ መጣ።

ኢሕአዴግ መቶ በመቶ ካሸነፈው የ2007 ምርጫ ተከትሎ በመጀመሪያ በኦሮሚያ ቀጥሎም በአማራ ክልል ወጣቶች በስፋት የተሳተፉበት ሕዝባዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ተጀመረ። እነዚህ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ኢሕአዴግ ውስጥ በተለይም ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በ2004 በሞት ከተለዩ በኋላ ከተከሰተው የውስጥ ክፍፍልና የሥልጣን ሽኩቻ ጋር በመደመር ኢሕአዴግን በእጅጉ በማዳከሙ፤ ድርጅቱ ታህሣስ 2010 ሥር-ነቀል ለውጦችን ለማካሄድ እንዲወስን ተገድዷል። የጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ በፈቃዳቸው ሥልጣናቸውን መልቀቅ ተከትሎ ዶ/ር ዐቢይ አህመድ በሚያዚያ 2010 ጠቅላይ ሚኒስትር በመሆን ተሹመዋል። ለውጡን ተከትሎ በርካታ የፖለቲካ እስረኞች ከመፈታታቸው በተጨማሪ ከአገር ውጭ ይንቀሳቀሱ የነበሩ የፖለቲካ ኃይሎች ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ተፈቅዶላቸዋል። በተጨማሪም የዲሞክራሲና ሠብዓዊ መብትን የሚገድቡ ሕጎች ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት በፖለቲካ ምህዳሩ በርካታ ተዋናዮች በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ።

እየተወሰዱ ያሉት የማሻሻያ እርምጃዎች ከላይ እንደተጠቀሰው ተስፋን የሚፈጥሩ ቢሆኑም በአገሪቱ አንዳንድ ክፍሎችም አሳሳቢ ሁኔታዎችም ተከስተዋል፡፡ ከ1.4 ሚሊዮን በላይ ሰዎች በግጭት ምክንያት ከቀዬያቸው ከመፈናቀላቸው በላይ በፖለቲካ ኃይሎች መሀከል የሥልጣን ሽኩቻዎች ተከሰተዋል፡፡ በተለይም በፖለቲካ ለውጡ መርሆና አቅጣጫ ላይ በኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች መካከል የጎላ ክፍፍል ተከስቷል፡፡ በታህሳስ 2012 ኢሕአዴግ አባል ድርጅቶቹና አጋሮችን በማዋሀድ ወደ ብልፅግና ፓርቲ ሲሸጋገር የድርጅቱ መሥራች የነበረው ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) ውህደቱን ከመቃወሙም በላይ በአሁኑ ወቅት የብልፅግና ፓርቲና የጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አህመድ ዋና ተቃዋሚ ሆኗል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አህመድ የጀመሯቸው ማሻሻያዎች በህዝብ እና በብዙ የተቃዋሚ ቡድኖች ሰፊ ድጋፍ ያላቸው ቢሆኑም፣ በለውጡ ጥልቀት እና አቅጣጫ ላይ በፓርቲዎችና በሌሎች ባላድርሻ አካላት መሀከል ድርድር ባለመደረጉና ስምምነት አለመኖሩ እንደ ትልቅ ተግዳሮት ሊቆጠር ይችላል፡፡ በአገሪቱ እየተደረገ ያለው የፖለቲካ ለውጥ ስኬት አንዱ መገለጫ የሚሆነው በኮሮና ቫይረስ ዓለም አቀፍ ወረሽኝ ምክንያት የተራዘመውን ምርጫ ግልጽ፣ ዲሞክራሲያዊና ተዓማኒ በሆነ መልኩ ማደረግ መቻል ወይም አለመቻል ነው ማለት ይቻላል፡፡

## 2.2 አካባቢያዊና ጂኦ-ፖለቲካዊ ሁኔታዎች

የአፍሪካ ቀንድ ቀጣና ስለሚያቅፋቸው አገሮች የተለያየ አስተሳሰብ ቢንጸባረቅም የምሥራቅ አፍሪካ በይነ-መንግሥታት ድርጅት (ኢጋድ) አባል አገሮችን ማለትም ጅቡቲ፣ ኤርትራ፣ ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ሶማሊያ፣ ደቡብ ሱዳን እና ዑጋንዳ በአፍሪካ ቀንድ እንደሚገኙ አገሮች አድርጎ መቁጠር ይቻላል፡፡ ቀጣናው ለግጭት ተጋላጭ የሆነና ከውጭ በሚነሱና በአገር ውስጥ በሚመነጩ ግጭቶች የተጎዳ ነው፡፡ በቀጣናው የሚነሱ አብዛኛዎቹ ግጭቶች ከአንዱ ሀገር ወደ ሌላው በቀላሉ ስለሚዛመቱ ግጭቶቹ ዓለም አቀፋዊ ባህርይ አላቸው፡፡ በሌላ አነጋገር ቀጣናው የተሳሰረው በኢኮኖሚ፣ በመንገድና በኮሚኒኬሽን አውታሮች ሳይሆን በግጭት ነው፡፡

የቀጣናው ክፍለ-አህጉራዊ አደረጃጀትም ከሌሎች መሰል አደረጃጀቶች የተለየ ነው፡፡ ሌሎቹ ክፍለ-አህጉራዊ ድርጅቶች በመጠሪያቸው የቀጣናቸውን ስም ሲይዙ የኢጋድ ስም ግን የአካባቢውን መጠሪያ አያመለክትም፡፡ ከሌሎቹ ክፍለ-አህጉራዊ ድርጅቶች በተለየ መልኩ ኢጋድ የተቋቋመው በተባበሩት መንግሥታት አነሳሽነት ነው፡፡ የኢኮኖሚ ትብብርን በተመለከተ አብዛኛዎች የኢጋድ አገራት ለሌሎች ክፍለ-አህጉራዊ ተቋማት ቅድሚያ ይሰጣሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል ኬንያ፣ ዑጋንዳና ደቡብ ሱዳን የምሥራቅ አፍሪካ ማህበረሰብ

(East Africa Community) አባል አገራት ሲሆኑ አብዛኛው የኢኮኖሚ ትብብራቸውንም የሚያደርጉት በዚህ ድርጅት አማካይነት ነው።

በቀጣናው በርካታ አሁናዊና የተዳፈኑ ግጭቶች አሉ። በመሆኑም በሶማሊያ፣ በሱዳንና በደቡብ ሱዳን የተባበሩት መንግሥታት እና የአፍሪካ ሕብረት የሠላም አስከባሪ ኃይሎች ተሰማርተዋል። በቀጣናው በሚካሄዱ የሠላም ማስከበርና ግንባታ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ኢትዮጵያ የጎላ ሚና ትጫወታለች። የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በተባበሩት መንግሥታትና በአፍሪካ ሕብረት የሠላም ማስከበር ተልዕኮዎች ውስጥ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ያበረክታል። ለዚህም ነው ብዙ የቀጣናው ታዛቢዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ግጭትና ያለመረጋጋት መከሰት ለቀጣናው ጎጂ አንድምታ ይኖረዋል የሚሉት። ባለፉት ሁለት ዓመታት ሁለቱ የቀጣናው ሰፋፊ አገራት፤ ኢትዮጵያና ሱዳን፤ በፖለቲካ ሽግግር ውስጥ ይገኛሉ። በሁለቱም አገሮች የሚደረገው ሽግግር ዕድሎችና ተግዳሮቶች ያሉት ሲሆን፤ የተሳካ ዲሞክራሲያዊና ሠላማዊ ሽግግር በሁለቱም አገሮች ውስጥ ማድረግ ለቀጣናው ሠላምና መረጋጋት ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

የሚከተሉት ዋና ዋና የቀጣናው ጂኦ-ፖለቲካዊ ባህርያት በኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ላይ ጉልህ በጎና ጎጂ ተፅዕኖዎች ይኖራቸዋል። በመጀመሪያ፣ በቀጣናው የሚገኙ ያሉ አገራት ድንበሮች በተገቢው መንገድ (በስምምነት) የተካለሉ ባለመሆናቸው የግጭት ምክንያቶች ናቸው። ኢትዮጵያን ብንወስድ ከኢትዮ-ኬንያ ድንበር ውጭ ያሉት ድንበሮች በአብዛኛው የተካለሉ ባለመሆናቸው የግጭት ምክንያት ሆነዋል። ምንም እንኳን ያልተካለሉ ድንበሮች ዋና የግጭት ምክንያት ናቸው በማለት መደምደም ቢያስቸግርም፤ በድንበር ምክንያት ኢትዮጵያ ከሶማሊያና ከኤርትራ ጋር ግጭት (ጦርነት) ውስጥ ገብታለች። የኢትዮጵያ እና ሱዳን ድንበር ሳይካለል ለረጅም ዓመታት መቆየትም በየጊዜው ለሚነሱ ግጭቶች ምክንያት ሆኗል። የቀጣናው ድንበሮች በአብዛኛው በቅኝ ግዛት ውል የተሰመሩ በመሆናቸው ቋንቋንና ባህልን የሚጋሩ ማህበረሰቦችን ይከፋፍላሉ፤ ይህም አንዳንድ ጊዜ የግጭት መንሥዔ ሲሆን ይስተዋላል።

ሁለተኛ፣ ቀጣናው ከሌሎች የአፍሪካ ክፍለ-አኀጉሮች በተለየ መልኩ የመገንጠል ግጭቶችን አስተናግዷል። ኤርትራ ከ30 ዓመታት ግጭት በኋላ በ1983 ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ነፃ መንግሥት መስርታለች። በተመሳሳይ መልኩ ደቡብ ሱዳንም ከረጅም ዓመታት ደም አፋሳሽ ግጭት በኋላ በሐምሌ 2003 ነፃነቷን አውጃለች። ምንም እንኳን ዓለም አቀፍ እውቅና ባታገኝም ሶማሌላንድ በግንቦት 1983 ከሶማሊያ በመለየት ነፃነቷን አውጃለች። አዳዲስ መንግሥታት በመገንጠል መመስረታቸው ምንም እንኳን ደም አፋሳሽ ጦርነቶች እንዲቆሙ ቢረዳም ዘላቂ ሠላምና ትብብር በማምጣት ረገድ የረባ ትሩፋት አላስገኘም። ለዚህም ጉልህ

ምሳሌ የሚሆነው ተገንጠለው እንደ አዲስ በተመሠረቱት እና በነባሮቹ አገራት መካከል የተከሰቱት የድንበር ግጭቶች ናቸው። በኤርትራና በኢትዮጵያ መካከል የተፈጠረው የድንበር ግጭት ወደለየለት ጦርነት በማምራት በሁለቱም አገራት ላይ ከፍ ያለ ጉዳት አድርሷል። በደቡብ ሱዳን እና በሱዳን መካከል የተነሳው የወሰን ጥያቄ ወደ ግጭት ያላመራው የተባበሩት መንግሥታት የሠላም አስከባሪ ጦር በአካባቢው በመሰማራቱ ነው። እንደ አዲስ የተመሠረቱት መንግሥታትም የውስጥ ሠላምን በማስፈን በኩል ያላቸው ውጤት ደካማ ሆኖ ተገኝቷል። በደቡብ ሱዳን በመሪዎች መካከል የተነሳው የሥልጣን ሽኩቻ ወደለየለት የርስ በርስ ጦርነት በማምራቱ አገሪቷን ከፍ ላለ የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ቀውስ ዳርጓታል።

ሦስተኛ፣ የአፍሪካ ቀንድ ጂኦ-ፖለቲካዊ ጠቀሜታ በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ግንኙነት ላይ ከፍ ያለ አንድምታ አለው። ቀጣናው ከፍ ያለ ስልታዊ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን፤ በተለይም ቀጣናው በአውሮፓና በኤስያን መካከል ላለው ግዙፍ የንግድ ልውውጥ እንደ ድልድይ ሆኖ ያገለግላል። በቀጣናው ባለው ያለመረጋጋት፣ የሽብርና የባህር ላይ ውንድብና ሥጋት ምክንያት ባለፉት ጥቂት ዓመታት በርካታ አገራት በአፍሪካ ቀንድና አካባቢው የጦር ሠፈሮቻቸውን በመመስረት ላይ ናቸው። የጦር ሠፈር በአካባቢው ከመሠረቱት በርካታ አገራት መካከል ፈረንሳይ፣ አሜሪካ፣ ቻይና፣ ጃፓን፣ ሕንድ፣ ቱርክና የተባበሩት አረብ ኢሚሬት የሚገኙበት ሲሆን፤ ወትሮውንም የመረጋጋት ችግር ባለበት የአፍሪካ ቀንድ የነዚህ የጦር ሠፈሮች መበራከት ለቀጣናው ዘላቂ ሠላም ተጨማሪ የሥጋት ምንጭ ሆኗል።

አራተኛ፣ በቀጣናው የተከሰተው ድንበር ዘለል ሽብርተኝነት ሌላው የኢትዮጵያን የውጭ ግንኙነት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር ሁኔታ ነው። ብዙዎች የቀጣናው አገሮች የተለያዩ የሽብር ጥቃቶች ሰለባ ነበሩ። መስከረም 1994 አልቃይዳ በአሜሪካ ላይ ካደረገው የሽብር ጥቃት በኋላ አሜሪካና አጋሮቿ የምዕራብ አገሮች ተመሳሳይ የሽብር ጥቃትን ለመከላከል ሲሉ ከቀጣናው አገሮች ጋር ከፍ ያለ ትብብር መስርተዋል። በወቅቱ የነበረው የሱዳን መንግሥት ለአልቃይዳ መሪዎች ድጋፍ ይሰጥ ስለነበረና ሶማሊያም መንግሥት አልባ ስለነበረች ቀጣናው የሽብርተኞች መሸሸጊያ ይሆናል በሚል ከፍተኛ ሥጋት ነበር። ከቀጣናው አገሮች መካከል ኢትዮጵያ፣ ኬንያ እና ዑጋንዳ አሜሪካ ከ1994ቱ ጥቃት በኋላ በከፈተችው ዓለም አቀፍ የፀረ-ሽብርተኝነት ጦርነት ተሳታፊ ሆነዋል። በዚህም ምክንያት አገራቱ ከአሜሪካና ከሌሎች የምዕራብ አገሮች የመከላከያ፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ድጋፍ አግኝተዋል።

አምስተኛ፣ ድንበር አቋራጭ የተፈጥሮ ሀብቶች እና አጠቃቀማቸው በአንድ አገር የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር ጉዳይ ነው። የተፈጥሮ ሀብቶች ብዙውን ጊዜ የአገራትን ድንበር አያከብሩም። በተለይም ወንዞችና የውኃ አካላት ድንበርን የሚያቋርጡ

የተፈጥሮ ሀብቶች ናቸው፡፡ ብዙዎቹ የኢትዮጵያ ታላላቅ ወንዞች ድንበርን አቋርጠው ወደ ጎረቤት አገሮች የሚፈሱ ሲሆን ወንዞቹን በጋራ ለመጠቀም የሚረዱ የትብብር ማዕቀፎች ባለመዘርጋታቸው ወንዞቹ የትብብር ምክንያት ከመሆን ይልቅ ለኢትዮጵያ የሥጋት ምንጭ ሆነዋል፡፡ ለዚህ ሁኔታ ግልጽ ምሣሌ የሚሆነው የዓባይ (ናይል) ወንዝ ነው፡፡ የናይል ወንዝ ተፋሰስ 11 አገሮችን ሲያቅፍ በአሁኑ ወቅት ወደ 300 ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ ይኖርበታል፡፡ ከ85 በመቶ በላይ የናይል ወንዝ ውኃ የሚመነጨው ከኢትዮጵያ ቢሆንም የናይል ወንዝን አጠቃቀም የሚደነግጉት የቅኝ ግዛት ዘመን ስምምነቶች የውኃውን ተጠቃሚነትን ለግብፅ እና ለሱዳን ሰጥተዋል፡፡ ይን እንጂ ስምምነቶቹ በኢትዮጵያ ዘንድ ተቀባይነተ አላገኙም፡፡ በወንዙ አጠቃቀም ላይ ያላትን የበላይነት ማጣት የማትፈልገው ግብፅ ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ተጠቃሚ እንዳትሆን ለብዙ ዘመናት ከመስራቷም በተጨማሪ ኢትዮጵያን ለማዳከም በአገሪቷ ውስጥ በሚነሱ የርስ በርስ ግጭቶች ውስጥ ለረጅም ጊዜ በተዘዋዋሪ መንገድ ተሳታፊ ሆና ቆይታለች፡፡

በአሁኑ ወቅት ከኢትዮጵያ ውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ዓብይ ጉዳዮች አንዱ በዓባይ ላይ በመገንባት ላይ የሚገኘው የሕዳሴ የሀይል ማመንጫ ግድብን አጠናቅቆ ወደ ሥራ ለማስገባት ግብፅ በዓለም አቀፍ መድረክ የምትፈጥረውን ተፅዕኖ መቋቋም ነው፡፡

## 2.3 ዓለም አቀፋዊ ሥርዓት

የዓለም አቀፍ ሥርዓት ማለት በመላው ዓለም የሚገኙ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተዋናዮች የሚፈጥሩት መስተጋብር ነው፡፡ በዋነኝነት የዓለም አቀፉ የፖለቲካ ሥርዓት ተዋናዮች ሉዓላዊ መንግሥታት ወይም አገሮች ሲሆኑ፤ በመካከላቸው የሚደረግ ግንኙነትን በበላይነት የሚመራ ተቋም ወይም የዓለም መንግሥት የለም፡፡ ለዚህም ነው በዓለም አቀፍ ግንኙነት የትምህርት ዘርፍ ሥመ-ጥር የሆኑ ምሁራን ዘመናዊው የዓለም አቀፍ ሥርዓት (መንግሥት) ወይም አለቃ-አልባ (anarchic) ነው የሚሉት (Bull, 1995)፡፡ ይህ ማለት ግን ዓለም አቀፍ ግንኙነት የሚገዛበት ሕግ የለውም ማለት አይደለም፡፡ ምንም እንኳን ዓለም አቀፍ ሕግ በስራ ላይ መዋሉን የሚቆጣጠር መንግሥታዊ ተቋም ባይኖርም መንግሥታት በአብዛኛው ዓለም አቀፍ ሕግን ያከብራሉ፡፡ የዓለም አቀፉ ሥርዓት ባህርያት በአገራት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲና ግንኙነት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራሉ፡፡ መንግሥታት ሠላማቸውን እና ነፃነታቸውን የሚጠብቅላቸው ዓለም አቀፋዊ ተቋም ስለሌለ ሁሉም መንግሥታት ሁል ጊዜም ደህንነታቸውን ለመጠበቅ ዝግጁ መሆን ይገባቸዋል፡፡ ከራስ ዝግጁነት በተጨማሪም አገራት ሠላማቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ የቃል ኪዳን ህብረት (alliance) እና የጋራ ደህንነት ቃል ኪዳን (collective security) ተቋማትን ይፈጥራሉ፡፡

በተጨማሪም አገራት ሠላማቸውን ለመጠበቅ ሲሉ ከተቀናቃኝ አገሮች ጋር የኃይል ሚዛን ለመፍጠር ጥረት ያደርጋሉ።

ከዓለም አቀፉ ሥርዓት ባህርያት መካከል በአገራት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ላይ ከፍተኛ አንድምታ የሚያመጣው በሥርዓቱ የሚገኙ የኃያላን ወይም የልዕለ ኃያላን ቁጥር (ስርጭት) ነው (Keersmaeker, 2017)። በዚህም መሠረት ብዙ ኃያላን የሚገኙበት የዓለም አቀፍ ሥርዓት ባለ ብዙ ዋልታ (multi-polar)፤ ሁለት ኃያላን ያሉት ሥርዓት ባለ ሁለት ዋልታ (bi-polar) እና አንድ ብቻ ኃያል ያለው ሥርዓት ባለ አንድ ዋልታ (uni-polar) በመባል ይታወቃል። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ 1939 ጀምሮ እስከ የቀዝቃዛው ጦርነት ማብቂያ 1982 ድረስ የነበረው የዓለም አቀፍ ሥርዓት ባለ ሁለት ዋልታ ነበር። የሥርዓቱ ሁለት ዋልታዎች አሜሪካና የቀድሞዋ ሶቭየት ሕብረት ሲሆኑ፤ ሁለቱ ልዕለ ኃያላን አገሮች ተጻራሪ ርዕዮተ ዓለም፣ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ሥርዓት ከመከተላቸውም በላይ የየራሳቸውን ግዙፍ ወታደራዊ የቃል ኪዳን ማህበራትን መሥርተው ነበር። በተጨማሪም ሁለቱ ሀያላን አገሮችና አጋሮቻቸው ተፅዕኖቻቸውን በዓለም ዙሪያ ለማስፋት ተግተው ይሰሩ ነበር። በዚህም ምክንያት በታዳጊው ዓለም በተከሰቱ ልዩ ልዩ ግጭቶች ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ይሳተፉ ነበር። ለምሣሌ ያህል በቀጣናችን በኢትዮጵያ እና በሶማሊያ መካከል በነበረው ግጭት ሁለቱ ኃያላን አገሮችና አጋሮቻቸው ተሳታፊ ነበሩ። አሜሪካ ከ1967 ከኢትዮጵያ አብዮት በፊት ለንጉሱ መንግሥት ድጋፍ ስተሰጥ፤ ሶቭየት ሕብረት በበኩሏ ለሶማሊያ መንግሥት ድጋፏን ትሰጥ ነበር። ከአብዮቱ በኋላ ሶቭየት ሕብረት አጋርነቷን ወደ ኢትዮጵያ ስታዞር፤ አሜሪካና አጋሮቿ ለሶማሊያ መንግሥት ድጋፍ ይሰጡ ነበር።

በባለ ሁለት ዋልታ ዓለም አቀፍ ሥርዓት ውስጥ አገሮች ከሁለት ኃያላን አገራት አንዱን የመመረጥ የውዴታ ግዴታ ነበረባቸው። ይህ ያልተጻፈ ሕግ ለታዳጊ አገሮች አጋር አገሮችን ለመመረጥ የሚሰጠው ዕድል ውስን ነበር። የኢትዮጵያን ሁኔታ ስንመለከት ከላይ እንደተጠቀሰው በቅድመ-አብዮት ዘመን ኢትዮጵያ ከአሜሪካና ከሌሎች የምዕራብ አገሮች ጋር ጥብቅ ግንኙነት ሲኖራት፤ የንጉሥ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት አስወግዶ ሥልጣን የያዘው ወታደራዊ መንግሥት የሶሻሊስት ርዕዮተ-ዓለም ተከታይ ስለነበረ ከቀድሞዋ ሶቭየት ሕብረት ጋር ጥብቅ የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ወታደራዊ ግንኙነት መስርቶ ነበር።

በ1982 የሶቭየት ሕብረትን መውደቅ ተከትሎ የቀዝቃዛው ጦርነት ሲጠናቀቅ፤ የሶሻሊስት ርዕዮተ-ዓለም ይከተሉ የነበሩ በርካታ የምሥራቅ አውሮፓ አገራትም ከሶቭዬት ሕብረት ተፅዕኖ ተላቅቀው ስር ነቀል የፖለቲካና ኢኮኖሚ ለውጦችን አደረጉ። የሶቭየት ሕብረትን የተካችው ሩሲያም የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተ-ዓለምን ወደ ጎን በመተው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ለውጦች አደረገች። ነገር ግን ከሶቭየት ሕብረት ውድቀት በኋላ እንደ አዲስ

የተመሠረተችው ሩሲያ እንኳን አሜሪካንን ልትቀናቀን ቀርቶ በወቅቱ በኢኮኖሚና በፖለቲካም በእጅጉ የተዳከመች ነበረች። በዚህም ምክንያት አሜሪካ በ1980ዎቹ እና በ1990ዎቹ ዓመታት ብቸኛ ልዕለ-ኃያል አገር ለመሆን በቃች። በመሆኑም በዚህ ወቅት የነበረው የዓለም አቀፍ ሥርዓት ባለ አንድ ዋልታ ነበር።

ባለ አንድ ዋልታ ዓለም አቀፍ ሥርዓት ኢትዮጵያን በመሳሰሉ ታዳጊ አገራት የውጭ ግንኙነት ላይ የጎላ ተፅዕኖ ያሳድራል። ይህ ሥርዓት በዋነኛነት አገራት ኃያላን ወዳጅ ለመመረጥ የሚችሉበትን ዕድል በማጥበብ ለብቸኛው ልዕለ-ኃያል አገር ከፍ ያለ ኃይል ይሰጣል። አሜሪካ በዚህ ዘመን ታዳጊ አገሮች ድጋፏን ለማግኘት ከፈለጉ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና ነፃ ኢኮኖሚ እንዲከተሉ ጫና ታደርግ ነበር።

ወደ ኢትዮጵያ ስንመለስ በዓለም አቀፉ ሥርዓት ላይ የተደረገው ሥር ነቀል ለውጥ በአገር ውስጥ ከተደረገ የፖለቲካ ለውጥ ጋር ተገጣጥሟል። የሶቭየት ሕብረት መንግሥት ከወደቀ አንድ ዓመት በኋላ በግንቦት 1983 በሶቭየት ሕብረት ይደገፍ የነበረው ወታደራዊ መንግሥት (ደርግ) በኢሕአዴግ ተገርስሶ ወድቋል። ደርግን የተካው ኢሕአዴግ በዓለም አቀፉ ሥርዓት የተደረገውን ለውጥ ከግንዛቤ በመውሰድ ይከተል የነበረውን የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተ-ዓለም ወደ ጎን በማድረግ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ እና የነፃ ኢኮኖሚ ሥርዓት ለመገንባት ቃል ገባ። በዚህም ምክንያት ከአሜሪካና ከአጋሮቿ ጋር ጥብቅ ወዳጅነትን መሠረተ። በዓለም አቀፉ ሥርዓት የአሜሪካ ብቸኛ ኃያልነት ለረጅም ጊዜ የዘለቀ አልነበረም። በተለይ ከ2000 ጀምሮ በዓለም አቀፉ ሥርዓት ከአሜሪካ በተጨማሪ ሌሎች ኃያላን አገሮች ተፅዕኖ ማሳደር ጀምረዋል። በአሁኑ ወቅት አሜሪካንን የሚገዳደሩ አገራት በርካታ ሲሆኑ ከነዚህ መካከል ቻይና፣ ሩሲያ፣ ሕንድ፣ ቱርክና ኢራንን መጥቀስ ይቻላል። በዚህም ምክንያት በአሁኑ ወቅት ያለው የዓለም አቀፉ የፖለቲካ ሥርዓት ባለ ብዙ ዋልታ (multi-polar) ነው። ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ታሪክ እንደምንገነዘበው ባለ ብዙ ዋልታ የዓለም ዓቀፍ ሥርዓት ቁልፍ ባህርያት መካከል ግጭትና ያለመረጋጋት ናቸው። በዚህም ምክንያት አገራት ደህንነታቸውን ለመጠበቅ በየጊዜው የሚለዋወጥ ወዳጅነት ወይም ወታደራዊ ሕብረት ይመሠርታሉ።

ባለ ብዙ ዋልታ ዓለም አቀፍ ሥርዓት ለታዳጊ አገሮች በርካታ በጎ አስተጽኦዎች ሊኖሩት ይችላል። በተለይም ሥርዓቱ አማራጭ የኢኮኖሚና የፖለቲካ አጋሮች ስለሚሰጥ ታዳጊ አገራት ወዳጅነታቸውን ከአንዱ አጋር ወደ ሌላው በመቀየር ከኃያላን አገራት የሚመጡባቸውን ጫናዎች ለመቋቋም ይችላሉ። ለምሣሌ ያህል በምዕራቡ ዓለም ጥብቅ የኢኮኖሚ ማዕቀብ የተጣለበት የዚምባብዌ መንግሥት ከውድቀት ሊድን የቻለው ከቻይና ባገኘው ከፍ ያለ የኢኮኖሚ ድጋፍ ነው። ኢትዮጵያም ከብዙዎቹ ኃያል አገሮች ጋር ወዳጅነት

በመመስረቷ ከባለ ብዙ ዋልታው የዓለም አቀፍ ሥርዓት ተጠቃሚ ሆናለች። በተለያዩ ምክንያቶች ዘላቂ የአገር ጥቅምን የሚጎዳ ተፅዕኖ ከአንዱ ኃያል አገር ቢመጣ ሌላውን ኃያል አገር በመጠቀም መቋቋም ስለሚቻል ይህ ሥርዓት ለኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት በጎ አንድምታ እንዳለው መረዳት ይቻላል።

## 3 ኢትዮጵያ ከጎረቤትና ከአርብ ባሕረ-ሠላጤ አገራት ጋር ያላት ግንኙነት

የዚህ ክፍል ዓላማ ኢትዮጵያ ከጎረቤትና ከገልፍ አገራት ጋር ያላትን ግንኙነቶች ዓበይት ባህርያት በአጭሩ መዳሰስ ሲሆን በዚህም ከውጭ ግንኙነት ታሪክ ይልቅ በወቅታዊ ሁኔታዎች ላይ ትኩረት ይሰጣል። በተለይም በአገሪቷ ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለው የፖለቲካ ለውጥ በውጭ ግንኙነት ላይ ያለውን አንድምታ ይቃኛል።

### 3.1 ኤርትራ

ኢትዮጵያና ኤርትራ በታሪክ፣ በባህልና በቋንቋ የሚዛመዱ ቢሆንም በሁለቱ አገሮች መካከል ያለው ግንኙነት ውስብስብ ሆኖ ቆይቷል። ኤርትራ ሦስት አስርት ዓመታት ከፈጀ ደም አፋሳሽ ጦርነት በኋላ በ1983 ከኢትዮጵያ መገንጠሏ በሁለቱ አገሮች የግንኙነት ታሪክ ላይ ያኖረው ጠባሳ አለ። በፀረ-ደርግ የትጥቅ ትግል ወቅት የሕዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ (ሕግሓኤ) አጋር የነበረው በሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) የሚመራው የኢሕአዴግ መንግሥት ከ1983 የመንግሥት ለውጥ በኋላ ኤርትራ ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያለው መንግሥት እንደትመሰርት ድጋፍ በመስጠቱ በሕግሓኤ እና በኢሕአዴግ የሚመሩት ሁለቱ መንግሥታት የሞቀ ግንኙነት መስርተው ነበር። ይህ የሞቀ ግንኙነት ለላቀ ቀጣናዊ ትብብር መንገድ ይከፍታል በሚል ከፍ ያለ ተስፋም ተጥሎበት ነበር። ነገር ግን በሁለቱ አገሮች መካከል ይደረግ የነበረው የኢኮኖሚና የንግድ ግንኙነት ሕግና ሥርዓትን ተከትሎ ባለመካሄዱ በኢትዮጵያ ወገን ቅሬታዎችን ከመፍጠሩ በተጨማሪ አልፎ አልፎ በመንግሥት አስፈፃሚዎች መካከል ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትራ በሚላኩ ዕቃዎችና ቀረጥ ሳይከፈልባቸው ከኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ በሚገቡ ሸቀጦች ምክንያት ያለመግባባቶች ይከሰቱ ነበር (ገብሩ፣ 2006)።

በተጨማሪም በሁለት መንግሥታት መካከል ድንበርን በተመለከተ ልዩነቶች እንደነበሩ ይታወቃል። ነገር ግን በድንበር ላይ ያላቸው ልዩነት አገራቱን ወደለየለት ጦርነት ይወስዳቸዋል ብሎ መገመት አስቸጋሪ ነበር። በድንበር ላይ የነበረው ውጥረት የኤርትራ መንግሥት በግንቦት 1990 ወታደራዊ ኃይል በመላክ በሰሜን ትግራይ የምትገኘውን ባድሜን ሲቆጣጠር በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የሁለቱን አገራት ዜጎችን ሰለባ ያደረገና የኢኮኖሚ ውድመት ያመጣ ጦርነት ተቀሰቀሰ። የጦርነቱ ምክንያቶች በርካታ ሲሆኑ ከነዚህ መካከል

የሚከተሉት ከፍ ያለ ሚና ተጫውተዋል ማለት ይቻላል። አንደኛው በኤርትራ መንግሥት መሪዎች ይንፀባረቅ የነበረው የወታደራዊ ኃይል የበላይነት ስሜት እና እንዲሁም መሪዎቹ አለመግባባቶችን ለመፍታት ኃይልን ለመጠቀም የነበራቸው ፍላጎት ሲሆን ለዚህም አንዱ ማስረጃ የኤርትራ መንግሥት አገሪቱ ነፃነቷን ካወጀች አስር ዓመት እንኳን ሳይሞላት ድንበርን በተመለከተ ከየመን፣ ከጅቡቲ እና ቀጥሎም ከኢትዮጵያ መጋጨቱ ነበር።

ከ1990-1992 በሁለቱ አገራት መካከል የተካሄደው ጦርነት በኤርትራ ተሸናፊነት ቢጠናቀቅም፤ በታህሣስ 1992 ሁለቱ አገራት በአልጀርስ የተፈራረሙት የሠላም ስምምነትና የድንበር ግጭታቸውን ለዓለም አቀፍ የግልግል ፍ/ቤት ለማቅረብ መስማማታቸው ከኢትዮጵያ ይልቅ ለኤርትራ የጠቀመ ነበር። በአልጀርሱ ስምምነት መሠረት የተቋቋመው የድንበር ፍርድ ቤት በሚያዚያ 1994 አጨቃጫቂዋን ባድሜ ለኤርትራ በመስጠቱና ኢትዮጵያም ውሳኔውን ውድቅ በማደረጓ የአልጀርስ ስምምነትና የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ዘላቂ ሠላም ለማምጣት ያግዛል የሚለው አስተሳሰብ ውድቅ ሆነ። በመሆኑም የሁለቱ አገራት ግንኙነት ከ1992 እስከ 2010 በውጥረት የተሞላ ነበር። በአንድ በኩል ሁለቱም አገሮች ‹‹የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው›› የሚለውን ነባሩን የቀጣናውን ብሂል በመከተል አንዱ የሌላውን ተቋዋሚ ድርጅቶች ሲደግፉ፣ በድንበር አካባቢ ደግሞ ወታደሮቻቸው በፍጥጫ ላይ ነበሩ።

በሌላ በኩል የአልጀርሱ ስምምነት ታዛቢ የነበሩት አገራት እና እንደ አፍሪካ ሕብረት ያሉት ተቋማት የድንበር ፍ/ቤቱ ውሳኔ ተግባራዊ እንዲሆን በኢትዮጵያ ላይ ተፅዕኖ አላደረጉም በሚል ቅሬታ የኤርትራ መንግሥት በአፍሪካ ሕብረትና በኢጋድ ውስጥ የነበረውን ተሳትፎ በዕጅጉ ቀነሰ፤ እንዲያውም ራሱን ከኢጋድ አባልነት አገለለ። በተጨማሪም በሶማሊያ ጉዳይ ውስጥ ጉልህ ሚና የምትጫወተውን ኢትዮጵያን ለመጉዳት በማለም በሶማሊያ ለሚንቀሳቀሱ ቡድኖች ድጋፍ ይሰጥ ነበር። ኢትዮጵያ በበኩሏ ይህን የኤርትራ ተግባር በማጉላት የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በኤርትራ ላይ ማዕቀብ እንዲጥል ብርቱ ጥረት አድርጋለች። ጥረቱም ሠምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ኤርትራ በተባበሩት መንግሥታት ማዕቀብ ስር ነበረች።

በኢትዮጵያ በ2010 የፖለቲካ ለውጥ ሲጀመር የቀድሞው ገዢ ፓርቲ ኢሕአዴግ ከወሰናቸው ቁልፍ ውሳኔዎች መካከል የኢትዮጵያ ኤርትራ የድንበር ውሳኔን ተቀብሎ በተግባር በማዋል የሁለቱ አገሮችን ግንኙነት ሠላማዊ ማድረግ ነበር። ውሳኔውን ተከትሎ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐብይ አህመድ በወሰዱት ቁርጠኛ ዕርምጃ የሁለቱን አገሮች ግንኙነት ሠላማዊ ለማድረግ ተችሏል። የሁለቱ አገሮች መሪዎች በየአገራቱ ተደጋጋሚ ጉብኝት ከማድረጋቸው በተጨማሪ ልዩ ልዩ ሥምምነቶችን ተፈራርመዋል። ለረጅም ጊዜ ተቀዛቅዞ የነበረው የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት፤ የቴሌኮሙኒኬሽና የትራንስፖርት አገልግሎት በሁለቱ አገራት መካከል በመፈቀዱ አሁን በተሻለ ሁኔታ ላይ ይገኛል። ከመስከረም 2010 ጀምሮ ሁለቱን አገሮች

የሚያገናኙ የየብስ መተላለፊያ መንገዶች ቢከፈቱም ተመልሰው ተዘግተዋል። ይህ ሁኔታም በሁለቱ አገሮች መካከል የኢኮኖሚ ትብብር ቢጠናከር የበለጠ ተጠቃሚ ሊሆን ይችል በነበረው በትግራይ ክልል ላይ ቅሬታን ፈጥሯል።

ምንም እንኳን በኤርትራና በኢትዮጵያ መካከል የነበረው ውጥረት ረግቦ ሠላማዊ ግንኙነት በመገንባት ላይ ቢሆንም፤ የሁለቱ አገሮች መፃኢ ግንኙነት በምን መልክ ይራመዳል የሚለው ሀሳብ ከመልስ ይልቅ በርካታ ጥያቄዎችን ያጭራል።

በመጀመሪያ፣ የድንበሩ ውዝግብ አሁንም ድረስ አልተቋጨም። የድንበር ፍ/ቤቱ ውሳኔ እንዴት ነው ተግባራዊ የሚደረገው? ውሳኔውስ ተግባራዊ ሲደረግ በድንበር ላይ የሚገኙ ማህበረሰቦች መብት ምን ይሆናል የሚሉት ጥያቄዎች አወዛጋቢ ናቸው።

ሁለተኛ፣ በሁለቱ አገሮች መካከል የሚኖረውን የኢኮኖሚ ግንኙነት፣ ንግድና ወደብ አጠቃቀም በተመለከተ አሁንም ግልፅ የሆነ የሕግ ማዕቀፍ አልተዘጋጀም። ሁለቱ አገራት ከቀድሞ ታሪካቸው በመማር ለነዚህ ጉዳዮች ትኩረት በመስጠት የሁለቱንም አገሮች ፍትሀዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ስምምነቶች ላይ መድረስ ለሁለቱ አገሮች ዘላቂ ሠላም ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

ሶስተኛ፣ በቀድሞው ገዢ ፓርቲ ኢሕአዴግ ውስጥ የተከሰተው ክፍፍልና ሕወሓት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አህመድ ከሚመሩት የብልፅግና ፓርቲ በተፃሪ መቆም ለሁለቱ አገሮች ግንኙነት ላይ የራሱ ጎጂ አንድምታ እንደሚኖረው አሌ የማይባል ጉዳይ ነው። ከዚህም አልፎ በሕወሓት መሪዎችና በጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ በሚመራው የፌዴራል መንግሥት መካከል ባለው ውጥረት ውስጥ የኤርትራ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መሳተፍ በአገራቱ ግንኙነት ላይ ጎጂ አንድምታ ይኖረዋል።

በመጨረሻም፣ ኤርትራ በቀጣናው የሚኖራት ሚናን በተመለከተ እስከ አሁን ግልፅ የሆነ ነገር የለም። የኤርትራው ፕሬዜዳንት ከኢትዮጵያ ጋር ወግኗል ብለው የሚወቅሱትን ኢጋድን ከማጠናከር ይልቅ በኢትዮጵያ፣ ኤርትራና ሶማሊያ መካከል የተጀመረውን አዲስ የትብብር ማዕቀፍ ለማጠናከር የሚተጉ ይመስላል። በሌላ በኩል የኢጋድ መዳከም የኢትዮጵያን ጥቅም የሚጎዳ በመሆኑ የኢትዮጵያ መንግሥት ከኢጋድ የበለጠ ለአዲሱ የትብብር ሙከራ ድጋፍ ያደርጋል ብሎ መጠበቅ አስቸጋሪ ነው።

## 3.2 ኬንያ

ኢትዮጵያና ኬንያ ከ55 ዓመት በላይ ሞቅ ያለ ግንኙነት አላቸው። የሁለቱ አገሮች ግንኙነት የተጀመረው ኬንያ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት በነበረችበት ዘመን ነበር። ከ1944 እስከ 1952

ኬንያ ውስጥ የማኡ ማኡ የፀረ-ቅኝ አገዛዝ አመጽ በተካሄድበት ጊዜ ኢትዮጵያ ለኬንያ የነፃነት ታጋዮች ድጋፍ ትሰጥ ነበር። ኬንያ በታኅሣሥ 1956 ከእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ነፃ ከወጣችበት ጊዜ ጀምሮ በሁለቱ አገሮች መካከል በቀላሉ የማይዋዥቅ የወዳጅነት ግንኙነት ለመመሥረት ተችሏል። ሁለቱ አገሮች በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት በተለይም ከ1967 እስከ 1983 ባለው በደርግ የሥልጣን ዘመን በርዕዮተ-ዓለምና በዓለም አቀፍ የኃይል አሰላለፍ በተፃራሪ ወገን ቢቆሙም፤ የሁለትዮሽ ግንኙነታቸው ግን መልካም ነበር። እዚህ ላይ በኢትዮጵያና ኬንያ መካከል ፀንቶ ለኖረው መልካም ግንኙነት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ያደረጉ ሁለት ምክንያቶችን መጥቀስ ይገባል።

አንደኛው በሁለቱ አገሮች መካከል የድንበር ወይም የግዛት ጥያቄ (ውዝግብ) አለመኖር ሲሆን  እንዲያውም በአገራቱ መካከል ያሉት ድንበሮች ስለተካለሉ ድንበሮች የጭቅጭቅ ምክንያት አይደሉም። ሁለተኛው ምክንያት ኢትዮጵያና ኬንያ በቀጣናው የሚጋሩት የደህነነት ሥጋት ነው። በተለይም በተለያየ ጊዜ ስልጣን ላይ የወጡት የሶማሊያ መንግሥታት በጎረቤት አገሮች የሚገኙ የሶማሌ ማህበረሰቦች በሙሉ ወደ ሱማሊያ ሪፑብሊክ መካለል አለባቸው የሚለው የግዛት ማስፋፋት ፖሊሲ ስጋት ሁለቱ አገራት በጋራ እንዲቆሙ ምክንያት ሆኗቸዋል። ሁለቱ አገሮች በታህሣሥ 1956 የትብብር እና የጋራ መከላከያ ሥምምነት የተፈራረሙ ሲሆን ሥምምነቱ የሁለቱን አገራት ሠላምና የግዛት አንድነት ማስጠበቅ ላይ ትኩረት ከመስጠቱም በላይ፤ የአገራቱን የግዛት አንድነት የሚፈታተን አደጋ ሲከሰት አብረው እንደሚቆሙ ያረጋግጣል። ፀንቶ የዘለቀው የኬንያና ኢትዮጵያ የፀጥታ ትብብር ለቀጣናው መረጋጋት ጉልህ አስተዋጽኦ አድርጓል።

በኢትዮጵያና ኬንያ መካከል ያለው የፀጥታ ትብብር የመሐመድ ዚያድ ባሬ መንግሥት በጥር 1983 መውደቅን ተከተሎ በሶማሊያ በተከሰተው መንግሥት አልባነትና አለመረጋጋት ምክንያት ተጠናክሮ ቀጥሏል። በአሁኑ ወቅት ሁለቱ አገሮች የሶማሊያ መንግሥትን በፀጥታው ዘርፍ ለማጠናከር በተሰማራው የአፍሪካ ሠላም አስከባሪ ጦር ተሳታፊ ከመሆናቸውም በተጨማሪ በተለያዩ ጊዜያት ወታደራዊ ኦፔሬሽኖችን ከአፍሪካ ሕብረት ማዕቀፍ ውጭ በሶማሊያ ውስጥ ያካሂዳሉ። በሶማሊያ የሚንቀሳቀሰው አልሸባብ የተባለው የሽብር ቡድን ለሁለቱም አገሮች የጋራ የደህንነት ሥጋት ስለሆነ አገራቱ በፀጥታው ዘርፍ ያላቸው ግንኙነት ጠንክሮ እንደሚቀጥል መረዳት ይቻላል።

ምንም እንኳን ኢትዮጵያና ኬንያ ጠንካራ የፀጥታና የፖለቲካ ግንኙነት ቢኖራቸውም የኢኮኖሚና የንግድ ግንኙነታቸው ግን ደካማ ሆኖ ቆይቷል። ቀጣናዊ የኢኮኖሚ ትብብርን በተመለከት ኬንያ ትኩረት የምታደርገው ቡሩንዲን፣ ኬንያን፣ ሩዋንዳን፣ ታንዛኒንያን፣ ደቡብ ሱዳንንና ዑጋንዳን በሚያቅፈው የምሥራቅ አፍሪካ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ነው። ያም

ሆኖ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በኢትዮጵያና ኬንያ መካከል ያለውን የኢኮኖሚ ግንኙነት ለማሻሻል ገንቢ እርምጃዎች ተወስደዋል። ከነዚህም መካካል ኢትዮጵያ ለኬንያ የኤሌክትሪክ ኃይል ማቅረብ መጀመሯ ሊጠቀስ ይገባል።

በተጨማሪም የሁለቱን አገሮች የኢኮኖሚ ትብብር ለማጠናከር ይረዳ ዘንድ አዲስ አበባን ከናይሮቢ የሚያገናኘው አውራ መንገድ ከመሻሻሉም በላይ የኬንያ መንግሥት ‹‹የላሙ-ሊፕሴት›› የተባለውን ፕሮጀክት ነድፎ ወደ ሥራ ገብቷል። ይህ 30 ቢሊዮን ዶላር የሚፈጅ ግዙፍ ፕሮጀክት ሲሆን የላፕሴት ኮሪደር በመባል ይታወቃል። ዋና ዓላማውም በኢትዮጵያ፣ በኬንያ እና በደቡብ ሱዳን መካከል የትራንስፖርት ትስስር መፍጠር ነው። በተጨማሪም ፕሮጀክቱ የምስራቅ አፍሪካን የባህር ዳርቻን (በሰሜን ኬንያ ከምትገኘውን የላሙ ወደብ ተነስቶ) ከምዕራብ አፍሪቃ (ካሜሩን ከምትገኘው የዱዋላ ወደብ) ጋር ለማገናኘት አቅዷል። ይህ መርሀ-ግብር የወደቦች፣ የነዳጅ ዘይት ማስተላለፊያ ቧንቧ መስመሮች፣ አዳዲስ መንገዶች፣ አውሮፕላን ማረፊያዎች፣ ከተሞች እና የባቡር ሃዲዶችን ግንባታን ያካትታል። በዕቅዱ መሠረት ናይሮቢን፣ ጁባንና አዲስ አበባን የሚያስተሳስሩ የባቡር መስመሮች ይዘረጋሉ። የኢትዮጵያ መንግሥት ለፕሮጀክቱ ድጋፉን ሰጥቷል። ይሁን እንጂ ፕሮጀክቱን ለመተግበር ግዙፍ የፋይናስ አቅምና የቀጣናው አገሮችን የጠነከረ ትብብርን ስለሚጠይቅ አፈጻጸሙ በርካታ ተግዳሮቶች ሊገጥሙት እንደሚችሉ ይገመታል። በቀጣናው አገራት ያለው የፖለቲካ አለመረጋጋትም በዚህና በሌሎች ተመሳሳይ የትብብር ዕቅዶች ላይ ጎጂ ተፅዕኖ ያሳድራል።

ከፖለቲካና ፀጥታ ትብብር ባሻገር የኢትዮጵያና ኬንያን ግንኙነት ለማጠናከር በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን የኢኮኖሚ ትብብር ማጠናከር ተገቢ ነው። በኢትዮጵያ በመካሄድ ላይ ያለው የፖለቲካና ኢኮኖሚ ማሻሻያ የሁለቱን አገሮች ግንኙነት ለማጠናከር ሊረዳ ይችላል። በተቃራኒው የፖለቲካ ለውጡን ተከትሎ ያለው አለመረጋጋትና በፖለቲካ ኃይሎች መካከል ያለው የሥልጣን ሽኩቻ የሁለቱን አገሮች ግንኙነት ሊያዳክም እንደሚችልም መረዳት ተገቢ ነው።

## 3.3 ሱዳን

ከጥንታዊዎቹ አክሱም እና ማሮዌ መንግሥታት ጀምሮ በኢትዮጵያ እና በሱዳን መካከል ረዥም ታሪካዊ ግንኙነት ነበር። ኢትዮጵያ እና ሱዳን ከ1600 ኪሎ ሜትር በላይ የጋራ ድንበር ሲኖራቸው በሁለቱ አገራት ሕዝቦች መካከል ጠንካራ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት አለ። ብዙ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵያውያን በሱዳን ውስጥ ሲኖሩ ኢትዮጵያም ለበርካታ ሱዳናውያን መኖሪያ ናት። በርከት ያለ ቁጥር ያላቸው የሁለቱ አገራት ሕዝቦች

በስደት በሁለቱ አገራት ውስጥ ተጠልለው ከመኖራቸው በተጨማሪም፤ በአስር ሺ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያን በየዓመቱ ሱዳንን በማቋረጥ መደበኛ ባልሆነ መንገድ ወደ አውሮፓ ይፈልሳሉ።

የኢትዮጵያ እና ሱዳን ግንኙነት ለዘመናት በትብብርና በግጭት መካከል የሚዋልል ሆኖ ቀጥሏል። የነዚህ ሁለት የጎረቤት አገሮች ግንኙነት በየአገራቱ ውስጥ በየጊዜው በሚነሱ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች እና ከውጭ ከሚመጡ ጫናዎች ጋር የተቆራኘ ነው። ሁለቱ አገራት ባላቸው ስልታዊ ጠቀሜታ ምክንያት ግንኙነታቸው ለኃያላን አገሮች፣ ለመካከለኛው ምሥራቅ አገሮችና ለግብፅ ጣልቃ ገብነት ተጋላጭ ሆኖ ቆይቷል።

የሁለቱ አገራት ግንኙነት ከደርግ መንግሥት ውድቀት በኋላ እየተሻሻለ መጥቷል። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ሁለቱ አገሮች የተሻለ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የፀጥታ ትብብር ማድረግ ጀምረዋል። ኢትዮጵያ በሱዳን ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች የተነሱ ግጭቶችን ለማብረድ በተቋቋሙ የአፍሪካና የተባበሩት መንግሥታት የሠላም ማስከበር ተልዕኮዎች ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ከመሆኗም በላይ የጄኔራል ዑስማን አልበሽር መንግሥት በሕዝባዊ አመፅ በ2011 ከወደቀ በኋላ ወታደሩን ጨምሮ ሌሎች ኃይሎችን ያካተተ የሽግግር መንግሥት እንዲመሠረት ገንቢ የማደራደር ስራ ሰርታለች። ኢኮኖሚን በተመለከት ሁለቱ አገሮች በቅርብ ዓመታት ውስጥ በኢነርጂ ዘርፍ ጥሩ ትብብር ማድረግ ጀምረዋል። ኢትዮጵያ ለሱዳን የኤሌክትሪክ ኃይል ስታቀርብ፤ ሱዳን ደግሞ ለኢትዮጵያ የነዳጅ ዘይት እያቀረበች ነው። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ሁለቱን አገሮች የሚያስተሳስሩ የመሠረተ-ልማት አውታሮችም ተገንብተዋል። ሆኖም በሁለቱ አገራት መካከል ያለው ግንኙነት በጠንካራ መሠረት ላይ የተመሠረተ ነው ለማለት አያስደፍርም።

በኢትዮጵያና በሱዳን ግንኙነት ላይ ጉልህ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ዋና ዋና ምክንያቶች ይገኛሉ። የመጀመሪያውና በሁለቱ አገሮች ግንኙነት ላይ ከፍ ያለ ተፅዕኖ የሚያሳድረው የዓባይ (ናይል) ወንዝ ጉዳይ ነው። እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ለናይል ወንዝ ከ85 በመቶ በላይ ውኃ የምታበረክት ቢሆንም እስካሁን ድረስ የወንዙ ተጠቃሚ አልነበረችም። ግብፅና ሱዳን በ1952 ባደረጉት ስምምነት ውኃውን ለሁለት በመካፈል ለመጠቀም ከመስማማታቸውም በተጨማሪ የሁለቱም አገራት ፍላጎት ኢትዮጵያ ከወንዙ ተጠቃሚ እንዳትሆን ማድረግ ነው። በኢትዮጵያ በኩል የ1952ቱ የሱዳንና ግብፅ ስምምነት ተቀባይነት የለውም ብላ ገና ስምምነቱ ሲፈረም ከማስታወቋ በላይ በውኃው የመጠቀም ሙሉ መብት እንዳላት በተደጋጋሚ ትገልፃለች።

በመጋቢት 2003 ኢትዮጵያ የሕዳሴን ግድብ ግንባታ ከመጀመረች በኋላ በዓባይ ወንዝ ላይ የኢትዮጵያ ተጠቃሚነትን በተመለከት ሱዳን የነበራት አቋም ለውጥ አሳይቷል። ኢትዮጵያ

የግድቡን ግንባታ ስተጀምር ሱዳንና ግብፅ በጋራ የግድቡን ግንባታ ተቃውመው ነበር፡፡ እያደር ግን የሱዳን መንግሥት የግድቡ መገንባት ለሱዳን በርካታ ጥቅሞች እንዳሉት በመረዳቱ በግድቡ መገንባት ላይ ያለውን ተቃውሞ አለሳልሷል፡፡ ግድቡ ለሱዳን ሊሰጥ ከሚችለው ጥቅም መካከል በየዓመቱ በኢትዮጵያ የክረምት ወቅት በሱዳን የሚያጋጥመውን የጎርፍ መጥለቅለቅ መቀነስ ነው፡፡ ይህ የሱዳን የአቋም ለውጥ ግብፅ ኢትዮጵያ በወንዙ እንዳትጠቀም የምታደርሰውን ጫና ለመቀነስ የበኩሉን ድርሻ አበርክቷል፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው የሱዳን አቋም በውስጥና በውጭ ተፅዕኖዎች ምክንያት ተለዋዋጭ ስለሆነ፤ በዓባይ ወንዝ ጉዳይ ላይ የሱዳን አቋምን ተደጋግሞ ሊለዋወጥ እንደሚችል መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡

ሁለተኛው ምክንያት የሁለቱ አገሮች ድንበሮች በተገቢው መንገድ ባለመካለላቸው ምክንያት በየጊዜው በድንበር አካባቢ በሚገኙ ማህበረሰቦች መካከል የሚነሱት ግጭቶች ናቸው፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ ግጭቶች ወደለየለት ጦርነት ባያመሩም በአገራቱ መካከል ያለው ግንኙነት እንዳይጠናከር እንቅፋት መሆናቸው አልቀረም፡፡

በሦስተኛነት የሚጠቀሰው ምክንያት የሁለቱ አገራት አንደኛው በሌላኛው አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባትና ለተቃዋሚ ድርጅቶች ድጋፍ መስጠት ነው፡፡ ሁለቱም አገራት ይህን ጎጂ ተግባር እስከ 1983 በሰፊው ፈጽመውታል፡፡ ሱዳን የኢትዮጵያን መንግሥት ይቃወሙ ለነበሩ የኤርትራና ልዩ ልዩ የኢትዮጵያ አማፂ ቡድኖች ድጋፍ ስትሰጥ፤ ኢትዮጵያ በበኩሏ ለደቡብ ሱዳን አማፂያን ድጋፍ ትሰጥ ነበር፡፡ ይህ ተግባር የሁለቱን አገሮች ግንኙነት በእጅጉ አዳክሞት ቆይቷል፡፡

በመጨረሻም በአሁኑ ወቅት በሁለቱ አገሮች በመካሄድ ላይ ያለው የፖለቲካ ለውጥና ሽግግር በአገራቱ ግንኙነት ላይ አንድምታ እንደሚኖረው መረዳት ተገቢ ነው፡፡ በኢትዮጵያ በኩል በአገሪቱ ያለው የፖለቲካ አለመረጋጋትና በፖለቲካ ኃይሎች መካከል የሚካሄደው ሽኩቻ አገሪቱ ከጎረቤት አገሮች ጋር ባላት ግንኙነት በተለይም የዓባይ ወንዝን ፍትሀዊ በሆነ መልኩ ለመጠቀም በሚደረገው የዲፕሎማሲ ትግል (ድርድር) ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚኖረው ይገመታል፡፡

## 3.4 ሶማሊያ

ከሁሉም ጎረቤቶቿ በበለጠ ኢትዮጵያ ከሶማሊያ ጋር ያላት ግንኙነት በግጭት የተፈተነና የተወሳሰበ ነው፡፡ የሶማሊያ መሪዎች አገሪቷ በሰኔ 1952 ከቅኝ አገዛዝ ነፃ ከወጣች በኋላ የተከተሉት ‹‹ታላቋን ሶማሊያ›› የመመሥረት ትልም የኢትዮጵያንና ሶማሊያን የሁለትዮሽ ግንኙነት ከማበላሸቱ በላይ በቀጣናው የፖለቲካ አለመረጋጋት እንዲከሰት አድርጓል፡፡

የሶማሊያ መንግሥት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘውንና በስፋት የሶማሌ ማህበረሰብ የሚኖርበትን የአገሪቷን ክፍል (የአሁኑን የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልልን) ኢትዮጵያ በቅኝ የያዘችው የሶማሊያ አካል ስለሆነ ወደ ሶማሊያ ሪፑብሊክ መካተት አለበት ብሎ የወሰደው አቋም የሁለቱን አገሮች ግንኙነት ከመሠረቱ ከትብብር ይልቅ በጥርጣሬና በግጭት የተሞላ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ከሶማሊያ ነፃ መውጣት በኋላ በሁለቱ አገራት መካከል በ1956፣ እና በ1969-70 ወታደራዊ ግጭቶች (ጦርነቶች) ተካሂደዋል፡፡ ከሁሉም የከፋው ከ1969-70 የተደረገውና የኦጋዴን ጦርነት ተብሎ የሚታወቀው ሲሆን ይህ ጦርነት በሁለቱም አገራት ላይ ከፍ ያለ ጉዳት አስከትሏል፡፡ እንዲያውም በዚህ ጦርነት የመሐመድ ዚያድ ባሬ መንግሥት መሸነፍና ጦርነቱ ያስከተለው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ቀውስ እንዲሁም ተከተሎም የተከሰተው የርስ በርስ ግጭት ለሶማሊያ መንግሥት መዳከምና በመጨረሻም በ1983 መውደቅ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

በድህረ 1983 ዓመታት ሶማሊያ በርስ በርስ ግጭት ከመዳከሟም በላይ በአገሪቱ ጠንካራና ብቃት ያለው ማዕከላዊ መንግሥት መመስረት አዳጋች ሆኖ ቀጥሏል፡፡ በተጨማሪም ቀድሞ የእንግሊዝ ቅኝ የነበረው የሶማሊያ ሰሜናዊ ክፍል ነፃነቱን በማወጅ የሶማሊላንድ ሪፑብሊክን መስርቷል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የሶማሊላንድ መንግሥት ዓለም አቀፍ ዕውቅና አላገኘም፡፡ የሶማሊያ ማዕከላዊ መንግሥት መዳከምን ተከተሎ ፑንትላንድን የመሳሰሉ አካባቢያዊ መንግሥታትም ተመስርተዋል፡፡ የደቡብ ሶማሊያ ማዕከላዊ ክፍል (ሞቃዲሾን ጨምሮ) እስከ አሁን መረጋጋት እንደራቀው ነው፡፡ በደቡብ ማዕከላዊ ክፍል አልሸባብ የተባለው የሽብር ቡድን በሰፊው ከመንቀሳቀሱ ባሻገር ዛሬም ብዙውን ገጠራማ አካባቢ በቁጥጥሩ ስር እንዳዋለ ይገኛል፡፡

የሶማሊያ ማዕከላዊ መንግሥት በወደቀበት ዘመን ከላይ እንደተቀሰው በኢትዮጵያም ወታደራዊው የደርግ መንግሥት በኢሕአዴግ በግንቦት 1983 ተተክቷል፡፡ ከ1983 ወዲህ ያለው የኢትዮጵያና የሶማሊያ ግንኙነት በተወሰነ መልኩ መሻሻል አሳይቷል፡፡ ለምሣሌም በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ሶማሊያውያን በሠላም እጦት ከአገራቸው በመሰደድ በኢትዮጵያ ውስጥ መጠለል ችለዋል፡፡ ስደቱ አስከፊ ቢሆንም በኢትዮጵያውያንና በሶማሊያውያን መካካል የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት እንዲሻሻል አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥትም በዓለም አቀፉ የሶማሊያ የሠላም ግንባታ ጥረት ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅትም ለሶማሊያ ፌዴራል መንግሥት ድጋፍ ለመስጠት በተቋቋመው የአፍሪካ ሕብረት የሠላም ተልዕኮ ውስጥ ኢትዮጵያ ተሳታፊ ናት፡፡ አልፎ አልፎም ከአፍሪካ ሕብረት ተልዕኮ ማዕቀፍ ውጭ ኢትዮጵያ አልሸባብ ላይ እርምጃ ለመውሰድ በሶማሊያ ውስጥ ወታደራዊ እንቅስቃሴ ታደርጋለች፡፡

ይሁን እንጂ ባለፉት 27 ዓመታት ያለው የሁለቱ አገሮች ግንኙነት ከግጭትና አለመግባባት የጸዳ አይደለም፡፡ በተለይም የኢትዮጵያ መንግሥት በታህሣሥ 1999 ባይዶዋ ይገኝ የነበረውን የሶማሊያ የሽግግር ፌዴራል መንግሥትን ለመደገፍ በሚል ጣልቃ በመግባት የመንግሥትን ሥልጣን ለመቆጣጠር ተቃርበው በነበሩት የእስላማዊ ፍ/ቤት ኃይሎች ላይ የወሰደው ዕርምጃ አወዛጋቢ ነበር፡፡

በሁለቱ አገራት ግንኙነት ላይ ጉልህ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ የተለያዩ ምክንያቶች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ‹‹የታላቋ ሶማሊያ›› አጀንዳ ሲሆን፤ ምንም እንኳን በአሁኑ ወቅት የሶማሊያ መንግሥት ይህን አጀንዳ ባያነሳም፤ ስምምነት ያልተደረሰባቸው የድንበርና የግዛት ጥያቄዎች የሁለቱን አገራት ግንኙነት ለማሻሻል ሳንካ መፍጠራቸው አይቀርም፡፡ አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች የኢትዮጵያ መንግሥት ዛሬም ‹‹የታላቋ ሶማሊያ›› አጀንዳ ሥጋት ስላለበት ጠንካራ የሶማሊያ መንግሥት እንዲፈጠር ብዙም ፍላጎት የለውም የሚል አስተሳሰብ ያንፀባርቃሉ፡፡ እንዲህ ያለውን ጥርጣሬ መፍታት ካልተቻለ የሁለቱን አገራት ግንኙነት በጠንካራ መሠረት ላይ መገንባት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

ሁለተኛ፣ ኢትዮጵያና ሶማሊያ ረጅም ድንበርና የጋራ ማንነትና ቋንቋና የሚጋሩና በአብዛኛው አርብቶ አደር የሆኑ ልዩ ልዩ የሶማሌ ጎሳዎችን ይጋራሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ለሁለቱ አገራት ግንኙነት መጠናከር ወይም መደፍረስ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በበጎ ጎኑ በሁለቱ አገራት የሚገኙ የሶማሌ ማህበረሰቦች ለአገራቱ ግንኙነት መጠናከር ድልድይ ሆነው ሊያገለግሉ ሲችሉ፤ በሌላው በኩል በሁለቱ አገራት የሚገኙ ማህበረሰቦች የሚጋሯቸው የውኃና የግጦሽ ሀብቶች፤ የአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ድንበርን በማቋረጥ የሚያደርገው እንቅስቃሴ በተገቢው መንገድ ማስተዳደር ካልተቻለ ከትብብር ይልቅ የግጭት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

ሦስተኛ፣ በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባትና ለተቃዋሚ ድርጅቶች ድጋፍ መስጠት ሲሆን ሁለቱም አገራት ይህን ጎጂ ተግባር እስከ 1983 ድረስ በሰፊው ፈጽመውታል፡፡ ሶማሊያ የኢትዮጵያን መንግሥት ይቃወሙ ለነበሩ ልዩ ልዩ አማፂ ቡድኖች ድጋፍ ስትሰጥ፤ ኢትዮጵያ በበኩሏ የሶማሊያ መንግሥትን ይቃወሙ ለነበሩ ኃይሎች ድጋፍ ትሰጥ ነበር፡፡ ይህ በአፍሪካ ቀንድ የተለመደ ተግባር የሁለቱን አገሮች ግንኙነት በእጅጉ አዳክሞት ቆይቷል፡፡

አራተኛ፣ ከሶማሊያ የሚመነጭ የሽብር ሥጋት ሲሆን ከላይ እንደተጠቀሰው በሶማሊያ የመንግሥት አቋም መዳከም ምክንያት ከዓለም አቀፍ የሽብር ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ያላቸው ልዩ ልዩ የሽብር ቡድኖች በሶማሊያ ውስጥ ይንቀሳቀሱ ነበር፡፡ አል ኢትሀድ አል

ኢስላም ይባል የነበረው ቡድን በ1988 እና በ1989 ኢትዮጵያ ውስጥ ጥቃት አድርሶ ነበር። በአሁኑ ወቅት ደግሞ አልሸባብ የተባለው ቡድን ለኢትዮጵያና ለቀጣናው የሥጋት ምንጭ ከመሆኑም በላይ በሁለቱ አገራት ግንኙነት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል።

አምስተኛውና በሁለቱ አገራት መካከል ያለው ግንኙነት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድረው ኢትዮጵያ ከሶማሌላንድ ጋር ያላት ግንኙነት ነው። የደርግ መንግሥት የዚያድ ባሬን መንግሥት በመቃወም በሰሜን ሶማሊያ ይንቀሳቀሱ ለነበሩ ኃይሎችን ድጋፍ ይሰጣቸው የነበረ ሲሆን፤ የኢሕአዴግ መንግሥት በበኩሉ ከሶማሌላንድ መንግሥት ጋር ጥብቅ የኢኮኖሚና የፀጥታ ትብብር መስርቷል። በተጨማሪም ኢትዮጵያ በቅርቡ የበርበራ ወደብን ለማሻሻል በተቋቋመው ኩባንያ ውስጥ የ19 በመቶ ድርሻ ገዝታለች። የሶማሊያ መንግሥትና ፖለቲከኞች ይህን የኢትዮጵያ እርምጃ በሶማሊያ የውስጥ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ እንደመግባት በመቁጠር አውግዘዋል። ከኢትዮ-ኤርትራ ግንኙነት ተሀድሶ በኋላ፤ በኢትዮጵያ፣ ኤርትራና ሶማሊያ መካከል የኢኮኖሚና የፀጥታ ትብብር ለማጠናከር ስምምነቶች ተደርገዋል። ኢትዮጵያን እንደ ዋነኛ አጋሯ የምታየው የሶማሌላንድ ሪፑብሊክ እነዚህን ሁኔታዎች በትኩረት ትከታተላለች። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ የውጭ ፖሊሲ አውጪዎች በሶማሊያና በሶማሌላንድ መካከል ያሉትን ተጻራሪ ፍላጎቶች የሚያስተናግድና የአገሪቱን ዘላቂ ጥቅም የሚያስከብር ፖሊሲ መንደፍ ይገባቸዋል።

ለማጠቃለል በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በመካሄድ ላይ ያለው የፖለቲካ ለውጥና ሽግግር በሁለቱ አገሮች ግንኙነት ላይ አንድምታ እንደሚኖረው መረዳት ተገቢ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የፖለቲካ አለመረጋጋትና በፖለቲካ ኃይሎች መካከል የሚደረግ ሽኩቻ ኢትዮጵያ ከሶማሊያ ጋር ባላት ግንኙነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚኖረው ማጤንም ይገባል።

## 3.5 ጅቡቲ

ኢትዮጵያ እና ጅቡቲ ለዘመናት የዘለቀ መልካም ግንኙነት አላቸው። በሁለቱ አገሮች መካከል ያለው ተደጋጋፊ የኢኮኖሚ ግንኙነት ለሁለቱ አገራት ወዳጅነት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርጓል። ከዚህም በተጨማሪ ጅቡቲም ‹‹የታላቋ ሶማሊያ›› አጀንዳ ሥጋት ስላለባት ኢትዮጵያና ሶማሊያ በ1969-70 ጦርነት ላይ በነበሩበት ወቅት ድጋፏን ለኢትዮጵያ ነበር የሰጠችው። በሁለቱ አገሮች ግንኙነት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮችን በአጭሩ እንደሚከተለው ማየት ይቻላል።

በመጀመሪያ ጅቡቲ በቆዳ ስፋትም ሆነ በሕዝብ ብዛት አነስተኛ ብትሆንም በጣም ጠቀሜታ ያለው ጂኦግራፊያዊ አቀማመጧ ተፅዕኖ ፈጣሪ እንድትሆን አድርጓታል። አገሪቷ ባበል

መንደብ የተባለውን የሕንድ ውቅያኖስና ቀይ ባሕርን በሚያገናኘው መስመር ላይ መገኘቷ ከፍ ያለ ስትራቴጂክ ቀሜታ እንዲኖራት አስችሏታል። እንደሚታወቀው ይህ መስመር የስዊዝ ቦይን በማቋረጥ በአውሮፓና በኤስያ መካከል የሚደረገውን የንግድ ልውውጥ ያስተናግዳል። አገሪቱ ባላት ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ምክንያት ፈርንሣይ፣ አሜሪካ፣ ጣልያን፣ ጃፓንና ቻይናን ጨምሮ ብዙ አገራት በአገሪቷ ወታደራዊ የጦር ሠፈር መስርተዋል:: የጦር ሠፈሮችን በማከራየት ጅቡቲ በዓመት ከ300 ሚሊዮን በላይ የአሜሪካ ዶላር ታገኛለች። አገሪቱ የጦር ሠፈር እንዲያቋቁሙ የፈቀደችላቸው አንዳንዶቹ አገሮች ተጻራሪ ስለሆኑ አንዳንድ ፀሀፊዎች ሦስተኛው የዓለም ጦርነት የሚጀመረው በጅቡቲ ሊሆን ይችላል ይላሉ።

ወደ ቀጣናውንና የኢትዮጵያን የፀጥታ ሁኔታ ስንመለከት በጅቡቲ የውጭ ኃይሎች የጦር ሠፈር መስፋፋት ጎጂ አንድምታ እንደሚኖረው መገንዘብ ይገባል:: በአንድ በኩል የወታደራዊ ጦር ሠፈሮች መበራከት ተቀናቃኝ የሆኑ ኃያል አገሮች ግጭታቸውን ወደ አካባቢው ሊያመጡ የሚችሉበትን ዕድል ስለሚፈጥር ለቀጣናው የስጋት ምንጭ ነው። በሌላ በኩል በቀጣናው የሠፈሩ የውጭ ኃይሎች በቀጣናው በሚነሱ ግጭቶች ውስጥ የሚሳተፉበት ዕድል ከተፈጠረ ግጭቶቹ ይበልጥ እንዲወሳሰቡ ያደርጋሉ።

ሁለተኛ፣ ጅቡቲ ለረጅም ዘመናት ለኢትዮጵያ የባህር በር በመሆን አገልግላለች። ይህ ሁኔታ የሁለቱን አገራት ግንኙነት ተደጋጋፊ ያደርገዋል። ኢትዮጵያ በየዓመቱ ከ1.5 እስከ 2 ቢሊዮን ዶላር በላይ ለወደብ አገልግሎት ለጅቡቲ ትከፍላለች (Ethiopian Observer, 2018)። በሌላ በኩል ኢትዮጵያ የግብርና ምርቶቿን ለጅቡቲ በማቅረብ ተጠቃሚ ናት። ከወደብ አገልግሎት በተጨማሪ ሁለቱ አገሮች በትራንስፖርትና ኢነርጂ መሠረት-ልማት ተሳስረዋል። እዚህ ላይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በቻይና ድጋፍ የተገነባውን ኢትዮጵያንና ጅቡቲን የሚያገናኘውን የባቡር መስመር መጥቀስ ተገቢ ነው። የወደብ አገልግሎትን በተመለከተ ጅቡቲ በኢትዮጵያ ላይ ያላት ተፅዕኖ ኢትዮጵያና ኤርትራ በ1990 ግጭት ውስጥ ሲገቡ በከፍተኛ ደረጃ አድጓል። ባለፉት 10 ዓመታት ኢትዮጵያ ለወደብ አገልግሎት በጅቡቲ ላይ ያላትን ጥገኝነት ለመቀነስና እያደገ የመጣውን የወጪና የገቢ ንግድ እንቅስቃሴ በተሻለ ሁኔታ ለማስተናገድ በማለት በሌሎች የቀጣናው ወደቦች የመጠቀም ዕድልን ለመፍጠር እንቅስቃሴ እያደረገች ነው። ከላይ እንደተጠቀሰው የበርበራ ወደብን ለማልማት ከተቋቋመው ኩባንያ የተወሰነ ድርሻ ገዝታለች። ከኤርትራ ጋር በቅርቡ የተደረገው ስምምነትም የአሰብ ወደብን የመጠቀም ዕድል ስለሚፈጥር አገሪቱ በጅቡቲ ላይ ያላትን ጥገኝነት ይቀንሳል ብሎ መገመት ይቻላል።

ሦስተኛ፣ ጅቡቲና ኢትዮጵያ የጋራ ማንነት ያላቸው ሕዝቦችን ይጋራሉ። ሁለቱ ዋና በጅቡቲ የሚገኙ የሶማሊ ኢሣ ጎሳና አፋሮች በኢትዮጵያ ውስጥም ይገኛሉ። እንዲያውም ኢትዮጵያና ጅቡቲ ውስጥ ለሚገኙት የኢሣ ማህበረሰብ አባላት የጋራ ባሕላዊ መሪ (ዑጋዝ) የሚኖሩት ኢትዮጵያ (ድሬዳዋ) ውስጥ ነው። ኢሣዎችና አፋሮች በጅቡቲና በኢትዮጵያ ውስጥ መገኘት በሁለቱ አገሮች መካከል ጥሩ ግንኙነት ለመመስረት እንደሚረዳ አያጠራጥርም። በሌላ በኩል ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ለረጅም ዘመናት በአፋርና ኢሣ ማህበረሰቦች መካከል በመሬትና በሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች ምክንያት ያለው ግጭት የሁለቱን አገሮች ግንኙነት ሊያበላሽ ስለሚችል ግጭቱን በዘላቂ መንገድ መፍታት ብዙ ጠቀሜታ አለው።

## 3.6 ደቡብ ሱዳን

በ2003 ከሱዳን በመገንጠል ነፃነቷን ያወጀችው ደቡብ ሱዳን ከኢትዮጵያ ጋር የሚያስተሳስሯት በርካታ ጉዳዮች አሉ። በመጀመሪያ ሁለቱ አገሮች ከ880 ኪሎ ሜትሮች በላይ ርዝመት ያለው ድንበር ይጋራሉ። በተጨማሪም አገራቱ ተመሳሳይ ቋንቋ የሚናገሩ ማህበረሰቦችን ከመጋራታቸውም በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ በ10 ሺዎች የሚቆጠሩ የደቡብ ሱዳን ስደተኞች ይኖራሉ።

ረጅም ዘመን ከተደረገ ጦርነት በኋላ ነፃ የወጣችው ደቡብ ሱዳን ድህረ-ግጭት አገር ግንባታን በተመለከተ ከፍ ያሉ ተግዳሮቶች ገጥመዋታል። ከጎረቤት ሱዳን ጋር አሁንም ድረስ ያልተቋጩ የድንበር (የግዛት) ጥያቄዎች አሉ። ሱዳንና ደቡብ ሱዳን አብዬ በተባለው አካባቢ ዕጣ ፈንታ ላይ መስማማት ባለመቻላቸው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሙሉ በሙሉ በሚባል መልኩ በኢትዮጵያ ወታደሮች የተዋቀረውን የሠላም አስከባሪ ጦር በ2003 ወደ አካባቢው ልኳል። በተጨማሪም የደቡብ ሱዳንን የነፃነት ሽግግር እንዲረዳ በሚል በ2003 የተቋቋመው የተባበሩት መንግሥታት የደቡብ ሱዳን ተልዕኮ አሁንም በሥራ ላይ ነው። የተልዕኮው ሚና በ2005 በአገሪቷ መሪዎች መካከል የተፈጠረውን የሥልጣን ሽኩቻ ተከትሎ በተከሰተው የርስ በርስ ጦርነት ምክንያት እንደገና ተጠናክሯል።

የኢትዮጵያና የደቡብ ሱዳን ግንኙነት ከግጭት ይልቅ ወደ ትብብር የሚያጋድል ሲሆን፤ በሁለቱ አገራት ግንኙነት ላይ ተፅዕኖ ሊያደርሱ የሚችሉ ዋና ዋና ጉዳዮች እንደሚከተለው በአጭሩ ሊዳሰሱ ይችላሉ።

በመጀመሪያ፣ ኢትዮጵያ ለደቡብ ሱዳን የነፃነት ትግል ሁለንተናዊ ድጋፍ በመስጠቷ በሁለቱ አገሮች መካከል የአጋርነትና የወዳጅነት ስሜት አለ። ምንጊዜም ቢሆን አገራት ከታሪክ ይልቅ ዘላቂ ጥቅማቸውን ተመልክተው የውጭ ፖሊሲያቸውን ስለሚያወጡ፤ ኢትዮጵያ

ለደቡብ ሱዳን የሰጠችው ድጋፍ ሁልጊዜም ከዚያች አገር ድጋፍ ያመጣልኛል ብላ መጠብቅ የለባትም፡፡

ሁለት፣ የሁለቱ አገራት ድንበር ባለመካለሉ የሥጋት ምንጭ ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም ወሰን ተሻጋሪ ሕገ-ወጥ የመሣሪያ ዝውውርና ድንበር ተሻገረው ጥቃት የሚያደርሱ ማህበረሰቦች በሁለቱ አገራት የድንበር አካባቢ መኖራቸው ለኢትዮጵያ የሥጋት ምንጭ ነው፡፡

ሦስት፣ ሁለቱ አገራት ተመሳሳይ ቋንቋ የሚናገሩ ሕዝቦችን ስለሚጋሩና ሕዝቦቹም በተለየም የኑዌር ማህበረሰብ አባላት የአገራቱ ድንበሮቹ ሳያግዷቸው ከአንዱ አገር ወደ ሌላው እንቅስቃሴ ስለሚያደርጉ እንዲህ አይነቱ እንቅስቃሴ ከደቡብ ሱዳን ጋር ድንበር የሚጋራውን የጋምቤላን ክልል ፀጥታ እንዳያውክ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ሥጋት አለ፡፡

አራት፣ ሌላው ለኢትዮጵያ የሥጋት ምንጭ ደቡብ ሱዳን በኢትዮጵያ፣ ሱዳንና ግብፅ መካከል የናይል ወንዝን በተመለከተ በሚደረገው ትግል ውስጥ የሚኖራት ሚና ነው፡፡ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አውጭዎች ደቡብ ሱዳን በወንዙ ላይ ያላት ዘላቂ ጥቅም የሚጠበቀው ሁሉንም የተፋሰሱ አገሮች የሚያካትት የትብብር ማዕቀፍ ተቀባይነት ሲኖረው በመሆኑ ደቡብ ሱዳን ለማዕቀፉ ድጋፍ እንደተሰጥ አበክረው መስራት ይገባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የደቡብ ሱዳንን ግዛት በመጠቀም ግብፅ በሕዳሴው ግድብ ላይ አደጋ እንዳታደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

## 3.7 ግብፅና የአረብ ባሕረ-ሠላጤ አገራት

ግብፅ እና ኢትዮጵያ የጋራ ድንበር ባይጋሩም በታሪክ የተሳሰሩ አገራት ናቸው፡፡ የሁለቱ አገራት ግንኙነት ከግጭቶች፣ ስትራቴጂካዊ እና ፖለቲካዊ እሰጥ-አገባዎች በተጨማሪ የጋራ ዕሴቶችን ያካትታል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ተከታይ ያለው የኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስትያን ከግብፅ ኮፕቲክ ቤተ-ክርስትያን ጋር ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ ግንኙነት አለው፡፡ እስከ 1951 ድረስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስትያን ፓትርያርክ ይሾም የነበረው በግብፅ የኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ነበር (Erlich, 2015)፡፡

በኢትዮጵያ እና በግብፅ ግንኙነት ላይ ሁልጊዜም ጉልህ ቦታ ያለው የዓባይ (ናይል) ወንዝ ነው፡፡ የታሪክ ተመራማሪው ኤርሊክ ሃጋይ እንደሚያወሳው ግብፆች ከጥንት ጀምሮ የህይወታቸው መሠረት የሆነው የናይል ወንዝ ምንጭ ኢትዮጵያ መሆኗን ከመረዳታቸውም በላይ፤ ኢትዮጵያውያን የወንዙን ፍሰት ሊያስቆሙ ይችላሉ የሚል ፍራቻ ነበራቸው፡፡

በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ሩብ ዓመታት የዘመናዊ ግብፅ ብሔረተኝነት ሲጠናከር በግብፅ መሪዎች ዘንድ የናይል ሸለቆን ከግብፅ ጋር ለማዋሀድ አቅደው መንቀሳቀስ ጀመሩ። ይህ ትልም የከሸፈው የግብፅ ሠራዊት በ1867 እና 1868 በጉንደት እና በጉራዕ ጦርነቶች በኢትዮጵያ ሲሸነፍ ነው። ይህ ሽንፈት ግብፅ ሱዳንን ለመቆጣጠር የነበራትን ዕድል ከማመናመኑም በላይ ራሷም በመዳከሟ በእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ስር እንድትገባ አስተዋጽኦ አደርጓል (Erlich, 2015)።

ኢትዮጵያን በመቆጣጠር የናይል ወንዝን ከምንጩ ለመቆጣጠር የነበራት ትልም የከሸፈባት ግብፅ ከሀያኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ ወንዙን በበላይነት ለመጠቀም ልዩ ልዩ ስልቶችን በመቀየስ ተንቀሳቅሳለች። በዚህም በመጀመሪያ የናይል ወንዝን የላይኛው ተፋሰስ አገራትን ሳታማክር በ1962 የተጠናቀቀውን የአስዋን ግድብን ገንብታለች። በ1964 አሁንም የላይኞቹን ተፋሰስ አገራት ሳታሳትፍ ውኃውን ከሱዳን ጋር ለመካፈል ስምምነት አድርጋለች። በተጨማሪም ግብፅ በዚህ ዘመን ተቀባይነት የሌላቸው የቅኝ ግዛት ውሎችንና ‹‹ታሪካዊ መብት›› የሚለውን አስተሳሰብ በማንጸባረቅ የኢትዮጵያንና የሌሎቹን የላይኛው ተፋሰስ አገሮች በወንዙ የመጠቀም መብት ለመገደብ ተግታ ትሠራለች።

ከላይ ከተጠቀሱት ሥልቶች በተጨማሪ ግብፅ የምትከተለው ሌላው ሥልት ኢትዮጵያን ማዳከም ነው። በግብፅ የውጭ ፖሊሲ አውጭዎች እምነት በናይል ወንዝ ላይ የግብፅን የበላይነት ለማረጋገጥ ኢትዮጵያን ማዳከም ጠቃሚ ሥልት ነው። በዚህም መሠረት ግብፅ በአፍሪካ ቀንድና በኢትዮጵያ ውስጥ በተከሰቱ ግጭቶች ውስጥ ሁልጊዜም ከኢትዮጵያ በተፃራሪ ከመቆሟም በላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚነሱ ፀረ-መንግሥት እንቅስቃሴዎች ድጋፍ ትሰጣለች። ለምሣሌም ያህል ግብፅ ለኤርትራ የነፃነት እንቅስቃሴዎች ከምስረታቸው ጀምሮ ሰፋ ያለ ድጋፍ ስተሰጥ እንደነበር ይታወቃል።

የናይል ውኃን በተመለከተ ለጋራ ተጠቃሚነትና ለትብብር ቦታ የማይሰጡት የግብፅ መሪዎች አብዛኛዎቹ የተፋሰሱ አገራት የደገፉትን ‹‹የናይል የትብብር ማዕቀፍ›› ተቃውመዋል። ምንጊዜም ቢሆን በተፈጥሮ ሀብቷ የመጠቀም መብቷን አበክራ የምትገልጸው ኢትዮጵያ በመጋቢት 2003 የጀመረችው የታላቁ ሕዳሴን ግድብ የናይል ውኃን ፖለቲካ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚቀይር ግልፅ ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት ስለ ግድቡ ቴክኒካዊና የውኃ አሞላል ጉዳዮች ከታችኞቹ አገራት ማለትም ከግብፅና ከሱዳን ጋር ድርድር እያደረገ ቢሆንም፤ ድርድሩ እስከ አሁን ሊቋጭ አልቻለም። ግብፅ በቴክኒክ ጉዳዮች ላይ በሚደረጉ ሥምምነቶች አማካይነት በወንዙ ውኃ ላይ ያላትን የበላይነት ለማስጠበቅ ተግታ እየሰራች ነው። በሌላ አነጋገር የግብፅ ውትወታና ፍላጎት ቢቻል የግድቡ ግንባታ እንዲቋረጥ ማድረግ፤ ካልሆነም ደግሞ ኢትዮጵያ ያልተሳተፈችባቸውንና በዘላቂነት የርሷን ጥቅም የሚጎዱ የቅኝ

ግዛት ሥምምነቶችን እንደትቀበል ጫና ማሳደር ነው። ይህንን ዓላማዋን ለማሳካት ግብፅ በርካታ ስልቶችን ትከተላለች። የመጀመሪያው ስልት በመካከለኛው ምሥራቅ ያላትን የጂኦ-ፖለቲካ ተፅዕኖ ፈጣሪነቷን በመጠቀም አሜሪካንን የመሳሰሉ ኃያል አገሮችን ከጎኗ ማሰለፍ ነው። ሁለተኛው የአረቡ ዓለም ድጋፍን በመያዝ በኢትዮጵያ ላይ ተፅዕኖ ማድረግ ሲሆን ሌላው ግን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የግድቡ አሞላል የግብፅን መመሪያ የማይከተል ከሆነ ወታደራዊ እርምጃ እወስዳለሁ የሚል ዛቻ ነው።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት እንደታዘብነው ግብፅ በግድቡ ድርድር ላይ ያላት አቋም ከኢትዮጵያ የውስጥ ፖለቲካ ጋር የተሳሰረ ነው። ሠላሟ የተጠበቀና በውስጧ የተባበረች ኢትዮጵያ የተሻለ የድርድር ቁመና ሲኖራት፤ የተከፋፈለችና የውስጥ ሠላሟ የተዳከመ ኢትዮጵያ በዓባይ ውኃም ይሁን ሌሎች ጉዳዮች ላይ የሚኖራት የድርድር አቋም ደካማ ነው የሚሆነው። ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነው ግብፅ በዓባይ ግድብ ድርድር ላይ የኢትዮጵያን የውስጥ ሁኔታ እየመዘነች የምትከተለው ተለዋዋጭ የድርድር ስልት ነው። በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለውን የፖለቲካ ለውጥና ሽግግርን ተከትሎ የተከሰተው አለመረጋጋትና በፖለቲካ ኃይሎች መካከል የሚደረገው የሥልጣን ሽኩቻ ኢትዮጵያ ከግብፅ ጋር ባላት ግንኙነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚኖረውና በግድቡ ድርድር ላይም የአገሪቷን የመደራደር አቅም እንደሚቀንስ በማጤን በመንግሥት ውስጥም ይሁን ከመንግስት ውጭ ያሉ አካላት ይህንን ከግንዛቤ በማስገባት ተገቢውን እርምጃ ሊወስዱ ይገባል።

ኢትዮጵያ ከአረብ ባህረ-ሠላጤ አገሮች ጋር ጥንታዊ ግንኙነት አላት። በእስልምና ታሪክ እንደተመዘገበው በኃይማኖቱ የመጀመሪያ ዘመናት ከተቀናቃኞቻቸው ጥቃት የደረሰባቸው የነቢዩ መሐመድ ተከታዮች የመጀመሪያውን ሂጅራ (ስደት) ያደረጉት ወደ አቢሲኒያ (ኢትዮጵያ) ነበር። የአረብ ባሕረ-ሠላጤው ወደ ስምንት የሚጠጉ አገራትን ሲያካትት፤ ኢትዮጵያ የጎላ ግንኙነት ያላት ከሳውዲ አረቢያ፣ ከዩናይትድ አረብ ኤሜሬትስና ከኳታር ጋር ነው።

ከሁሉም የባሕረ-ሠላጤው አገራት በላይ ኢትዮጵያ ከሳውዲ አረቢያ ጋር ከፍ ያለ የባህል፣ የኃይማኖት እና የኢኮኖሚ ግንኙነት አላት። በየዓመቱ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ለሀይማኖታዊ ጉዞ ወደ ሳውዲ አረቢያ ከመጓዛቸው በላይ በአገሪቷ ውስጥ የእስልምና የተቀደሱ ቦታዎች ስለሚገኙ በብዙ ሚሊዮን በሚቆጠሩ ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ዘንድ ለሳውዲ አረቢያ ጥሩ አመለካከት አለ። ከ1980ዎቹ ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ ላለው የእስልምና ኃይማኖት መነቃቃት ከፍ ያለ የሳውዲ አረቢያ ድጋፍ እንዳለ አንዳንድ ፀሀፊዎች ያወሳሉ (Erlich, 2015)። በሳውዲ መንግሥት የሚደገፈው የዋሀቢይ እስልምና አስተምህሮት በኢትዮጵያ መስፋፋት በኢትዮጵያ መንግሥት እንደ ሥጋት

በመቆጠሩና መንግሥት የእስልምና አክራሪነትን እቆጣጠራለሁ በሚል የወሰዳቸው እርምጃዎች መንግሥትን ከሙስሊሙ ማህበረሰብ ጋር እንዳጋጨው የቅርብ ጌዜ ትዝታ ነው (Mohammed, 2016)። አሁንም ቢሆን ለኢትዮጵያ መንግሥት የኃይማኖት ነፃነትን አስከብሮ በሁሉም ኃይማኖቶች ውስጥ የሚንፀባረቀውን ጽንፈኝነት ለመከላከል የሚያስችል ፖሊሲ መዘርጋትና መተግበር ትልቅ ፈተና ነው።

ሳውዲ አረቢያ ከዕምነት ግንኙነት ባሻገር ከኢትዮጵያ ጋር ከፍ ያለ የኢኮኖሚ ግንኙነት አላት። በ2009 ኢትዮጵያ ከ150 ሚሊዮን ዶላር በላይ የሚገመቱ ምርቶችን ወደ ሳውዲ አራቢያ ስትልክ፣ በዚያው ዓመት ከሳውዲ አረቢያ ከ460 ሚሊዮን ዶላር በላይ የሚገመቱ ምርቶችን ወደ አገር ውስጥ አስገብታለች (Trading Economics, 2020)። የሳውዲ ኩባንያዎች ቀጥተኛ የውጭ መዋለ-ንዋይ በማፍሰስ በኢኮኖሚ ውስጥ እየተሳተፉ ነው። እንዲያውም 1980ዎቹ ሳውዲ ለኢትዮጵያ ከፍተኛዋ የውጭ ቀጥተኛ መዋለ-ንዋይ ምንጭ ነበረች። በተጨማሪም አገሪቷ ለኢትዮጵያ ብድርና ዕርዳታ ትሰጣለች።

ከንግድና ከፋይናንስ ትስስሮች በተጨማሪ በየዓመቱ በአስር ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በሕጋዊና ሕጋዊ ባልሆኑ መንገዶች ወደ ሳውዲ አረቢያ ለሥራ ይፈልሳሉ። በ2005 ሳውዲ አረቢያ ፍቃድ ሳይኖራቸው በአገሯ ውስጥ የሚኖሩ የውጭ ዜጎችን ስታባርር እንደታየው ከመቶ ሺህ በላይ ኢትዮጵያን በዚያች አገር ውስጥ በሥራ ላይ እንደተሰማሩ መገመት ይቻላል (Asnake and Zerihun, 2015)። እነዚህ የኢትዮጵያ ዜጎች አገር ቤት የሚገኙ ቤተሰቦቻቸውን ለመርዳት የሚልኩት ገንዘብ ለኢኮኖሚው ትልቅ ድጋፍ እንደሆነ ግልፅ ነው። ባለፉት ጥቂት ዓመታት እንደታየው ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ገንዘብና ዕቃ መጠን ኢትዮጵያ ዕቃዎች ወደ ውጭ በመላክ ከምታገኘው የውጭ ምንዛሬ በላይ ሆኗል (Asnake and Zerihun, 2018)።

ኢትዮጵያ ከተባበሩት የአረብ ኢሜሬቶች እና ከኳታር ጋር ያላት ግንኙነት ከሳውዲ አረቢያ ጋር ካላት ግንኙነት ጋር ተመሳሳይ ነው። ሁለቱም አገራት የቀጥታ የውጭ መዋለ-ንዋይ ምንጭ ከመሆናቸው በላይ አገራቱ ለኢትዮጵያ ብድርና የፋይናንስ ድጋፍ ያቀርባሉ። በተጨማሪም ኢትዮጵያውን ወጣቶች በሁለቱም አገሮች ውስጥ ሥራ ላይ ተሰማርተዋል።

ለማጠቃለል ኢትዮጵያ ከአረብ ባሕረ-ሠላጤው አገራት ጋር ያላት ግንኙነት መልካም ዕድሎችና ሥጋቶችን ያካተተ ነው። በአንድ በኩል በዘይት ሀብት እጅጉን የናጠጡት እነዚህ አገራት ለኢትዮጵያ በንግድ፣ በመዋለ-ንዋይና በሥራ ስምሪት መልካም ዕድል ሲፈጥሩ፤ በሌላ በኩል እነዚህ አገራት የሥጋትም ምንጭ ናቸው። የሥጋት ምንጮቹ የሚከተሉትን ያካትታሉ።

አንደኛ፣ የኃይማኖት ፅንፈኝነት ሲሆን ከላይ እንደተቀሰው ሳውዲ አረቢያ ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ ኃይሎች ጽንፈኛ አስተምህሮት ለሚከተሉ ቡድኖች ድጋፍ ስለሚሰጡ፤ ይህ መሠል እንቅስቃሴ የኃይማኖት ግጭት ሊያመጣ ስልሚችል የሥጋት ምንጭ ሆኖ መቀጠሉ ግልፅ ነው።

ሁለተኛ፣ በአረብ ገልፍ አገሮች መካከል ያለው ግጭትና የፖለቲካ ውጥረት ለኢትዮጵያ የሥጋት ምንጭ ነው። በአንድ በኩል የሱኒ ኃይማኖት የሚከተሉት የአረብ ባህረ-ሠላጤው አገራት በጋራ በመቆም የሺዓ እስልምናን ከምትከተለው ኢራን ጋር የሚያደርጉት ፍጥጫ ለየመን የርስ በርስ ግጭት መባባስ ምክንያት ከመሆኑም በላይ ለአፍሪካ ቀንድ የሥጋት ምንጭ ነው። በሌላ በኩል በሳውዲ አረቢያና በኳታር መካከል የተፈጠረው ቀውስ ለአፍሪካ ቀንድ የሥጋት ምንጭ ሆኗል። ሳውዲ አረቢያና አጋሮቿ የአፍሪካ ቀንድ አገሮች ኳታርን በማግለል ከእነርሱ ጋር አብረው እንዲቆሙ ባደረጉት ግፊት ምክንያት የተወሰኑ አገሮች ከሳውዲ አረቢያ እና አጋሮቿ ጎን ተሠልፈዋል። ይህ አይነቱ አድራጎት በባሕረ-ሠላጤው ያለውን ውጥረት ወደ አፍሪካ ቀንድ እንዳያመጣው ያሰጋል። ወደ ኢትዮጵያ ስንመለስ ከሁለቱም ግጭቶች ማለትም ከሳውዲ-ኢራን እና ከሳውዲ-ኳታር ፍጥጫዎች ራሷን በማግለል ከሁሉም አገሮች ጋር ወዳጃዊ ግንኙነቷን ቀጥላለች። ይህ ፖሊሲ የአገሪቷን ዘላቂ ጥቅም ለማስከበር ስለሚረዳ በዚሁ መቀጠሉ አስፈላጊ መሆኑን ማስመር ያስፈልጋል።

## 4 ማጠቃለያ

ኢትዮጵያን የመሳሰሉ ብዙ አገሮች የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ዓላማ በሁለት ቁልፍ ጉዳዮች ላይ የሚያጠንጥን ሲሆን ፤ እነርሱም የአገርን ነፃነት፣ ሉዓላዊነት እና የግዛት አንድነት ማስጠበቅ እና ለፖለቲካ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚ ልማት አስተዋጽኦ ማድረግ ናቸው። የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲም መታየት የሚገባው ከዚህ አንጻር ነው። ምንም እንኳን የመንግሥታት መለዋወጥ በውጭ ጉዳይ ፖሊሲ እና አፈፃጸሙ ላይ ለውጦች ቢያመጣም የውጭ ጉዳይ ፖሊሲዎችን በተመለከተ ከለውጥ ይልቅ የፖሊሲ መወራረስ ያመዝናል። የውጭ ጉዳይ ፖሊሲና ዲፕሎማሲ ኢትዮጵያ ለረዥም ዘመን ነፃነቷን ጠብቃ እንድትቆይ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። በዚህ ጽሁፍ እንደተመለከተው የኢትዮጵያ መሪዎች የተከተሉት አንዱን ኃያል አገር ተወዳጅቶ ሌላውን የመመከት የውጭ ፖሊሲ አቅጣጫ የአገሪቷን ነፃነት ለመጠበቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል።

የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲና አተገባበሩ በሶስት ደረጃ ሊታዩ በሚችሉ ምክንያቶች ተፅዕኖዎች ይደርስበታል። እነርሱም የአገር ውስጥ፣ የአካባቢ እና የዓለም አቀፍ ሁኔታዎች ናቸው። ከአገር ውስጥ ሁኔታዎች ባለፉት 50 ዓመታት እንደታየው የፖለቲካ ለውጥና

የሥልጣን ትግል በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ላይ ከፍተኛ ደረጃ ተፅዕኖ አድርሷል፡፡ በአንድ በኩል በፖለቲካ ለውጥ ምክንያት ተቋማትን እንደ አዲስ አፍርሶ መገንባት ልምድ በሆነባት ኢትዮጵያ የ1967ቱ እና የ1983ቱ የመንግሥት ለውጦች በውጭ ጉዳይ ተቋማት ላይ ከፍ ያለ ጉዳት ማድረሳቸው አይዘነጋም፡፡ በሌላ በኩል የፖለቲካ እና የዲሞክራሲ ባህል በኢትዮጵያ ውስጥ ባለመጠናከሩ ምክንያት በአገር ውስጥ ለሥልጣን የሚራኮቱ ኃይሎች ከኢትዮጵያ በተፃፃሪ ከቆሙ አገሮች ጋር አብረው ሲሰለፉ በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች ተስተውሏል፡፡ ይህ ተግባር የአገርን ዘላቂ ጥቅም ከመጉዳቱም በተጨማሪ አገሪቷ ከውጭ ኃይሎች ጋር ያላትን የመደራደር አቋም ያዳክማል፡፡

ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት የፖለቲካ ሽግግር ላይ ስትሆን፤ ሽግግሩ በአገሪቱ የውጭ ፖሊሲና ግንኙነት ላይ ተፅዕኖ እንደሚኖረው ዕሙን ነው፡፡ የፖለቲካ ሽግግሩ ሠላማዊና ዲሞክራሲያዊ ከሆነ የአገሪቱን ዓለም አቀፍ አቋም ከማጠናከሩም በተጨማሪ ለውጭ ግንኙነት መጠናከር የበለጠ ጥንካሬ ይሰጣል፡፡ በሌላ በኩል የፖለቲካ ሽግግሩ ግጭትና ያለመረጋጋትን የሚያስከትል ከሆነ የአገሪቱን ዓለም አቀፍ ቁመናን ከማዳከሙም ባሻገር የውጭ ኃይሎች በአገሪቷ ፖለቲካ ውስጥ ጣልቃ እንዲገቡ ዕድል ይፈጥራል፡፡ ለምሣሌ ያህል በኢትዮጵያ፣ በሱዳና በግብፅ መካከል በሕዳሴው ግድብ ላይ በመካሄድ ላይ ያለው የድርድር ሂደት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲና የመደራደር አቅም አገር ውስጥ ካለው የፖለቲካ ሁኔታ ጋር በእጅጉ እንደሚተሳሰር ያሳያል፡፡ በአገር ውስጥ በፖለቲካ ኃይሎች መካከል ያለው ክፍፍልና ሽኩቻ ሲጠናከር የተደራዳሪ አገሮቹ በተለይም የግብፅ አቋም የመክረር ዝንባሌ ይታይበታል፡፡ ይህ የሚያሳየው በፖለቲካ መሪዎች ዘንድ በብሔራዊ ጥቅሞች ላይ መግባባትን የመፍጠር አስፈላጊነት ነው፡፡

በዚህ ጽሁፍ ከቀረበው የኢትዮጵያና የጎረቤት አገሮቿ ግንኙነት መረዳት እንደሚቻለው ከኬንያና ከጅቡቲ በስተቀር ከሌሎች ጎረቤት አገራት ጋር ያሉት ግንኙነቶች በጠንካራ መሠረት ላይ የተመሠረቱ አይደሉም፡፡ ድንበሮች በአብዛኛው ስላልተካለሉ ከትብብር ይልቅ የግጭት ምክንያት ናቸው፡፡ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ (ሕዝብ ለሕዝብ) ግንኙነቶች ያን ያህል የተጠናከሩ አይደሉም፡፡ ለኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ መጠናከር እነዚህ ተግዳሮቶች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ሊፈቱ ይገባል፡፡ በሌላ በኩል፤ ላለፉት በርካታ አስረተ-ዓመታት ለአፍሪካ ቀንድ አለመረጋጋት ጉልህ ሚና የተጫወተው ‹‹የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው›› የሚለው ብሂል ፈጽሞ እስካልተወገደ ድረስ በቀጣናው መተማመንን ማምጣት ስለማይቻል፤ ይህን አመለካከት ለማስወገድ ኢትዮጵያ ተግታ መስራት ይኖርባታል፡፡ በቀጣናው መተማመን ከጎለበተና በአገራት ውስጥና መካከል ሠላም ማስፈን ከተቻለ ኢጋድን የመሳሰሉ ክፍለ-አሕጉራዊ ተቋማት ይጠናከራሉ፡፡

የአረብ ባሕረ-ሠላጤው አገሮች ለኢትዮጵያ ካላቸው የጂኦግራፊ ቅርበት አኳያ ለኢትዮጵያ ጠቃሚ የንግድ አጋር እና የቱሪስት ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ:: በተጨማሪም አገራቱ በኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ምንጭና ለበርካታ ወጣት ኢትዮጵያውያን የሥራ ዕድል ይፈጥራሉ:: ከእነዚህ አገራት ጋር መልካም ግንኙነትን ማዳበር አስፈላጊ ነው:: ነገር ግን እነዚህ አገሮች ባሕረ-ሠላጤው ባላቸው ግጭት ውስጥ ኢትዮጵያን ስበው እንዳያስገቡ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረጉ ይገባል::

በመጨረሻም፣ የምንገኝበት የዓለም አቀፍ ሥርዓት በርካታ ኃያላን አገሮችን ስለሚያቅፍ ኢትዮጵያን ለመሳሰሉ ታዳጊ አገሮች በጎ ዕድሎችን ይሰጣል:: ምንም እንኳን አሜሪካንን የመሳሰሉ ምዕራባውያን አገራት ከቻይና ጋር የቅርብ ወዳጅነት ያላቸውን የአፍሪካ አገራት ከቻይና ለመነጠል ጥረት ቢያደርጉም፤ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም የሚጠበቀው ከሁሉም ኃይሎች ጋር ሚዛናዊ ግንኙነት በማድረግ ስለሆነ እንዲህ አይነቱን ጫና የመቋቋም አስፈላጊነትን ላይ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል::

## ዋቢ መፃህፍት እና ጽሁፎች


Asnake Kefale and Zerihun Mohammed. 2015. *Ethiopian Labour Migration to the Gulf and South Africa*. FSS Monograph No. 10. Addis Ababa: Ethiopia.

Asnake Kefale and Zerihun Mohammed.2018. *Remittance and Household Socio-Economic Well-Being: The Case of Ethiopian Labour Migrants to the Republic of South Africa and the Middle East*. Addis Ababa: Forum for Social Studies (FSS)

Ben, Rawlence, Leslie Lefkow, and Georgette Gagnon. 2010. *Development without freedom: how aid underwrites repression in Ethiopia.* New York: Human Rights Watch.

Bull, Hedley. 1995. *Anarchical society: study of order in world politics.* Houndmills: Macmillan.

Central Statistical Agency (CSA) 2013a. *Population Projection of Ethiopia for All Regions At Wereda Level from 2014 – 2017*. Addis Ababa: CSA

Central Statistical Agency (CSA) 2013b. *Ethiopia Labour Force Survey 2013.* Addis Ababa: Central Statistical Agency.

Daniel, Don Nanjira, 2010. *African foreign policy and diplomacy: from antiquity to the 21st century*. Santa Barbara, CA: Praeger Security International. Pp. 132-133

Erlich, Ḥagai. 2015. *The cross and the river: Ethiopia, Egypt, and the Nile*. Boulder, Colorado : Lynne Rienner Publishers.

Ethiopian Observer, 2018. “Djibouti, Ethiopia strike port deal, Djibouti to partner in Ethiopian airlines, telecom” April 29, 2018. Available

[https://www.ethiopiaobserver.com/2018/04/29/djibouti-ethiopia-strike-port-deal-djibouti-to-partner-in-ethiopian-airlines-telecom]. Available June 14, 2020

Keersmaeker, Goedele De. 2017. Polarity, balance of power and international relations theory: post-cold war and the 19th century compared. Ghent: Palgrave Macmillan.

Marcus, Harold G. 1995. *The politics of empire: Ethiopia, Great Britain, and the United States, 1941-1974*. Lawrenceville, NJ: Red Sea Press.

Mesfin, Berouk. 2004. "A study of the decision-making process and the strategies of Ethiopia's foreign policy (1974-1991), with particular emphasis on Ethio-US relations". *Ethiopian Journal of the Social Sciences and Humanities*. 2 (1): 1-44.

Ministry of Information.2002. *The Federal Democratic Republic of Ethiopia: Foreign Affairs and National Security Policy and Strategy*. Addis Ababa: Ministry of Information

Mohammed Dejen Assen.2016. Contested Secularism in Ethiopia: The Contention Between Muslims and the Government. PhD Dissertation, Center for Federal Studies, College of Law And Governance Studies. Addis Ababa University

Ramazani, R. K. 1989. "Iran's Foreign Policy: Contending Orientations". *Middle East Journal*. 43 (2): 202-217.

Trading Economics, 2020. Ethiopia exports from Saudi Arabia and Ethiopia imports from Saudi Arabia. Avaialbale [https://tradingeconomics.com/ethiopia/imports/saudi-arabia] and [https://tradingeconomics.com/ethiopia/ exports/saudi-arabia]. Accesseed. June 14, 2020.

UNCTD, United Nations Conference on Trade and Development. 2019. *World investment report*. 2019. New York: United Nations.

UNDP, Human Development Report 2019 “Briefing note for countries on the 2019 Human Development Report Ethiopia”. Available [http://hdr.undp.org/sites/all/themes/hdr_theme/country-notes/ETH.pdf] Accessed, June 14, 2020.

**ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር. 1989. *የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ፤* የሚኒስትሮች ም/ቤት ህዳር 13 ቀን 1989 ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ የጸደቀ አዲስ አበባ፡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡፡**

**ገብሩ አስራት (2006) *ሉዓላዊነትና ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ፤* አዲስ አበባ፡፡**

# የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ አቅጣጫና በቀይ ባህር እና በባህረ ሠላጤው አካባቢ ያለን ወቅታዊ ግንኙነት

ጎሩይ አማኑኤል

## 1 መግቢያ- ታሪካዊ ቅኝት

ኢትዮጵያ ነፃነቷን ጠብቃ ለረጅም ዓመታት የቆየች አገር መሆኗ ይታወቃል፡፡ በዚህ ረጅም ዘመን ውስጥ በቅርብና በርቀት ካሉ አገራት ጋር የዲፕሎማሲ ግንኙነት ስታካሂድ ቆይታለች፡፡ ወደ ኋላ ያለው የዲፕሎማሲ ግንኙነት ታሪክ በአመዛኙ የሚያተኩረው በአገር ውስጥና በጎረቤት የሚገኙ ባላንጣዎችን ለማሸነፍና የበላይነት ለማግኘት የሚያስችል የጦር መሣሪያ ለማግኘት የሚያስችል ዕድል በማግኘት ላይ የሚያተኩር ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ ድረስ ቀጥሏል፡፡

በአንፃራዊነት ቅርብ ወደሆነው ጊዜ ስንመጣ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አስርተ-ዓመታት ላይ ወደ ስልጣን የመጡት አፄ ኃይለ ስላሴ ይህንን የዲፕሎማሲ ፖሊሲ ቀጥለውበት በቅርብና በሩቅ ካሉ አገራት ጋር ስትራቴጂካዊ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶችን አጠናክረው ቀጥለዋል፡፡ የተለያዩ ውጤቶችንም አግኝተውበታል፡፡

ኢትዮጵያ ከጣልያን ወረራ ነፃ ከወጣች በኋላ በአፄ ኃይለ ስላሴ የረጅም ጊዜ የዲፕሎማሲ ግንኙነቶችን አጠናክረው በመቀጠል የተለያዩ ብሔራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ውጤቶችን አግኝተዋል፡፡ በዓለም አቀፍ ከተገኙ ውጤቶች መካከል የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ የመጀመሪያው በአፍሪካን ለመቀራመት አህጉሪቱን ባጥለቀለቁት ኮሎኒያል ኃይሎች ሳቢያ በኢጣልያ ቅኝ ገዢነት ስር የቆየችውን ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል በማድረግ ኢትዮጵያ የቀይ ባሕር ተዋሳኝ በማድረግ ለአገሪቱ የባሕር በር አስገኝተዋል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ሊጠቀስ የሚችለው አፍሪካ አገራት ከቅኝ አገዛዝ ቀንበር ነፃ በወጡበት በእ.ኤ.አ በ1960ቹ ማግስት የተለያዩ አቋሞች የነበራቸውን ነፃ የአፍሪካ አገራት ወደ አንድ እንዲመጡ በማድረግ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲመሠረትና ጽ/ቤቱም በአዲስ አበባ እንዲቋቋም ኢትዮጵያ ቀደምት ሚና እንድትጫወት አስችለዋታል፡፡

2ኛው የዓለም ጦርነት ማብቃትን ተከትሎ በነበረው የቀዝቃዛው ጦርነት ፍጥጫ ውስጥ ኢትዮጵያ ገለልተኛ ነበረች ማለት አይቻልም፡፡ በወቅቱ ከምስራቁ ጎራ በተቃራኒ ከዩናይትድ ስቴትስና አጋሮቿ ጋር ጥብቅ ግንኙነት አዳብራ ነበር፡፡ እንዲያውም ዩናይትድ ስቴትስ በኢትዮጵያ ውስጥ የጦር ሠፈር እንድታቋቁም በመፍቀዷ የቀድሞዋ ሶቭየት ሕብረት ዒላማ ነበረች፡፡

አፄ ኃይለ ስላሴን ከስልጣን አውርዶ ራሱን ወደ ስልጣን ያመጣው የደርግ ወታደራዊ መንግሥት አስተዳደር የርዕዮተ-ዓለም ለውጥ በማድረጉ የኢትዮጵያም ዲፕሎማሲ ሁኔታ የዓይነትና የትኩረት ለውጥ አስከትሏል፡፡ የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም በተከተለው የደርግ መንግሥት መርህ ሳቢያ ኢትዮጵያ ከምዕራቡ ዓለም ጋር (ቻይንንም ጨምሮ) የነበራትን ግንኙነት በማላላት ከምሥራቅ አውሮፓ ሶሻሊስት አገራት ጋር ጥብቅ መተሳሰር ፈጥሯለች፡፡

ይሁን እንጂ የደርግ መንግሥት አፍሪካን በተመለከተ የአፄ ኃይለ ስላሴ መንግስት ይከተለው የነበረውን ፖሊሲ ቀጥሎበታል፡፡ በዚህ መሠረት ከቅኝ ግዛት ነፃ ለመውጣት ይደረጉ የነበሩ ትግሎችንና ሌሎች የመብትና የዕኩልነት ንቅናቄዎችን በጽኑ መደገፉን ቀጥሎበታል፡፡ በዚህ መሠረት ኢትዮጵያ በአሁኖቹ ዝምባቡዌ፣ ናሚቢያ እና ምዕራብ ሠሀራ ይደረጉ ለነበሩትን የነፃነት ትግሎች፤ እንዲሁም በደቡብ አፍሪካ ይካሄድ ለነበረው የፀረ-አፓርታይድ ትግል የዲፕሎማሲ እና ሌሎች ድጋፎችን ማድረጓን ቀጥላበት ነበር፡፡

በ1983 የተደረገው የመንግሥት ለውጥን ስልጣን ላይ በወጣው የኢሕአዴግ መራሹ መንግሥት ዘመን እንዲሁም የቀዝቃዛው ጦርነትን ማክተም ተከትሎ በዲፕሎማሲ ግንኙነት ረገድ ለምዕራቡ ዓለም ቅድሚያ ተሰጠ፤ እንዲሁም ከአሜሪካ እስከ ቻይና ያለው ግንኙነትም ተጠናከረ፡፡

የድሕረ-1983 ዓመታት የአገር ውስጥ ግጭቶችና ጦርነቶች የቀነሱበት ጊዜ ስለነበር የተገኘውን ዕድል በመጠቀም የተለያዩ የልማት ኢንቨስትመንቶችና መሠረተ-ልማት የተስፋፉበት ወቅት ነበር፡፡ እንዲሁም በቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት ሳቢያ ዓለምን በሁለት ጎራ የከፈላት ስርዓት በመወገዱ አገሪቱ የተለያየ ርዕዮተ-ዓለም ከሚከተሉ የተለያዩ አገራት ጋር በነፃነት የዲፕሎማሲ ግንኙነቷን ለማዳበር ችላለች ማለትም ይቻላል፡፡

በተጨማሪም የተገኘውን አንፃራዊ ሠላም በመጠቀም ከተለያዩ አገራት ጋር በልማት (ለምሣሌ ከታላቋ ብሪታንያ ጋር) እና በኢቨስትመንት (ለምሣሌ ከሕንድ እና ከቱርክ ጋር) የበለጠ ለመቀራረብ የቻለችበትም ወቅት ነበር፡፡ የተገኘው ውስጣዊ ሠላም ወታደራዊ ኃይልን ለማጎልበት ከማስቻሉ በላይ በተባበሩት መንግስታት ስር በመሆን በተለያዩ አገራት ውስጥ በተከሰቱ የርስ በርስ ግጭቶች ኢትዮጵያ በሠላም አስከባሪነት ከመሰማራቷ ባሻገር ሶማሊያ ውስጥ ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት እንድታደርግ ዕድሉን ሰጥቷታል፡፡

## 2 አዲሱ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ

ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ግንኙነቶች መንግስታት ሲቀያየሩ እንደሁኔታው ቀጣይነትና ተለዋዋጭነት (change and continuity) ሲያሳይ ኖሯል። ከቅርብ ዓመታት ውስጥ አገሪቱ የምትመራበት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲን መንግሥት በማውጣት ተግባራዊ ለማድረግ ሲጥር ቆይቷል። በዚህ መሠረት ከ1983 ወዲህ ያለውን ጊዜ ብንመለከት በሽግግር ወቅት የወጣው ቻርተር የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ክፍል ነበረው። በመቀጠልም እ.ኤ.አ በ2002 የተሻሻለ የውጭ ግንኙነትና ፀጥታ ፖሊሲ ይባል የነበረ ሠነድ ወጥቷል።

በአሁኑ ወቅት አዲስ ውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ተቀርጾ ወደ ፍፃሜ በመቃረብ ላይ ይገኛል። አዲሱ ፖሊሲ ካለፉት ፖሊሲዎች ላይ በመንተራስ እየዳበረ የመጣ ነው። ይሁንና የአቀራረብና የይዘት ለውጦችም አሉት። የፖሊሲው ረቂቅ መነሻውን በአገር ውስጥ ሁኔታ ላይ ያደረገ ሲሆን በውስጡም የተለያዩ መልካም ክፍሎችን ይዟል። ከነዚህ መካከል የሠላም ዲፕሎማሲ፣ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ፣ ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ ክፍሎች ተካትተውበታል። በተጨማሪም የፖሊሲው ረቂቅ የአየር ንብረት ለውጥን፣ ፍልሠትና ስደትን፣ ስለ ሳይበርና ሕዋ፣ ስለዜጎች ክብርና ደህንነት የመሳሰሉ ጉዳዮችን ይመለከታል። ረቂቁ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ኃሳብ እንዲሰጡበትና እንዲዳብር ተደርጓል።

## 3 የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ መነሻዎች

በአጠቃላይ ሲታይ የኢትዮጵያ የውጭ ፖሊሲ መነሻዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. የአገሪቱ ጂኦ-ፖለቲካዊ አቀማመጥ፤
2. የአገሪቱ ታሪክ፤
3. የአገሪቱ የፖለቲካ ስርዓትና የመረጋጋት ሁኔታ፤
4. የአገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም፤
5. የአገሪቱ ደህንነቷን የመጠበቅ እና ተፅዕኖ የማሳደር አቅም ናቸው።

እነዚህ ጉዳዮች በዝርዝር ስንመለከት፡ በጂኦ-ፖለቲካ አቀማመጣችንና በሕዝባችን ማንነትና አሰፋፈር ከጎረቤቶቻችን ጋር በስፋት እንገናኛለን፤ እንተሳሰራለን። ኢትዮጵያ በድንበር አካባቢ የሚኖሩ ማህበረሰቦችን ከጎረቤት አገራት ጋር ትጋራለች። ኢትዮጵያ ከኬንያ ጋር የቦረና፣ ገብራ እና የሶማሌ ብሔረሰቦችን ትጋራለች። በተመሳሳይ ሁኔታ የሶማሌ ብሔረሠብ በኢትዮጵያ፣ በሶማሊያና በኬንያ የሚገኝ ሲሆን፤ የአፋርና የኢሣ (ሶማሌ) ብሔረሠቦች በኢትዮጵያም በጅቡቲም ይገኛሉ። በደቡብ ሱዳን በኩል ስንመለከት የአኝዋክና ኑዌር ብሔረሰቦች በሁለቱም አገራት ክልሎች ይገኛሉ። በሱዳን በኩል በቤኒሻንጉል ክልል ባሉ

የተለያዩ ብሔረሠቦች ስንተሳሰር በኤርትራ በኩል በሁለቱም አገራት የሚኖሩ ትግርኛና አፋር ተናጋሪ ሕዝቦች ይገኛሉ። እነዚህ የጋራ መተሳሰሪያ በሆኑ ሕዝቦች ላይ መስራት ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ጥቅም ሊያስገኝ ይችላል የሚል ዕምነት አለ። በመሆኑም አንዱ የዲፕሎማሲ አቅማችን ሕዝባችን ነው። ይሁንና እስካሁን ባለው የዲፕሎማሲ ስራችን እነዚህ ሕዝቦች በብዛት የሚሳተፉበት አይደለም። እነዚህ ህዝቦች ከማዕከል ርቀው በድንበር አካባቢ ስለሚገኙ በኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ስራና የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አፈጻጸም ላይ በሚገባ ደረጃ ተሳታፊ አልሆኑም። ለማሣያ ያህልም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ የአጎራባች አገራት ቋንቋ ችሎታ ውስን መሆን የዚህ ችግር አመላካች ነው።

ሌላው ተፅዕኖ የማሳደሪያ አቅማችን የውኃ አቅራቢ አገር መሆናችን ነው። የውኃ አቅራቢ አገር ከመሆናችን አንፃር ለምናቀርበው ውኃ ተገቢውን ዋጋ ማግኘት ይኖርብናል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ያለው ሌላው የተፅዕኖ ማሳደሪያ አቅማችን ኃይል (ኤሌክትሪክ) አቅራቢ አገር መሆናችን ሊጠቀስ ይገባዋል። ሌላው አቅማችን ደግሞ የወታደራዊ ኃይላችን ሲሆን በዚህም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በዓለም አቀፍ አሠላለፍ ውስጥ ገብተን የምንሳተፍባቸው መስኮች እየሰፉ መጥተዋል። በሠላም አስከባሪነት በዳርፉር፤ በደቡብ ሱዳን (በአብዬ ግዛት) እና በሶማሊያ በሠላም አስከባሪነት ያለን ሲሆን ቀደም ሲል በላይቤሪያ፣ ቡሩንዲና ሩዋንዳ ተሰማርተን አመርቂ ውጤት አምጥተናል። ወደኋላ በጣም ከሄድን በኮሪያ እና በኮንጎ መሰማራታችን በመስኩ ያለንን ልምድና ባህል ያመለክታል። ከዚህ በተጨማሪ በዓለም አቀፍ መድረኮችና በሁለትዮሽና ሦስትዮሽ ግንኙነቶች የዲፕሎማሲ ስራዎች ይሰራሉ። በአፍሪካ አንድነት፤ በተባበሩት መንግስታት ድርጅትና በሌሎች መድረኮችም ዕድሎች በፈቀዱ መጠን በመሳተፍ የዲፕሎማሲ ስራዎች ይሰራሉ።

ኢኮኖሚን ስንመለከት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመሠረተ-ልማት ከጎረቤት አገሮች ጋር ይበልጥ እየተገናኘንና እየተሳሰርን መጥተናል። ከአዲስ አበባ ካርቱም፣ ጅቡቲ፣ አስመራ፤ ናይሮቢ እና ደቡብ ሱዳን ጠረፍ ድረስ ያሉት መንገዶች የሚጠቀሱ ናቸው። እነዚህ መሠረተ-ልማቶች፣ ንግድና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቶች የዲፕሎማሲ ግንኙነቶቻችንን ይበልጥ የሚያዳብሩ ናቸው።

ይህ በዚህ እንዳለ በውጭ ግንኙነታችን ውስጥ ስጋቶችም አሉብን። የደህንነት፣ የዘርና የኃይማኖት ጽንፈኝነት፣ የጸጥታ መጓደል፣ የባሕር በር አለመኖር ዋና ዋናዎቹ ስጋቶቻችን ናቸው። በብሔራዊ ደረጃ ገና ሙሉ በሙሉ አለመዋሀዳችን (national integration) ጠንካራ የፖለቲካና የኢኮኖሚ አሀድ (entity) ለመሆን ገና እንዲቀረን አድርጎናል። በዚህ ረገድ የሕዝቦች ሕብረት መኖር ወሳኝ ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህን ሕብረት ማጠናከር የሚቻለው ኢኮኖሚውን በማሳደግና ዕድል በመስጠት እንደሆነ ግልጽ ነው። በዚህ ረገድ የውጭ ፖሊሲያችን የኢኮኖሚ ዕድገታችንን ማገዝ ይኖርበታል። በየውጭ አገራቱ የተመደቡ

ዲፕሎማቶች አገሪቱን ሊጠቅሙ የሚችሉ ሁኔታዎችን በማጥናት ኢኮኖሚውን የሚጠቅሙ ስራዎችን ማከናወን ይኖርባቸዋል። ይህን በማድረግ ውጤታማ ኢንቨስተሮችን ውጤታማ ካልሆኑት በመለየት ኢንቨስት እንዲያደርጉ ማበረታታት ይቻላል።

## 4 ኢትዮጵያ ከጎረቤትና አካባቢ አገራት ጋር ያላት ወቅታዊ ግንኙነት

ኢትዮጵያ ከጎረቤትና አካባቢያዊ አገራት ጋር የተለያየ መልክ ያላቸው አንዳንዴም ተለዋዋጭ ግንኙነቶችን ስታደርግ ቆይታለች። እነዚህ ግንኙነቶች በአሁኑ ባለው አገራዊ፣ አካባቢያዊና ዓለም አቀፋዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች አንፃር ምን መልክ እንዳላቸው በመጠኑ ለመዳሰስ ልሞክር።

በኢትዮጵያና በኤርትራ ጋር ያለው ግንኙነት ሁኔታ በሠፊው የሚታወቅ ነው። ከሌሎች ጎረቤት አገሮቻችን ጋር ካሉን ግንኙነቶች በዓይነቱ የተለየና የተወሳሰበ ነው። በአንድ በኩል ከኤርትራ የበለጠ እንደ አገር የሚቀርበን ስለሌለ ግንኙነቱ እጅግ የተቀራረበ ነው። በሌላ በኩል ኤርትራ ከኢትዮጵያ በኃይል ተገንጥላ በቅርብ የወጣች አገር በመሆኗ በህብረተሠቡ ዘንድ አሁንም ያልበረደ መልካም ያልሆነ ስሜት አለ። በተጨማሪ ከኤርትራ ነፃነት በኋላ በመሬት ይገባኛልና የድንበር ውዝግብ ሳቢያ ሁለቱም አገራት ከፍተኛ ዋጋ የከፈሉበት ጦርነት ውስጥ ገብተዋል። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ የተጀመረውን የፖለቲካው ለውጥ ተከትሎ በሁለቱ አገራት መካከል የሠላም ስምምነት ተደርጓል። የድንበር መከፈትና ሌሎች ግንኙነቶች የተጀመሩ ቢሆንም ሁኔታው ከአራት ወራት በላይ አልዘለቀም። አሁንም ግንኙነቱን መልክ ለማስያዝ ጊዜ ይጠይቃል። በአገራቱ መካከል ስምምነት ቢፈረምም የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት፣ ንግድንና የገንዘብ ጉዳይን ጨምሮ ገና ስምምነት ያልተደረሰባቸው ብዙ ጉዳዮች አሉ። ኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር በሚኖራት ግንኙነት ላይ ያለው ሌላው ጉዳይ በአገር ውስጥ በሚገኙ ሁሉም አካላት መካከል ግንኙነቱን በተመለከተ ተመሳሳይ አቋም ላይ መድረስ ያስፈልጋል። በአሁኑ ጊዜ ከኤርትራ ጋር የሚዋሰነው የትግራይ ክልል ስሜት አዲስ አበባ ካለው የፌዴራል መንግስት ስሜት ጋር ልዩነት ይታይበታል። ይህ ልዩነት መፈታት ይኖርበታል።

ከጅቡቲ ጋር ያለን ግንኙነት ይበልጥ የተሳሰረ ይመስላል። ግንኙነቱ በንግድ፣ በመገናኛ (አሁን የተጠናቀቀውን ባቡር ጨምሮ) እና ኢነርጂ በመሳሰሉት መስኮች የተጠናከረ ሲሆን ወደፊት ይዘረጋል ተብሎ የሚታሰበው የነዳጅ ማስተላለፊያ ቧንቧ መስመር ይበልጥ ያጠናክረዋል የሚል ዕምነት አለ። በሌላ በኩል በጅቡቲ ብዙ አገራት የጦር ሠፈሮች መመስረታቸው የሁለቱን አገራት ግንኙነት ሊፈታተን ይችላል የሚል አመለካከት ይስተዋላል። ይሁን እንጂ የተለያዩ አገራት የጦር ሠፈሮች በጅቡቲ መኖራቸው ሁለቱን አገራት ሊያራርቅ ይችላል የሚል ዕምነት የለኝም። ምክንያቱም ኢትዮጵያ ጅቡቲን

የምትፈልጋት ያህል ጅቡቲም ኢትዮጵያን ትፈልጋለች፡፡ ይህ መፈላለግ ደግሞ ይቀጥላል ተብሎ ይታመናል፡፡ ኢትዮጵያ የባሕር ደህነቷን ለማረጋገጥ የባሕር ኃይሏን ዳግም ለመመስረት የመፈለግ አዝማሚያ አላት፡፡ ይህን ማድረግ በሁለቱ አገራት ግንኙነት ውስጥ የራሱን አዎንታዊም አሉታዊም ተፅዕኖ ይዞ ይመጣል፡፡ በቆዳ ስፋትና በሕዝብ ብዛት ኢትዮጵያ ትልቅ አገር፤ ጅቡቲ ደግሞ ትንሽ አገር መሆናቸው በግንኙነቶቻው ውስጥ የሚያስከትለው ውስብስብነት አለ፡፡ ለምሣሌ የጅቡቲ ዜጎች ወደ ኢትዮጵያ ካለ ቪዛ የሚገቡ ሲሆን ኢትዮጵያውያን ግን ወደ ጅቡቲ ለመጓዝ ቪዛ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ኢትዮጵያውያን ካለ ቪዛ ይጓዙ ቢባል በጅቡቲያውያን በኩል በኢትዮጵያውያን እንጥለቀለቃለን የሚል ስሜት ሊያሳድር ይችላል፡፡

ከሱዳን ጋር ያለን ግንኙነት ቀደም ሲል የሚዋልል ነበር፡፡ በሁለቱ አገራት የተጀመሩት የፖለቲካ ተሀድሶ እንቅስቃሴዎች ግንኙነቱን አሻሽለውታል፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ በሱዳን በኩል ከሞላ ጎደል የወዳጅነት መንፈስ ይታያል፡፡ በአረባዊነትና በአፍሪካዊነት መካከል የሚዋልለውን የሱዳኖች ማንነትን በአዲስ የሱዳን ብሔራዊ ማንነት የመተካት እንቅስቃሴያቸው የሁለቱን አገራት ግንኙነት ይበልጥ ያጠናክረዋል የሚል ዕምነት አለ፡፡ ሁለቱን አገራት የሚያገናኛው አንዱ ዋና ጉዳይ የዓባይ ወንዝና ኢትዮጵያ እየገነባች ያለችው የሕዳሴ ግድብ ነው፡፡ ሱዳኖች ግድቡ ለእነርሱ የሚሰጠውን ጥቅም እንደሚገነዘቡ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ የአገራቱ ግንኙነት ከተግዳሮት የፀዳ ነው ማለት አይቻልም፡፡ በተለይ በድንበር አካባቢ የመሬት ይገባኛል ጥያቄ አለ፡፡ ሱዳን የእኔ ነው በምትለው አካባቢዎች የኢትዮጵያ ገበሬዎች ሠፍረው እያመረቱ ምርቱም ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በኢትዮጵያ በኩል ወደገበያ ስለሚወጣ ሱዳን ምንም ጥቅም አላገኘሁም የሚል ቅሬታ አላት፡፡ ይህ ጉዳይ ወደፊት የሚታይ ነው እየተባለ ለዘመናት ሲንከባለል ለብዙ ዓመታት ቆይቷል፡፡ ይህ መፍትሔ ሊበጅለት ይገባል፡፡

ከደቡብ ሱዳን ጋር ያለን ግንኙነት ማለፊያ ነው፡፡ ደቡብ ሱዳኖች የነፃነት ትግላቸው ውስጥ ኢትዮጵያ ባለውለታ እንደሆነች ይቆጥራሉ፡፡ ከነፃነት በኋላም ኢትዮጵያ ሠራዊት በመመደብ ሠላም በማስከበር አስተዋፅኦ አድርጋለች፡፡ ይሁን እንጂ በድንበር ጉዳይ በተለይ በጋምቤላ በኩል አሁንም ጥያቄዎች አሉ፡፡ ደቡብ ሱዳኖች ድንበርን የመሬት ጉዳይ ብቻ አድርገው አይመለከቱም፤ የብሔረሠቦችና ሕዝቦች አሠፋፈር ጉዳይም እንጂ፡፡ በዚህ ሳቢያ ደቡብ ሱዳን ውስጥ ያሉ ብሔረሠቦች (ለምሳሌ የኑዌር ብሔረሠብ) ያሉባቸው የኢትዮጵያ አካባቢዎች የደቡብ ሱዳን አካል መሆን አለባቸው የሚል አመለካከት በአንዳንድ የህብረተሠብ ክፍሎች መካከል ይንፀባረቃል፡፡ ይህ ወዴት ሊያመራ ይችላል የሚለው ጉዳይ ከወዲሁ ሊታሰብበት ይገባል፡፡

ከሶማሊያ ጋር ያለን ግንኙነት የተወሳሰበ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ የሶማልኛ ተናጋሪ ብሔረሠብ አባላት ክልል መኖሩ ግንኙነቱ ላይ አዎንታዊም አሉታዊም አስተዋፅኦ ይኖረዋል። በአንዳንድ የሶማሊያ ልሂቃን አካባቢ ሶማሊያ ዘወትር የተከፋፈለችና የተዳከመች ሆና እንድትኖር ኢትዮጵያ ትጥራለች የሚል አመለካከት አለ። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ክልሎች ተከፋፍለው ይኖሩ የነበሩትን የሶማሌ ብሔረሠብ አባላት በአንድ ራሱን በቻለ ክልል እንዲሰባሰቡ ማድረጓ ጎረቤት ሶማሊያን ደካማና የተከፋለች ለማድረግ ትጥራለች የሚለው አመለካከት መሠረተ ቢስ መሆኑን ያመለክታል። በዚህ ረገድ ያለውን ጥርጣሬ ለማስወገድ ብዙ ጥረት መደረግ ይኖርበታል። ኢትዮጵያ ወዳጅ አገር ትፈልጋለች። ሶማሊያና ኢትዮጵያ እንደ አገርም እንደ ሕዝብም እጅግ የተሳሰሩ ናቸው። እዚህ ላይ አንድ ነጥብ ማንሳት ይቻላል። በቅርቡ ጅግጅጋ ላይ የእንግሊዝ ቅኝ ገዥዎችን ይታገል ለነበረው መሐመድ አብዱላሂ ሐሠን ሐውልት ቆሞለታል። ከጅግጅጋ 109 ኪ.ሜ. ርቀት ሐረር ላይ ደግሞ የልዑል መኮንን ሐውልት ይገኛል። ይህ ሁኔታ በአገራችን በልዩነት ውስጥ ያለውን አንድነትና ከሶማሊያ ጋር ያለንን ቅርርብ የሚያመለክት ነው።

ኢጋድን በሚመለከት አዲስ ሕገ-ደንብ ለማውጣት እየታሰበ መሆኑ ይሰማል። አሁን ያለው ድርጅቱን እምብዛም የማይገልጸው ዓርማም በዚያው ይሻሻላል የሚል ዕምነት አለኝ። የአፍሪካ ሕብረት ለኢትዮጵያ ትልቅ ሥፍራ የሠጠ፣ የአገሪቱን ስም ከፍ አድርጎ ያስጠራ ድርጅት ነው። የአፍሪካ ሕብረት በአዲስ አበባ በመገኘቱ ብቻ እስከ 120 የሚደርሱ አገራት ኤምባሲዎቻቸውን በአገራችን እንዲከፍቱ ግፊት ፈጥሯል። አገራቱ የተባበሩት መንግስታትን በመሳሰሉ ዓለም አቀፍ መድረኮች ያላቸውን ጉዳይ ለማስፈጸም የአፍሪካ አገራትን ድጋፍ ይፈልጋሉ። ለዚህም ሲሉ በሕብረቱ መቀመጫ በሆነችው በአዲስ አበባ ኤምባሲዎቻቸውን ይከፍታሉ። ይህም ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸው ግንኙነት እንዲዳብር ያደርጋል።

በአሁኑ ጊዜ የቀይ ባሕር ጉዳይ እና ከኤደን ባሕረ-ሠላጤ አገራት ጋር ያለን ግንኙነት በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ሆኖ መጥቷል። እዚህ ላይ ለምንድነው ይህ ከዛሬ አራትና አምስት ዓመታት በፊት ብዙም ትኩረት ይሠጠው ያልነበረ ጉዳይ ዛሬ በጣም አንገብጋቢና ትኩረት የሚሻ ጉዳይ የሆነው የሚለው ጥያቄ መመለስ ይኖርበታል። ያለፉት 3-4 ዓመታት በዚህ አካባቢ የተለያዩ አገራት የጦር ሠፈሮች ለመክፈትና የወደብ አገልግሎትን ለመቆጣጠር የተንቀሳቀሱበት ዓመታት ናቸው። ለምን ወደዚህ መጡ ለሚለው ጥያቄ ሙሉ ለሙሉ አጥጋቢ መልስ ገና ያገኘን አይመስለኝም። ይሁን እንጂ አንዳንድ መላ ምቶችን መሠንዘር ይቻላል። አንዱ ምክንያት ቀደም ባሉት ዓመታት አሜሪካ በአካባቢው ላሉ አገራት ትሰጠው የነበረው የጥበቃ ተገን (security umbrella) ማንሳቷ እና በዚህም ምክንያት አገራቱ የራሳቸውን ጥቅምና ደህንነት በራሳቸው አቅም ለማስጠበቅ በመገደዳቸው በአካባቢዎቹ

ያላቸውን እንቅስቃሴ አጠናክረዋል ማለት ይቻላል፡፡ አገራቱ ወደቦችን ሲቆጣጠሩ ድርሻቸውን ለማስጠበቅና በዓለም አቀፍ ውድድር ውስጥ ራሳቸውን ሲያመቻቹ ነው የሚል ዕሳቤ አለ፡፡

ሁለተኛው ሊሆን የሚችለው ምክንያት በየመን የተቀጣጠለው ጦርነትና የኢራን ደጋፊ የሆኑ ወገኖች እስካሁን አለመሸነፍ ሲሆን፤ ኢራንን እና የሺዓ እስልምና ዕምነት ተከታይ ወገኖችን ተፅዕኖ ለመከላከል በየስፍራው መገኘትና መስፈር አለብን የሚል አስተሳሰብ ፈጥሮ ሱኒ አረብ አገሮች ደሴቶችን ሳይቀር እስከመቀራመት አድርሷቸዋል፡፡

በእኛ በኩል ከክልሉ ጋር በታሪክ የረጅም ጊዜ ግንኙነት አለን፡፡ ለመጥቀስ ያህል አሁን በአካባቢው ትልቅ ተፅዕኖ በመፍጠር ላይ ያለችው የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ ነች፡፡ አረብ ኤምሬት ትንሽ አገር ብትሆንም የጦር ኃይሏ አቅም የሚናቅ አይደለም፡፡ ኤርትራ ማዕቀብ ስር በነበረችበት ዓመታት ሳይቀር አሰብ ላይ የጦር ሠፈር አቋቁማ ነበር፡፡ ኤምሬትስ ይህንን ጠንካራ ወታደራዊ ዓቅም ለመገንባት የሚያስችል ከፍተኛ ኃብት አላት፡፡ ከአገሪቷ መጠን ጋር ሲነፃፀር ጠንካራና ዘመናዊ ወታደራዊ ዓቅም ገንብታለች፡፡

ኳታር ከዩናይትድ ስቴትስና ከእስራኤል ጋር ሳይቀር የቆየ ጥብቅ ግንኙነት የመሠረተች አገር ነች፡፡ በሌላ በኩል የኳታር መሪዎች ከቱርክ ጋር በመሆን የሙስሊም ወንድማማችነት (Muslim brotherhood) ርዕዮተ ዓለም (Ideology) የሚያራምዱ ናቸው፡፡ በመሆኑም ከሳዑዲና ከኤምሬትስ ጋር በተፃራሪ ቆመዋል፡፡ ኢትዮጵያም ከኳታር ጋር ቀደም ሲል መልካም ግንኙነት አልነበራትም፡፡ ኳታር በሱዳን፤ በሶማሊያና በኤርትራ ውስጥ ጨምሮ ከተለያዩ ኢትዮጵያን ከሚቃረኑ ክፍሎች ጋር ትሰራ ነበር፡፡ አሁን ግን ግንኙነቱን ለማሻሻል ጥረት በማሳየት ላይ ትገኛለች፡፡ ለዚህም አንዱ ምክንያት ኳታር ኢትዮጵያን መቃረን በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ውስጥ ዋጋ ሊያስከፍል ይችላል በሚል ስጋት ስላደረባት ሊሆን ይችላል፡፡

ከጎረቤት አካባቢ አገራት ጋር ካለን ግንኙነቶች ጋር በተያያዘ ዛሬ የአገራችንን የውጭ ጉዳይ በተመለከተ ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች አሉ፡፡ እነርሱም የዓባይና የቀይ ባሕር ጉዳዮች ናቸው፡፡ የዓባይ ጉዳይ ቀጥሎ ባሉት ጽሑፎች በሌሎች ጸሀፊዎች በጥልቀት የተዳሰሰ በመሆኑ አልፈዋለሁ፡፡ የቀይ ባሕር ጉዳይ ግን እጅግ ወሳኝ በመሆኑ አንዳንድ ነገሮች መመልከት ይጠቅማል፡፡ ቀይ ባህር ኢትዮጵያ ከውጭው አለም ጋር በባህር የምትገናኝበት ዋና መስመር ነው፡፡ ይሁን እንጂ 1983 ኤርትራ ከኢትዮጵያ መለየት ተከትሎ አገሪቱ የቀይ ባህርን የምታገኝበት የራሷ ግዛት የላትም፡፡ በመሆኑም ለባህር በሩ ያላት ተደራሽነት በሌሎች ጎረቤት አገራት መልካም ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ ስድስት የሚሆኑ የቀይ ባሕር አዋሳኝ የሆኑ የአፍሪካና የገልፍ አገራት በሳዑዲና ግብፅ አስተባባሪነት የቀይ ባሕር ፎረም (Red Sea Forum) የሚል በጋራ የሚመክሩበት

መድረክ ፈጥረው መሰባሰብ ጀምረዋል። ይህ በአንድ በኩል ሲካሄድ በአፍሪካ በኩል የቀይ ባሕር ወሰንተኛ አገራት አንድ አቋም ሊኖራቸው ይገባል በሚል ሀሳብ በኢጋድ አስተባባሪነት መሰባሰብ ጀምረዋል፤ ታስክ ፎርስም ተመስርቷል። ኢትዮጵያ የባህሩ ኢትዮጵያ ወሰንኛ ሀገር ባለመሆኗ በሁለቱም መድረኮች ላይ አልተጋበዘችም።

## 5 ማጠቃለያ

ከላይ ከተዘረዘረው መሠረት ኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነቷን ስታካሂድ ያላትን አቅም (assets) ሙሉ ለሙሉ ተጠቅማ መስራት ይኖርባታል። የምንገኝበት አካባቢ ፉክክርና ውጥረት ያለበት በመሆኑ በአገር ውስጥ ቢያንስ በዋና ዋና ወሳኝ አገራዊ ጉዳዮች ላይ አንድ መሆንና አንድ ዓይነት አቋም ሊኖረን ይገባል። የተቀናጀ አቋም ከሌለን ፈተና ላይ እንወድቃለን።

ጠንካራ ጎኖች እንዳሉን ሁሉ፤ ድክመቶችም አሉብን። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መስራች አገር ትሁን እንጂ በአፍሪካ ውስጥ ለመከፋፈልም ኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ አገር ናት። በምግብ ዓይነቶቿ በመላው ዓለም የታወቀች ሆና ሳለ፤ ዛሬም ኢትዮጵያ በምግብ ራሷን አልቻለችም። በብዝኃ-ሕይወት የታወቀች አገር ሆና ሳለ፤ በደን መጨፍጨፍ ሳቢያ ለከፍተኛ ችግር የተዳረገች አገር ነች። በአፍሪካ በትልቅነቱ አንደኛ የሆነ አየር መንገድ እያላት፤ አገር ውስጥ በመንገድ መጠን (density) ወደኋላ ቀሩ ከሚባሉት አገራት ተርታ ነች። በአፍሪካ ውስጥ የራሷ መንግስት አካል የሆነ የመርከብ ድርጅት ያላት ብቸኛ አገር ኢትዮጵያ ናት። ነገር ግን አንድም የባሕር በር የላትም። ወደ ሚሊዮን የሚጠጋ ስደተኛ የምታስተናግድ አገር ናት። ነገር ግን ራሷ ስደተኛ አምራች አገር ናት። ኢትዮጵያ በነዚህ ተቃርኖዎች ውስጥ ያለች አገር ናት።

ያም ሆኖ ልዩ የሚያደርጉን ጠንካራ አቅሞች ስላሉን ከሰራን ጥሩ ውጤት ላይ መድረስ እንችላለን። እዚህ ላይ ለመድረስ ግን ጠንካራ ድርጅታዊ ዝግጅት ማድረግ ይጠይቃል። የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሌሎች መ/ቤቶች ጋር ተቀናጅቶ መስራት ይኖርበታል። በውጭ ያሉንን ኤምባሲዎቻችን ኢትዮጵያን በማስተዋወቅ ረገድ አንዱ ተቋም ብቻ መሆናቸው መታወቅ ይኖርበታል። የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ በውጭ አገራት ያሉ የኢትዮጵያ ሬስቶራንቶች፣ የባህል አልባሳት አቅራቢዎች፣ በኢትዮጵያ ላይ ጥናት የሚያደርጉ ተቋማት፣ ኢትዮጵያ ውስጥ በንግድ፣ ኢንቨስትመንትና ቱሪዝም መስክ የተሰማሩ እንዲሁም በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በጋራ ለጋራ ዓላማ ተቀናጅተው መስራት ይኖርባቸዋል።

# የዓባይ ውኃ አጠቃቀምና የኢትዮጵያ
# የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ

# የዓባይ ወንዝና የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ

**ያዕቆብ አርሳኖ**

### *መግቢያ*

ዓባይን ጨምሮ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞቿ ኢትዮጵያን የሰሜን ምስራቅ አፍሪቃ የውኃ ማማ እንድትባል አድርገዋታል። አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ወንዞች በሁሉም አቅጣጫ ድንበር ተሻግረው ወደ ጎረቤት ሀገሮች የሚፈሱ ናቸው። ዓባይ መቶ በመቶ ወደ ሱዳን ይገባና ወደ ግብፅ ይዘልቃል። ተከዜ መቶ በመቶ ከኢትዮጵያ ይመነጭና በመጠነኛ ርቀት የኢትዮጵያና የኤርትራ ወሰን አካልሎ ወደ ሱዳን ይፈሳል። ከዚያም በዓባይ ውኃ ካፋፋው የናይል ወንዝ ይገባል። ባሮና አቆቦ መቶ በመቶ ከኢትዮጵያ መንጭተው ወደ ደቡብ ሱዳን ይሻገራሉ። ከዚያም ሶባት ይባሉና ናይልን ይቀላቀላሉ። መረብ ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትራ ገብቶ እዚያው ይቀራል። ዋቤ ሸበሌ ሙሉ በሙሉ ከኢትዮጵያ ያጠራቀማቸውን ትንንሽ ወንዞች ይዞ ወደ ሶማሊያ ይሻገራል። ገናሌ ሙሉ በሙሉ ከኢትዮጵያ ተነስቶ ወደ ሶማሊያ ይገባል። ዳዋ መቶ በመቶ ከደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ ተነስቶ በኢትዮጵያና በኬንያ መሀል ድንበር ለድንበር ይጓዝና ከገናሌ ጋር ተገናኝቶ፣ የኢትዮጵያና የሶማሊያን ድንበር በትንሹ ነክቶ ከገናሌ ጋር ይቀላቀላል።

እንግዲህ በሁሉም አቅጣጫ ኢትዮጵያን የሚያዋስኗት ጎረቤት ሀገሮች ከኢትዮጵያ የውኃ ፍሰት የሚቀበሉ ናቸው። ከደቡብ ሱዳን በስተቀር ሁሉም የኢትዮጵያ ጎረቤቶች በረሃማ ወይም ደረቅ የአየር ጠባይ ያላቸው በመሆኑ የሕዝቦቻቸው ቁጥርና የልማት ፍላጎታቸው እየጨመረ ስለሚሄድ ከኢትዮጵያ የሚፈልጉት የውኃ ጥቅም እየጨመረ የሚሄድ መሆኑን መገመት ይቻላል። በመሆኑም በድንበር ተሻጋሪ ወንዞቿ አማካይነት የኢትዮጵያ ጎረቤቶች ከኢትዮጵያ ጋር ከፍ እያለ የሚሄድ የጋራ ንብረት ቁርኝት ይኖራቸዋል ማለት ነው። ኢትዮጵያ የውኃ ሀብቷን ማልማት አማራጭ የሌለው በመሆኑ፤ ጠንካራ፣ ዘላቂና ተፅዕኖ ያለው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ማበጀትና በአፈፃፀሙ ላይ መትጋት ይኖርባታል።

## የድንበር ተሻጋሪ ውኃዎች ፖሊሲ አስፈላጊነት

ድንበር ተሻጋሪ ውኃዎች በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሉዓላዊ ሀገሮች መካከል ያሉ ቋሚና ዘላቂ ንብረቶች ተደርገው ይቆጠራሉ። አጠቃቀማቸው፣ አስተዳደራቸው፣ እንክብካቤያቸውና ጥበቃቸው በመንግስታቱ መካከል የሚደረጉ የፖለቲካ ትብብርን፣ የጋራ ስምምነትንና ተቋማዊ ማዕቀፍን የግድ ይላሉ። የድንበር ተሻጋሪ ወንዞችን ጉዳይ በውኃ ፖለቲካና በሀገሮቹ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አንፃር መቃኘትና መተግበር አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው። በመሆኑም ድንበር ተሻጋሪ ወንዞችና የውኃ ሀብቶች በተጋሪ ሀገሮች መካከል ያሉ ዘላቂ የጋራ ሀብት መሆናቸውን ማጽናት፣ በመተማመንና በመተሳሰብ ለመጠቀም መስማማት፣ በጋራ የመጠበቅና የመንከባከብ ኃላፊነትን መቀበል የግድ ይላል። የጋራ ውኃ ሀብትን ለዘላቂ ትብብር፣ ለልማትና ለጋራ ብልጽግና ሲባል ተጋግዞ ማልማት ከምኞት ባለፈ አስፈላጊነቱ የጎላ ነው። እነዚህ ሀሳቦች ጠቋሚ የመሆናቸውን ያህል፣ ውኃ በሚጋሩ ሀገሮች መካከል የቆየውንና ያለውን ውስብስብ የብሔራዊ ጥቅም ጉዳዮችን ማስከበሪያ ቀያይ መስመሮች አስምሮ ጥንቃቄ በተሞላ ድርድርና ስምምነት አማካይነት ማስፈጸም ተገቢ ነው። በሰሜን ምስራቅ አፍሪቃ ካለው ወቅታዊ የውኃ ፖለቲካ አንፃር ስንነሳ የዚህ ጽሁፍ ዋና ትኩረት ኢትዮጵያ በዓባይ ውኃ ላይ ያላትን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲን መፈተሽና መተንተን ይሆናል።

## የኢትዮጵያ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞችና የዓባይ ልዩ ሁኔታ

ከኢትዮጵያ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች መሀል የዓባይ ወንዝ ልዩ ሥፍራ አለው። የዓባይ ዓመታዊ አማካይ ፍሰት 49 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ሲሆን፤ ተከዜን (11 ቢ.ኪ.ሜ)፣ ድንዳርን እና ረሃድን (3 ቢ.ኪ.ሜ) እንዲሁም ባሮና አቆቦን (23 ቢ.ኪ.ሜ) ከጎኑ አሰልፎ፤ ናይል ተብሎ ለሚታወቀው ለታላቁ የሰሜን ምስራቅ አፍሪቃ ወንዝ 86% የውኃ ፍሰት በማቀበል ይታወቃል። በመሆኑም የዓባይ ወንዝ ለታላቁ የናይል ወንዝ ማንነትና ምንነት፤ እንዲሁም ዝና መሠረት የሆነና ዝንተ-ዓለም የማይነጥፍ የሰሜን ምስራቅ አፍሪቃ የውኃ ሀብትና ጸጋ ነው። የናይል ወንዝ በታሪክ ታዋቂነቱ፣ በተፋሰስ ስፋቱ፣ በሚያቋርጣቸው ሀገራት ብዛቱ፣ በተፈጥሮ ድልድይነቱ፣ በልማት አስተዋጽኦው እንዲሁም በጂኦ-ፖለቲካዊ ሚናው ብዙ ሊባልለት ይችላል።

## የናይል ታሪካዊነትና ጥንታዊነት

የናይል ወንዝ በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ በአራት ዘፍጥረት የኤደን ገነት ወንዞች ተብለው ከተጠቀሱት አንዱ ሲሆን የኩሽ ምድርን የሚያጠጣ ወይም ኢትዮጵያን የሚከብ ወንዝ

ወይም ግዮን ተብሎ ተጠቅሷል። ግዮን ማለት ዓባይ መሆኑ ይታወቃል። በ700[3] ዓመተ ዓለም ግድም ነብዩ ኢሳያስ ስለናይል ወይም ስለኩሽ ወንዝ አንስቶ ስለተፋሰሱ ነዋሪዎች ባሕሪይ በሰፊው እንዳብራራ በመጽሐፉ ውስጥ ተገልጿል። በ450 ዓመተ ዓለም ግድም የኖረው ሔሮዶቱስ የተባለ ግሪካዊ የታሪክ ጸሐፊ “ግብፅ የናይል ስጦታ ናት” ብሎ እንደጻፈ ይወሳል። የጥንቱ የግሪክ ነገሥታት ቤተሰቦቻቸውን ለጤናቸው ፈውስና ለሕይወታቸው መታደስ ወደ ኢትዮጵያ ይልኳቸው እንደነበርም ይነገራል። ፈውስ ፈላጊዎቹ በዓባይ እየተጠመቁ ጤናና ተሐድሶ ያገኙ እንደነበረ ይታመን ነበር።

ግብፅን በዝርዝር ያጠናው ሴኔጋላዊ ምሁርና ፈላስፋ ሼይክ አንታ ዲዮጵ ግንባር ቀደም የግብፅ ሥልጣኔ ተመራማሪ ሆኖ ባገኘው ዕውቀት መሠረት፣ በግብፅ የሚታየው የጥንታዊ ሥልጣኔ መሠረቱና ምንጩ ከኢትዮጵያ መሆኑን THE AFRICAN ORIGIN OF CIVILIZATION በሚል ርዕስ በ1975 ባሳተመው መጽሐፉ አማካይነት አስረድቷል። ኤሚል ሉድዊግ የተባለ ሌላ ጸሐፊ፤ THE NILE በሚል ርዕስ በ1938 (እ.ኤ.አ) ባሳተመው መጽሐፉ ናይል የ6,000 ዘመን ድንቅ ታሪክ መገለጫ ነው ብሎ ነበር። ሌሎች በርካታ ጸሐፍት ባቆዩት መረጃም ሆነ በየጊዜው በሚወጡ የአርኪዮሎጂ ግኝቶች ናይል የግብፅን ሥልጣኔ የተሸከመ መሆኑ የታመነ ነው። የሆነ ሆኖ 86% የናይልን ውኃ የተሸከሙት ዓባይ እና ተጓዳኝ የኢትዮጵያ ወንዞች መሆናቸው የማይሻር ሐቅ ነው። ይህን ዘመናትን የተሻገረና ለወደፊትም የሚቀጥል ሐቅ በተለይ ታችኞቹ የናይል መንግስታትና ሕዝቦች መዘንጋት አይገባቸውም።

## ናይል ከየት ወዴት

የናይል ወንዝ ርዝመቱ ከምንጩ እስከ መዳረሻው 6,650 ኪሎ ሜትር ሲሆን በርዝመት በዓለም ላይ ተወዳዳሪ የለውም። የተፋሰሱ ስፋት የአፍሪቃን አህጉር አንድ አስረኛ ይሸፍናል። የተለያየ የውኃ መጠን ለናይል የሚያቀብሉና የናይል ውኃ አቋርጦ የሚሄድባቸው አስራ አንድ ሀገሮች በተፋሰሱ ውስጥ ይገኛሉ። ከነዚህ መሀከል፣ ኢትዮጵያን ጨምሮ የውኃ አመንጪ ሀገሮች ዑጋንዳ፣ ብሩንዲ፣ ዲሞክራቲክ ሪፓብሊክ ኮንጎ (ዲ.አር.ሲ)፣ ሩዋንዳ፣ ታንዛኒያና ኬንያ ሲሆኑ፤ ደቡብ ሱዳን፣ ሱዳንና ኤርትራ ከናይል ውኃ አመንጪ ሀገሮች የሚመጣውን ውኃ ወደታችኛው ተፋሰስ የሚያስተላለፉ አገራት ናቸው። ግብፅ የናይል ውኃ የመጨረሻ መዳረሻ ሀገር ስትሆን ለናይል አንዳችም ጠብታ ውኃ አታበረክትም። የናይልን ተፋሰስ ተፈጥሯዊ ባህርይ ባለማስተዋል የመጨረሻው ተደራሽ የሆነችው ግብፅ የናይልን

[3] በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ያለው የዘመን አቆጣጠር በተለይ ካልተገለፀ በስተቀር በሙሉ እንደ አውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ነው።

የውኃ ሀብት ለብቻዋ ለመቆጣጠር የምታደርገው ያልተገባ አካሄድ የሀገራቱን ሰላማዊ የውኃ አጠቃቀምና አስተዳደር ሲያወዛግብ ቆይቷል።

## የናይል የተፈጥሮ ድልድይነት

የናይል ወንዝ ከደቡብ ወደ ሰሜን የሚፈስ ታላቅ ጅረት ሲሆን አብዛኛውን የውኃ ፍሰት የሚያገኘው ከወደ ምስራቅ አቅጣጫ ከሚገኙ ከኢትዮጵያ ተራሮችና ከፍተኛ ሥፍራዎች መሆኑ የተረጋገጠ ነው። ናይል በተፈጥሮ የዝናብ ውኃ ከታደለው የምድር ወገብ አካባቢ ወደ ሰሜን በረሃማ አካባቢ ዝንተ-ዓለም የሚፈስ ለጋስ የውኃ ሀብት ነው። ናይል እርጥቡንና በርሃማውን ሁለት ጫፎች በማገናኘት የሕይወትና የሥልጣኔ መሠረትና ድልድይ ሆኖ ሲያገለግል ኖሯል። ለወደፊትም እንዲሁ ይቀጥላል። ሼይክ አንታ ዲዮጵ እንደደመደመው ዓባይ ባይኖር ኖሮ በግብፅ በረሃ እንኳን ሥልጣኔ ሕይወትም አይኖርም ነበር። ናይል ያበጀውን ድልድይነትና አገናኝነት በእንክብካቤ መያዝና መዝለቅ የሚያስፈልገው ለተፋሰሱ ሀገሮችና ሕዝቦች ቋሚ አገናኝ ሆኖ መቀጠል ስለሚገባው ነው።

## የናይል የልማት ሚና

ናይል ከጥንት ጀምሮ የተፋሰሱ ኗሪዎች የመተዳደሪያና የሥልጣኔ ምንጭ ሆኖ ቆይቷል። የመስኖ እርሻ፣ የውኃ ላይ መጓጓዣ፣ ጥንታዊ የአምልኮት ስርዓታት የመሳሰሉት ከጥንት ጀምሮ የናይል ስጦታዎች ነበሩ። በዚህ የተነሳ ናይል የዓለም ሥልጣኔ መነሻ ተብለው ከሚጠቀሱት ከጤግሮሰና ኤፍራጦስ፣ ከኢንዱስና ከሆዋንግሆ፣ ወዘተ. ሸለቆዎች ጋር ግንባር ቀደሙ ነው። በቅርብ ዘመናት አንፃርም፤ (1) የግብፅ አስዋን ግድብ ወይም የናስር ሐይቅና፣ በሰፊው የተንጣለለው የበረሃ መስኖ እርሻ (2) ከናይል ተጠልፎ በቀይ ባሕር ሥር በሰው ሠራሽ ቱቦ ተስቦ የሲና በረሃን የሚያጠጣው ውኃ፣ (3) ከአስዋን ግድብ ተጠልፎ ከዓባይ ሸለቆ ውጭ ያለውን የምዕራቡን የቶሽካ ሸለቆ የሚያጠጣው ውኃ፣ (4) በየዓመቱ በግብፅ እርሻዎችና ማሳዎች ጨውማ አፈር ለማጠብ የሚውለው ውኃ የናይል ስጦታ ነው። በሱዳን ከ1925 ጀምሮ የለሙት፣ የሴናርና የመናጂል የመስኖ ልማቶች፣ የሮሳሪስ ግድብና የመስኖ ልማት፣ የጀበል አውሊያ ግድብና የመስኖ ልማት፣ የካሽም ኤል-ግርባ ግድብና የመስኖ ልማት፣ የመሮዌ ግድብና የመስኖ ልማት፤ወዘተ.. ለሱዳን የናይል ስጦታዎች ናቸው። በዑጋንዳም የኦዌን ፏፏቴ ግድብና የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ የቡጃ ጋሊ ግድብ፣ የኤሌክትሪክ ኃይልና የመስኖ ልማት፤ወዘተ. በተመሳሳይ የናይል ስጦታዎች ናቸው። የታላቁ የቪክቶሪያ (ኒያንዛ) ሐይቅ ለታንዛኒያ፣ ለኬኒያና ለዑጋንዳ የማይነጥፍ የአሳ ሀብት ምንጭ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል። በኢትዮጵያ የጢስ ዓባይ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የፊንጫ ግድብ፣ የኤሌክትሪክ ኃይልና የመስኖ እርሻ ልማት፣ የጣና-በለስ የኤሌክትሪክ ኃይልና የመስኖ እርሻ፣ የተከዜ ግድብ የኤሌክትሪክ ኃይልና አነስተኛ የመስኖ ልማቶች፣ በባሮ ገባር ወንዝ በአልዌሮ

ወንዝ ላይ የተሰራው የአቦቦ ግድብ፣ በጣና ዙሪያ የተሰሩ የልማት ግድቦችና በዓባይ ተፋሰስ ውስጥ የታቀዱ የልማት ሥራዎች በሙሉ የኢትዮጵያ ናይል ስጦታዎች ናቸው። ከሁሉም በላይ ላቅ ብሎ የሚገኘው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ የዓባይ ተፋሰስ ትልቁ ፕሮጀክት ብቻ ሳይሆን በአሁን ሰዓት የናይል ሽለቆ ጂኦ-ፖለቲካ ትኩሳት መለኪያ ሆኗል።

## የናይል ጂኦ-ፖለቲካዊ ሚና

የናይል ወንዝ ለዘመናት ሲጠቀስና ሲወደስ የኖረ ነው። በቅርብ ጊዜ ታሪኩም አንፃር ሲታይ በርካታ ዓለም አቀፍ ትኩረቶችን መሳቡ ሊጠቀስ ይችላል። ለምሳሌ በ19ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ ጀምስ ብሩስ በምስራቁ ተፋሰስ አካባቢ ጆን ስፒክ በምድር ወገብ አካባቢ የናይልን መነሻ ፍለጋ በብርቱ ባዝነዋል። በየበኩላቸው የናይልን መነሻ አገኘን በማለት ፈንድቀዋል። በቅኝ ግዛት ዘመን ደግሞ እንደ ሎርድ ክትችነርና እንደ ቤኒቶ ሙሶሎኒ የመሳሰሉ ወራሪዎች የናይልን ተፋሰስ ለመቆጣጠርና ለመቀራመት ሞክረዋል፤ የተቻላቸውን ጥረትም አድርገዋል። እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ጣሊያን የመሳሰሉ ቅኝ ገዥ ሀገሮች በሰሜን ምስራቅ አፍሪቃ በያዟቸው ቅኝ ግዛቶቻቸው ትይዩ ያሉትን የናይልን ተፋሰስ ለመቆጣጠር ብዙ ለፍተዋል። ከኢትዮጵያው ተፋሰስ በስተቀር ሌሎቹ የናይል ተፋሰስ ሀገሮች በቅኝ ገዥዎች መዳፍ ሥር ከመውደቅ አላመለጡም። እንግሊዝ፣ ቤልጅየምና ጀርመን ዋናዎቹ የናይል ተፋሰስ ባለድርሻ ቅኝ ገዥዎች ነበሩ።

የቀዝቃዛው ጦርነት ዘመንም የናይልን ተፋሰስ ጉዳይ ከልዕለ ኃያላኑ መንግስታት እይታ አልወጣም ነበር። በዚህ ረገድ ሶቭየት ኅብረትና ዩናይትድ ስቴትስ ዋነኞቹ ነበሩ። በ1960ዎቹና በ1970ዎቹ ዓመታት ሶቭየት ኅብረት በግብፅ በኩል ዩናይትድ ስቴትስ ደግሞ በኢትዮጵያ በኩል ሆነው ለናይል ተፋሰስ የሰጡትን ትኩረት በግልፅ ማስተዋል ይቻል ነበር። በዚያን ዘመን ዝነኛ የነበሩት የኢትዮጵያና የግብፅ መሪዎችም በናይል ጉዳይ ተፅዕኖ ፈጣሪና ተፃራሪ ፖሊሲዎች ነበሯቸው። የኢትዮጵያ መሪ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የናይልን ውኃ ለእህትማማችነት፣ ለትብብርና ለጋራ ብልጽግና ይዋል ሲሉ ተከራክረዋል። የግብፅ መሪ ፕሬዜዳንት አብዱል ጋማል ናስር በተፃራሪ የናይልን ውኃ መዳረሻው ላይ በመከተር በሞኖፖል ለመጠቀምና ለመቆጣጠር ተግተዋል። የሁለቱ መሪዎች ሀሳቦች እስከዛሬም በሀገራቱ ፖሊሲዎች በውርስ እየወረደ የዘለቀና በቅብብሎሽ በወራሾቻቸው መካከል የብሔራዊ ጥቅም ግጭትና የጭቅጭቅ መንስኤ ሆኖ ቀጥሏል።

የጥንቱ፣ የቅርቡና ያሁን ዘመን ጸሐፍትና ባለቅኔዎች ስለ ናይል ታላቅነትና አቃፊነት ምጡቅ ሐሳባቸውን አስቀምጠዋል። የጥንቱ ዘመን ጸሐፊ ሔሮዶቱስ “ናይል ከሌለ ግብፅ የለችም” ሲል ዓባይ እና ተጓዳኝ የኢትዮጵያ ጅረቶች ባይኖሩ ደግሞ ናይል እንደማይኖር ተገንዝቦ ነበር ወይ ያሰኛል። ኤሚል ሉድዊግ “በኢትዮጵያ ሰማይ የሚጮህ ነጎድጓድ

የግብፅን ፌላዎች (ገበሬዎች) በተስፋ የሚያስፈነድቅ ነው" ሲል የናይል ምንጭና የውኃ መዳረሻ የተያያዙ መሆናቸውን መግለጹ ነበር። ሼይክ አንታ ዲዮጵ "በምድር ወገብ አካባቢ የሚዘንብ ዝናብ ባይኖር ኖሮ በግብፅ በረሃ አንድ ጠብታ ውኃ እንኳን አይኖርም ነበር" ሲል የናይል ውኃ የተፋሰሱን ምንጭና ጫፍ ማያያዣ ኃይል መሆኑን ማስረዳቱ ነበር። ሎሬት ባለቅኔ ፀጋዬ ገብረመድህን "ዓባይ የጥቁር ሕዝብ ምንጭ፣ የኢትዮጵያ ደም፣ የኩሽ እናት፣ የሥልጣኔ አማጭ" ሲል ናይል የሁሉም አለኝታ የሁሉም መመኪያ ለሁሉም የሚበቃ ስጦታ መሆኑን መግለጹ ነበር። ኃይሉ ገብረዮሐንስ ‹‹እናትክን በሉልኝ›› በተባለ መጽሐፉ "ዓባይ ከልማት ውጭ ሥራ-ፈት ነው፣ ዕውቀትና ዘዴ ተፈልጎ በትብብርና በኅብረት ቢለማ ለሁሉም ይበቃል" ብሎ ነበር። የናይል ልማት ኅብረትን ይሻል ማለቱ ነበር። ዝነኛዋ የአርት ሰው እጅጋየሁ ሽባባው ስለዓባይ ስታቀነቅን፡- "ዓባይ ለጋሱ የማያልቅ ፀጋው፣ የማይረግፍ ውበቱ፣ የሚበላው እሱ፣ የሚጠጣውም እሱ" ብላ በማዜም ዓባይ ከሕይወታችን ጋር ምንኛ መጣመሩን ገልጻለች።

## የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በዓባይ ውኃ

በዓባይ ውኃ ጂኦ-ፖለቲካዊ ጠቀሜታ የተነሳ ኢትዮጵያ የሚደርስባትን ጫናና ተፅዕኖ ስትጋፈጥ ኖራለች። በተለይ በዓባይ ጉዳይ ከተለያዩ ኃይሎች ለተነሱባት ጫናዎች ሳትበገር እንደየወቅቱ በፖሊሲም በዲፕሎማሲም የተደገፈ ምላሽ ስትሰጥ ቆይታለች። ለምሳሌ፡-

1. በ1902 አፄ ምኒልክ ከብሪታኒያ ጋር ያደረጉት ስምምነት ሊጠቀስ ይችላል። ስምምነቱ እንዲህ የሚል ነበር። *"ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፣ ከጥቁር ዓባይ ና ከባሕረፃና ከሶባት ወንዝ ወደነጭ ዓባይ የሚወርደውን ውኃ ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር አስቀድሞ ሳይስማሙ ወንዝ ተዳር እዳር የሚደፍን ሥራ እንዳይሰሩ። ወይም ወንዝ የሚደፍን ሥራ ለመሥራት ለማንም ፈቃድ እንዳይሰጡ በዚህ ውል አድርገዋል።"* በመሠረቱ ስምምነቱ ብሪታኒያ በቅርቡ በቅኝ ግዛትነት በያዘችው ጎረቤት ሀገር ሱዳንና በኢትዮጵያ መካከል ድንበር ለመካለልና የገበያ ሥፍራና መናኸሪያ ኪራይን የሚመለከት ነበር። የሆነ ሆኖ ኢትዮጵያ ወደ ሱዳን የሚፈሱ ወንዞችን ከዳር እስከዳር ደፍና የውኃውን ፍሰት አግዳ አታውቅም። ለወደፊትም ውኃ አፍና አታስቀርም። ታችኞቹ ሀገሮች ይህን ውል በተሳሳተ መንገድ በመተርጎም ኢትዮጵያ ውኃዋን ላለማልማት ተስማምታለች፤ ወይም ማልማት ስትሻም የታችኞቹን ሀገሮች ማስፈቀድ ይኖርባታል ሲሉ ይከራከራሉ። የስምምነቱ ትክክለኛ መንፈስና ትርጉም ኢትዮጵያ ወደ ጎረቤት ሱዳን ውኃ እንዳይፈስ አላግድም የሚል እንጂ በወንዞቿ ላይ ልማት አላካሂድም የሚል አልነበረም። እስከዛሬም ኢትዮጵያ ወደሱዳን በሚፈሱ ወንዞቿ ላይ ግድቦችን እየሰራች የመስኖ እርሻና የኤሌክትሪክ ኃይል ስታከናውን ኖራለች። በዚህም መሠረት በፊንጫ፣ በተከዜ፣ በባሮ አቆቦ፣ በጣና በለስ፣ በጣና ሐይቅ፣ በዓባይ እና በገባሮቹ ላይ

በርካታ የልማት ሥራዎች ተካሂደዋል። ወደ ሱዳን የሚፈሰው ውኃ ፍሰቱን አላቆመም። ለወደፊትም ውኃው ኢትዮጵያን እያለማ ወደ ሱዳን ፍሰቱን ይቀጥላል። ይህ አካሄድ በዘላቂና በተገቢ ሁኔታ እንዲቀጥል ሱዳንና ግብፅ ከኢትዮጵያ ጋር መተባበር ይጠበቅባቸዋል።

2. በ1906 ብሪታኒያ፣ ፈረንሳይና ጣሊያን ኢትዮጵያን በስውር ለመከፋፈል ባደረጉት ምስጢራዊ ስምምነት የዓባይን ተፋሰስ በብሪታኒያ የእጅ አዙር ቁጥጥር ስር ለማድረግ ያሰቡትን ሴራ ኢትዮጵያ በሰማች ጊዜ ለጉዳዩ እጅግም ቁብ ሳትሰጥ፤ የኢትዮጵያ ጉዳይ የማይመለከታቸው መሆኑን በማስገንዘብ፤ የቅኝ ገዥዎቹ ምኞት እንዲከሽፍ አድርጋለች።

3. በተመሳሳይ ሁኔታ በ1925 ብሪታኒያና ጣሊያን በስውር ቃል ኪዳናቸው በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ላይ ሴራ ጎንጉነው ሲያበቁ ጣሊያን ከኤርትራ ቅኝ ግዛቷ እስከ ሱማሊያ ግዛቷ ድረስ ኢትዮጵያን ሰንጥቆ የሚያልፍ የባቡር መንገድ እንድትሰራ የእንግሊዝ መንግስት ሲስማማላት፤ በአጸፋው ጣልያንም የእንግሊዝ መንግስት በኢትዮጵያ ዓባይ ተፋሰስ ላይ የተመኘችውን የእጅ አዙር የበላይነትን አውቃላት ነበር። ብዙም ሳይቆይ ሴራው ከሸፈ። ሁለቱም መንግስታት የተመኙትን ሳያገኙ ቀርተዋል።

4. በ1956 ነፃነቷን የተጎናጸፈችው ሱዳንና የቀድሞ ጥምር ቅኝ ገዥዋ የነበረችው ግብፅ በናይል ላይ አዲስ ድርድር በምስጢር መጀመራቸው ስለተደረሰበት የኢትዮጵያ መንግስት በ1957 ባስተላለፈው ‹‹ኤይድ ሜሙዋር›› በተሰኘው መንግስታዊ መግለጫ ለሱዳንና ለግብፅ መንግስታት ጠንካራ ተቃውሞ አስተላልፏል። እያደገ ለሚሄደው የሕዝቧ ቁጥርና ለኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ልማትና ብልጽግና ሲባል የኢትዮጵያ መንግስት በግዛቱ ክልል የሚገኘውን የውኃ ሀብት የማልማት መብቱ ምን ጊዜም ቢሆን የተረጋገጠ መሆኑን የግብፅና የሱዳን መንግስታት እንዲያውቁት ተነግሯቸዋል። ኢትዮጵያ በወንዞቿ ላይ የምታካሂደው ልማት ይህንን መርህ የተከተለ ነው።

5. ግብፅና ሱዳን ኢትዮጵያን አግልለው፣ በተጨማሪም ገና ከቅኝ ግዛት ነፃ ላልወጡ የናይል ተፋሰስ ውኃ አመንጪ ሀገሮች ምንም ደንታ ሳይኖራቸው የናይልን ውኃ ሙሉ በሙሉ የመከፋፈል ስምምነት በ1959 ተፈራረሙ። ያንን ስምምነት ኢትዮጵያ የማታውቀው ወይም የማትቀበለው ብቻ ሳይሆን ስምምነቱ የተሳሳተና ህገ-ወጥ መሆኑን አስገነዝባለች። እነሆ ያ ስምምነት ኖረም አልኖረም ኢትዮጵያን ስለማይመለከታት በውኃ ሀብቶቿ ላይ እንደአስፈላጊነቱ ልማት ስታካሂድ ቆይታለች። ለዚህም ቀደም ሲል ከተጠቀሱት በተጨማሪ የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ፕሮጀክትም አንዱ ማሳያ ነው።

6. ቀደም ሲልም ከ1958 እስከ 1964 ባሉት ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ መንግስት ከዩ ኤስ አሜሪካ ቢሮ ኦፍ ሪክላሜሽን (US America Bureau of Reclamation) ጋር በመቀናጀት የዓባይ ተፋሰስን ለማልማት ቆርጦ ተነሥቶ እንደነበር ይታወቃል። ሠላሳ ሦስት የሚሆኑ የልማት ፕሮጀክቶች ተለይተው ለተለያዩ የልማት ሥራዎች መዘጋጀታቸው ኢትዮጵያ በወንዞቿና በገባሮቻቸው ላይ ልማት የማካሄድ መብቷን ለመጠቀም ከልካይ እንደማይኖራት የሚያረጋግጥ ነው። የዛሬው የሕዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ተሻሽሎ የቀረበ ቢሆንም መሠረቱና መነሻው በ1958-64 ተጠንተው ከነበሩ የልማት ፕሮጀክቶች ውስጥ አንዱ ነው። ቀደም ሲል የወሰን ላይ ግድብ፣ ፕሮጀክት X (ኤክስ)፣ ሚልኒየም ግድብ ሲባል ቆይቶ በስተመጨረሻው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ፕሮጀክት በሚል ሲገነባ ቆይቶ እነሆ ዛሬ ግድቡ ለመጀመሪያው የውኃ ሙሌት እየተቃረበ ይገኛል።

7. በ1977 በማር ዴል ፕላታ በተደረገው የተባበሩት መንግስታት የውኃ ኮንፈረንስ ላይ ኢትዮጵያ የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ልማት መካሄድ ያለበት ውኃ በሚጋሩ ሀገሮች መካከል በሚደረግ ስምምነት እንጂ ቀደም ሲል በአንዳንድ ሀገሮች የግል ጥቅምና መብት ለመጠቅለል በተደረጉ ውሎች ተመሥርቶ መሆን የለበትም ስትል ተከራክራለች። የዚህ ክርክር ሀሳብ አድጎና ውኃ ቋጥሮ የናይል ተፋሰስ ሀገሮች ከ1999 ጀምሮ በናይል ተፋሰስ ኢኒሼቲቭ (Nile Basine Initiative-NBI) እና በትብብር ማዕቀፍ ስምምነት (Cooperation Framework-CFA) ደረጃ አድጎ ይገኛል። ከኢትዮጵያ አልፎ ለሁሉም የናይል ውኃ አመንጪ አገሮች የትብብርና የመደራደሪያ ሀሳብ መሠረት ሆኖ እየሠራ ነው።

8. ከ1993 እስከ 2002 በየዓመቱ ‹‹ናይል 2002 ኮንፈረንስ›› በሚል ማዕቀፍ ሲካሄዱ በነበሩ ኮንፈረንሶች ላይ በኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወገን በሆኑ ምሁራንና የሥራ ኃላፊዎች ይቀርቡ የነበሩ የምርምር ግኝቶችና የውይይት ሀሳቦች፣ ለኢትዮጵያም ሆነ ለሌሎች የተፋሰሱ ሀገሮች የትብብርና የጋራ ልማት አስፈላጊነትን የሚያቀነቅኑ ነበሩ። ኢትዮጵያ ሁለት ኮንፈረንሶችን ያዘጋጀች ሲሆን በሁሉም ኮንፈረንሶች በአማካሪነት በንቁ ተሳታፊነት ተገኝታለች። በኮንፍራንሶቹ ላይ የመንግስታቱ ተወካዮች የየሀገሮቻቸውን አቋም ሲያንፀባርቁ ምሁራኑ ደግሞ በምርምር ግኝት ላይ የተመሠረቱና በድንበር ተሻጋሪ ውኃዎች ላይ ስለሚጠበቁ የትብብርና የስምምነት ጉዳዮች ሀሳባቸውን እያቀረቡ ተከራክረዋል። በኮንፈረንሱ ሂደት የናይልን ወንዝ ጨምሮ ድንበር ተሻጋሪ ውኃዎች በስምምነት ላይ የተመሠረተ ተቋማዊ ማዕቀፍ ተበጅቶላቸው ሀገራቱ የጋራ ውኃ ሀብታቸውን በተመዛዘነና በፍትሐዊ መንገድ የማልማት አስፈላጊነት አማራጭ የሌለው መሆኑን አፅንኦት ሰጥተው ተወያይተውበታል።

9. የናይል ተፋሰስ ኢኒሼቲቭ (NBI) በደጋፊ ዓለም መንግስታትና በልማት ድርጅቶች ታግዞ በናይል ተፋሰስ ሀገራት መካከል የጋራ ዕይታና የልማት ትብብር እንዲጀመር ስምምነት ላይ ተደርሶ ነበር። በዚህ መሠረት ሁሉም የናይል መንግስታት የተሳተፉበት ሂደት ከ1999 እስከ 2010 ተካሂዷል። ግብፅ ከማዕቀፉ አፈንግጣ ብትወጣም ሌሎች የናይል ተጋሪዎች እስካሁን ቀጥለውበታል።

10. ከዚህ ሂደት ጎን ለጎን የተፋሰሱ ሀገራት ለትብብር ማዕቀፍ ስምምነት (CFA) በብርቱ ተደራድረዋል። ከአስራ አንድ ዓመት ድርድር በኋላ የስምምነቱ ሠነድ ተጠቃልሎ ሰባት መንግስታት ይሁንታ ሰጥተውት፣ ስድስት መንግስታት በ2010 ፊርማቸውን አኑረዋል። ግብፅና ሱዳን አፈንግጠው ፊርማቸውን ሳያኖሩ ከስምምነቱ ሂደት ወጥተዋል። ዋና ምክንያታቸው የትብብር ማዕቀፉ ስምምነት የናይልን ውኃ ለብቻችን የመጠቀም ታሪካዊ መብታችንን አላረጋገጠልንም የሚል ነበር። እስከናካቴው ሁለቱ ሀገሮች ከናይል ተፋሰስ ኢኒሼቲቭም መውጣታቸውን አወጀው ነበር። ግብፅ እንደወጣች ስትቀር ሱዳን አስፈቅዳ ወደ ኢኒሼቲቩ ተመልሳ ገብታለች። በማዕቀፍ ስምምነቱ ሠነድ መሠረት በድርድሩ ከተሳተፉበት ዘጠኝ ሀገሮች መካከል ስድስቱ ስምምነቱን በማጽደቅ የየሀገራቸው የሕግ አካል ሲያደርጉት የስምምነት ሠነዱ በአፍሪቃ ኅብረት ይመዘገባል። በዚህም በሁለት ሦስተኛ የተደራዳሪ ሀገሮች ፍላጎት ላይ ተንተርሶ የናይል ተፋሰስ ኮሚሽን ይቋቋማል ማለት ነው። ኮሚሽኑ በስምምነቱ ሠነድ ላይ በሰፈረው አግባብ የናይል ውኃ አጠቃቀም፣ አጠባበቅና እንክብካቤ በምን ሥርዓት እንደሚተዳደር ይከታተላል። እስካሁን የትብብር ማዕቀፍ ስምምነቱን ያጸደቁ ሀገሮች ኢትዮጵያ፣ ሩዋንዳ፣ ታንዛኒያና ዑጋንዳ ሲሆኑ ኬንያና ቡሩንዲ ገና ይጠበቃሉ። የሆነ ሆኖ፣ ኮሚሽኑ ገና ባይቋቋምም የናይልን ውኃ የታችኞቹ ሁለት ሀገሮች፤ ማለትም ግብፅና ሱዳን በሞኖፖል የሚቆጣጠሩበት ፍላጎት ተቀባይነት እንደማይኖረው የትብብር ማዕቀፍ ስምምነቱ አረጋግጧል። ሁሉም ፈራሚ ሀገሮች ስምምነቱን አጽድቀው ኮሚሽኑ ቢቋቋም፣ ወይም ቢዘገይ፣ ወይም ሳይቋቋም ቢቀር እንኳን እያንዳንዱ የተፋሰሱ ሀገር በግዛቱ ክልል ውስጥ ያለውን የናይልን ውኃ በሌሎች የተፋሰሱ ሀገሮች ላይ በከፋ መልኩ ጉዳት ሳያደርስ ከመጠቀም ሊታገድ አይችልም። ኢትዮጵያ የሕዳሴ ግድብና ሌሎች የውኃ ልማቶችን እያካሄደች ያለችው በዚህ መርህና ትንታኔ ላይ ተንተርሳ ነው።

## ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ የኢትዮጵያ የውኃ ፖሊሲ መፈተሻ

መጋቢት 24 ቀን 2003 የሕዳሴ ግድብ መሠረት ሲጣል ብዙ ወገኖች ለማመን ተቸግረው ነበር። በተለይ ግብፅና ሱዳን በእጅጉ ተበሳጭተዋል። ይህም የሆነው በተለይ ግብፅ በዓባይ ወንዝና በሌሎች የናይል ወንዞችና በገባሮቻቸው ላይ ያለርሷ ፈቃድ ግድብ መስራትም ሆነ

የረባ የውኃ ልማት ማካሄድ የማይታሰብ ነው ብላ ስለምታስብ ነው። ሱዳን በበኩሏ ከሁሉ አስቀድሞ ኢትዮጵያ የጀመረችው ግዙፍ ግድብ የተናደ እንደሆነ ካርቱምን ጨምሮ ዋና ዋና ከተሞቿንና የውኃ ግድቦቿን ጠራርጎ ያወድማቸዋል ብላ በመስጋት ነበር። ሌሎች የናይል ተፋሰስ ሀገሮች በግድቡ የተነሳ ኢትዮጵያና ግብፅ ይጋጩ ይሆናል ብለው በማሰብ ጉዳዩን በአግራሞት ነበር የተመለከቱት። ገሚሶቹ ደግሞ ኢትዮጵያ በዓለም ባንክ መመሪያ 07 የተነሳ የብድር ድጋፍ ስለማታገኝ ይህን ግዙፍ ግድብ የመስራት አቅም አይኖራትም ብለው ደምድመዋል።

የዐረብ ሀገሮች በበኩላቸው ወገናችን የሚሏት ግብፅ ታሪካዊ የውኃ መብቷ መነካት የለበትም በማለት የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ፕሮጀክትን አናንቀው ተችተዋል። የተቀረው የዓለም ማህበረሰብ በበኩሉ ኢትዮጵያ ይህን ግድብ ለመስራት አቅሙም ብቃቱም ስለማይኖራት ውሳኔው የምር ሳይሆን የላንቲካ ነው በማለት በሹክሹክታና በአሽሙር መስመር መላላክ ላይ አተኩረው ነበር። ለዚህም ሁለት ዋና ምክንያቶችን አጉልተው ይገልጹ ነበር። የመጀመሪያው ግድቡ እንደ ዕድል ቢሰራ እንኳ 74 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ውኃ ስለሚያስቀር ግብፅ በድርቅ ትመታለች፤ መዘዙም ግጭት ሊያመጣ ይችላል ብለው ስጋታቸውን ይገልጹ ነበር። ሁለተኛው ግብፅ ግድቡን ከመነሻውም ስለማትፈቅድ ግድቡ የማይሰራ ወሬ ነው ብለው ደምድመዋል።

የኢትዮጵያ ህብረተሰብ የግድቡን መጀመር በተቀላቀለ ስሜት ነበር ያስተናገደው። ባንድ ወገን ኢትዮጵያ ግድቡን ለመስራት መወሰኗ የቁርጠኝነትና የደፋርነት ውሳኔ ብቻ ሳይሆን የልማት ተስፋ የጫረና ለዘመናት ቁጭት ምላሽ ነው በማለት ፈጣን ድጋፍ የሰጡ በርካታ ናቸው። በሌላ ወገን የወቅቱ አገዛዝ ከአገሪቱ አቅም በላይ የሆነ ግድብ መጀመር ዝናና የፖለቲካ ድጋፍ ለማጋበስ እንጂ የውኃ ልማት ስትራቴጂ ያልተከተለና መዘዙ ከግብፅ ጋር ያላስፈላጊ ግጭት የሚጋብዝ የግድብ ስራ ነው በማለት ስጋታቸውን ሲገልጹ የነበሩ ወገኖች መኖራቸው ተስተውሏል።

## ዓለም አቀፍ የኤክስፔርቶች ፓነል (IPOE) መሰየም

የኢትዮጵያ መንግስት በበኩሉ ግድቡ በጥንቃቄና በብቃት ታቅዶ እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥና ለሁሉም ወገኖች ምላሽ እንዲሆን፤ በተለይ የግብፅንና የሱዳንን ስጋት ለማረጋጋት፤ የግድቡን አስተማማኝነት መርምሮ የሚያረጋግጥ ገለልተኛ ዓለም አቀፍ የኤክስፐርቶች ፓነል (International Panel of Experts – IPOE) እንዲሰየምና የግብፅ፣ የኢትዮጵያና የሱዳን ኤክስፐርቶችም አብረው በጋራ ሆነው እንዲመረምሩ ሀሳብ አቀርቦ፣ ሀሳቡ በግብፅና በሱዳን ወገኖች ተቀባይነት አገኘ። በዚህ መሠረት፣ በሀይድሮሎጂ፣ በኢንቫይሮንሜንት፣ በሶስዮ-ኢኮኖሚና በግድብ አሰራር ዕውቀትና ብቁ የሥራ ልምድ

ያላቸው ኤክስፐርቶች በሶስትዮሽ ስምምነት በተዘጋጀው የተግባር መመሪያ መሠረትና በዓለም አቀፍ ውድድር አሰራር ተመዝነው በጋራ ተቀጠሩ። የግብፅ፣ የኢትዮጵያና የሱዳን ኤክስፐርቶች በየሀገሮቹ ተመድበው ለዓለም አቀፉ ፓነል በባልደረባነት እንዲሰሩና የየሀገራቸውን እይታ እያቀረቡ የፓነሉን ስራ እንዲከታተሉ ተደርጓል።

ከ2012 እስከ 2013 በተካሄደው የፓነሉ የምርመራ ስራ ወቅት፣ ኢትዮጵያ የጀመረችው የግድብ ስራ በተገቢ ጥናትና ዲዛይን ላይ የተመሠረተ መሆኑን የሚያስረዱ 153 ሠነዶች ለፓነሉ ቀርበው ተመርምረዋል። የፓነሉ አባላት በግድቡ ሳይት ላይ በመገኘት በቂ ጊዜ ወስደውና እንደ የአስፈላጊነቱ ተመላልሰው የመስክ ጥናት አድርገዋል። በዚህ መልኩ ጥናቱ ተጠናቅቆ የፓነሉ ሪፖርት ለሶስቱም መንግስታት በተመሳሳይ ቀን (May 30, 2013) ቀርቧል። በሪፖርቱ ሠነድ ላይ የፓነሉ ዓለም አቀፍ ቡድን አባላትና ከሦስቱም ሀገሮች የተመደቡ ኤክስፐርቶች የማረጋገጫ ፊርማቸውን አኑረዋል። የፓነሉ የምርመራ ግኝት ያጠነጠነው በግድቡ የአሰራር ጥራትና ደኅንነት (Dam Safety) እና የግድቡ መኖር በአካባቢው ኢንቫይሮንሜንትና የማህበረሰቦች አኗኗር ላይ ሊያስከትል ስለሚችለው ማናቸውም ጫና ነበር። የግድቡ አሰራር ጥራት ዓለም አቀፍ የግድብ አሰራር ደንብና ጥራት የተከተለ መሆኑ በፓነሉ ሪፖርት ተረጋግጧል። ግድቡ ሲጠናቀቅ በኢንቫይሮንሜንትና በማኅበራዊአኗኗር ረገድ ሊያስከትል የሚችል ጫና መኖር አለመኖሩን ሦስቱ ሀገሮች በጋራ ሁነው በገለልተኛ ኤክስፐርት እያስጠኑ ማስተካከያዎችን እንዳስፈላጊነቱ በመተጋገዝ እንዲፈጸም የሚል ሀሳብ በሪፖርቱ ሰፍሯል።

በፓነሉ የቀረበውን ሪፖርት ሱዳንና ኢትዮጵያ ወዲያው ሲቀበሉ የግብፅ ወገን ላለመቀበል እያንገራገረ ሙሉ ዓመት ወስዶበታል። የግብፅ ወገን በፓነሉ ላይ በባልደረባነት የመደባቸውን ኤክስፐርቶች ከቀጣይ አገልግሎት ተገልለው እንዲባረሩ አድርጓል።

### ሦስትዮሽ ብሔራዊ ኮሚቴ (Tripartite National Committee-TNC) መቋቋም

በፓነሉ ምክረ-ሀሳብ ላይ ተንተርሶ ሦስቱ ሀገሮች በውኃ ሚኒስትሮቻቸው የሚመራ የሦስትዮሽ ብሔራዊ ኮሚቴ (Tripartite National Committee – TNC) ተቋቁሞ ተጨማሪ አስፈላጊ ጥናቶችን በጋራ ሆነው አማካሪ በመቅጠር ለማካሄድ እንቅስቃሴ ተጀምሮ ነበር። በዚህም መሠረት የኢንቫይሮንሜንትና ማኅበራዊአኗኗር ተፅዕኖ የሚያጠና አማካሪ ድርጅት ብዙ ጊዜ በፈጀ የምልመላና የቅጥር እሰጥ አገባ ተቀጥሮ ሥራውን የጀመረው በብዙ ተግዳሮት ነበር። የግብፅ ወገን ፍላጎት ተቀጣሪው ድርጅት የግብፅን "ታሪካዊ መብት" ጥያቄ የሚያስተናግድ፣ ቀደም ሲልም በግብፅ ውስጥ በአማካሪነት በመስራት የደንበኝነት ልምድ ያለው እንዲሆን ከመፈለግ ጋር የተቃኘ ነበር። የሆነ ሆኖ በብዙ የመረጣ ሂደት የተቀጠረው አማካሪ ድርጅት የመነሻ ሪፖርት (Inception Report) የግብፅን የእስካሁን

የውኃ የብቻ "ባለቤትነት መብት" መሠረት ያደረገ በመሆኑ በኢትዮጵያ በኩል ተቀባይነት ስላላገኘ የአማካሪው ጥናት እንዲቋረጥ ተደርጓል።

ይህ እንዲህ እንዳለ የግድቡ ስራ በኢትዮጵያ በኩል ጠንክሮ መቀጠሉ ግብፅን ይበልጥ እያሰጋ መጣ። የግድቡን ሥራ ለማስቆም ወይም ለማስተጓጎል በማሰብ ግብፅ ጉዳዩን ከቴክኒክ ደረጃ ወጥቶ ወደ ፖለቲካ ደረጃ እንዲሸጋገር የኢትዮጵያንና የሱዳንን መሪዎች በልመናና በጫና በማስቸገር፣ ከሁሉም በላይ የቴክኒክ ደረጃ ውይይትን በሆነ ባልሆነ ሰበብ (ለምሳሌ ቃለ ጉባኤዎችን ባለመፈረም፣ ስብሰባዎችን ባለመጨረስ፣ ወዘተ) በማስተጓጎል ጠቃሚ መድረክ እንዳይሆን ጥራለች። ግድቡን የሚያስቆም ሁኔታ ባይኖርም ለወቅቱ ዲፕሎማሲ ጥቅም ሲባል በሕዳሴ ግድብ ጉዳይ ላይ ለመደራደር ሦስቱ ሀገሮች መስማማት ነበረባቸው። የግብፅ ዕሳቤ ግድቡ የሚቆምበትን መንገድ ለመቀየስ ሲሆን የኢትዮጵያ ዕሳቤ ደግሞ ግድቡን እየሠራች መቀጠል የሚከለክላት ኃይል ስለማይኖር የፖለቲካ ድርድርም ቢሆን የኢትዮጵያ ጥቅም የሚጻረር ከሆነ መቆም የሚችል መሆኑን በመገንዘብ ለፖለቲካ ድርድሩ ዕድል ሰጥታለች። ሱዳን በጉዳዩ ላይ የጠበቀ አቋም ስላልነበራት ኢትዮጵያና ግብፅ የወሰኑትን ተቀብላለች።

## የመርህ መግለጫ (DOP) ስምምነት

ሦስቱ ሀገሮች በተስማሙበት መሠረት በኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ አሞላልና አስተዳደር ላይ ትኩረት ያደረገ ድርድር ተከፈተ። ስለግድቡ አሞላል፣ ስለግድቡ አስተዳደር፣ በግድቡ ዙሪያ ስለሚነሱ የጥቅም ግጭት አያያዝ እና አፈታት እና በመሳሰሉት ጉዳዮች ዙሪያ ዘላቂ የስምምነት ማዕቀፍ ለማበጀት በሚል ዓላማ ከታህሳስ 2014 እስከ መጋቢት 2015 በግብፅ፤ በኢትዮጵያ እና በሱዳን መካከል የሶስትዮሽ ድርድር ተካሂዷል። ድርድሩ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች የተመራና በውኃ ጉዳይ ሚኒስትሮች የታገዘ ሲሆን፤ ከየሙያው የተውጣጡ የተለያዩ ኤክስፐርቶችም ከሦስቱም ወገን ተሳትፈውበታል። በድርድሩ መነሻ ላይ ግብጾችና ኢትዮጵያውያኑ በመርህ ስምምነቱ ስያሜ ላይ መስማማት ነበረባቸው። የግብፅ ወገን የስምምነቱ ደረጃና ይዘት ከፍ ያለ ስለሆነ "በኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ (GERD) የሦስትዮሽ ውል (treaty)" እንዲባል ተከራክሯል። በኢትዮጵያ በኩል ደግሞ በናይል ተፋሰስ ሀገሮች መካከል የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት ቀደም ሲል የተፈረመ በመሆኑና (ግብፅና ሱዳን ረግጠው የወጡበት)፤ የአሁኑ ድርድር ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ብቻ የሚመለከት በመሆኑ፤ የግድቡ አሞላልና ቀጣይ አስተዳደር በግድቡ ባለቤት በኢትዮጵያ አማካይነት ሲካሄድ ሁለቱ የታችኞቹ ሀገሮች ማለትም ግብፅና ሱዳን ስጋት እንዳያድርባቸው ለማስተማመን ታስቦ በጋራ ከሚወጣ የመርህ መግለጫ ሊያልፍ አይገባውም የሚል ክርክር ቀርቧል። የኋላ ኋላ የስምምነቱ ደረጃና ስያሜ "የሕዳሴ ግድብ የመርህ መግለጫ" (Declaration of Principles – DoP) ብቻ በሚል እንዲጸድቅ ተደርጓል።

በመርህ መግለጫ ድርድር ወቅት ከሦስቱ ሀገሮች በተጨማሪ አራተኛ ወገን በታዛቢነት ያውም የዓለም ባንክ በታዛቢነት እንዲሰየምና፤ ሦስቱ ወገኖቹ ስምምነት ላይ በማይደርሱበት ወቅት ይህ በቋሚነት የሚሳተፈው አራተኛ ወገን ሀገሮቹን የማስማማት ሚና ይጫወታል በማለት ግብፅ በጽኑ ተከራክራለች። ኢትዮጵያና ሱዳን በመተጋገዝ ባቀረቡት ክርክር በሦስቱ ሉዓላዊ ሀገሮች መካከል ጉዳዩ በቀጥታ የማይመለከተውን ሌላ ሀገር ወይም ድርጅት በቋሚነት ማስገባት ትክክል አለመሆኑን አስረግጠው በዚሁ መሠረት የግብፅ ወገን የቀረበው ሀሳብ እንዲቀር ተደርጓል። በአንጻሩ ክርክር ያጋጠመ እንደሆነና ለጉዳዩ የሦስተኛ ወገን አስታራቂነት ወይም አደራዳሪነት ሲያስፈልግ እንደሁኔታው የማስገባት አንቀጽ ማካተት እንደሚቻል በመስማማት ክርክሩ ተቋጭቷል። ይኸው ሀሳብ የመርህ መግለጫ ስምምነቱ 10ኛ አንቀጽ ሆኖ እንዲገባ ተደርጓል።

የሦስትዮሹ ድርድር ተቋጭቶ በአስር መርሆች ላይ የተመሠረተ ‹‹በግብፅ አረብ ሪፐብሊክ፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ እና በሱዳን ሪፐብሊክ መካከል የተደረገ የመርሕ መግለጫ›› (Agreement on Declaration of Principles between the Arab Republic of Egypt, the Federal Democratic Republic of Ethiopia and The Republic of the Sudan) የተባለ ስምምነት በካርቱም ከተማ በሦስቱም መንግስታት መሪዎች መጋቢት 16 ቀን 2015 ዓ.ም (ማርች 23 ቀን 2015) ተፈርሟል። ይህ የስምምነት ሠነድ አስር መርሆዎችን የያዘ ሲሆን ፍትሀዊና ምክንያታዊ የውኃ አጠቃቀም መርህን ያካተተ አንቀጽም አለው።

የውኃ ጉዳይን በተመለከተ ግብፅና ኢትዮጵያ በጋራ የፈረሙት የመጀመሪያው ሠነድም ነው። ከሁሉ በላይ ግብፅ የጋራ የውኃ ሀብትን በፍትሀዊና ምክንያታዊ መርህ መሠረት ከሌሎች የውኃ ተጋሪ ሀገሮች ጋር በትብብር ለመንቀሳቀስ ፊርማ ያኖረችበት የመጀመሪያው የስምምነት ሠነድ ይህ የመርህ ስምምነት ሠነድ ብቻ ነው። በዚህ የስምምነት ሠነድ በተዘረዘረው መሠረት የግድቡ አሞላልና አስተዳደር ሁኔታን ጨምሮ፣ ስለግድቡ ኢንቫይሮንሜንትና ማኀበራዊ አኗኗር ተፅዕኖ አጥንቶ ሀሳብ የሚያቀርብ አማካሪ ድርጅት ቀጥሮ የማሰራቱ ጉዳይ በሚጋጩ ፍላጎቶች (conflict of interest) የተነሳ አዳጋች ሆኖ ቀጥሏል። ይህን ችግር ለመፍታት ከሦስቱም ሀገሮች በተውጣጡ የውጭ ጉዳይ፣ የውኃ ሀብትና የደኅንነት ሚኒስትሮች በጋራ ተመክሮ መላ ይፈለግለት በሚል በግብፅ በኩል በቀረበ ሀሳብ መሠረት የዘጠኝዮሽ ድርድር ለተወሰነ ጊዜ ተካሂዶ ነበር። ዞሮ ዞሮ፣ በተለይ ኢትዮጵያና ግብፅ ብሔራዊ ጥቅማቸውን በቀይ አስምረው ስለሚንቀሳቀሱ፤ የግብፅ ወገን የግድቡ አሞላልና የአስተዳደሩ ጉዳይ በፈለገው መንገድ ሊሄድለት ስላልቻለ ጉዳዩ ስምምነት ሊያገኝ አልቻለም።

ኢትዮጵያ የግድቧን ሥራ ሳታቋርጥ በመቀጠሏ ለግብፅ ወገን ስጋት ሆኖ ቀጥሏል። ከዚህ አዙሪት ለመውጣት ተብሎ ሲካሄድ የነበረው የዘጠኝዮሽ ምክክርም ቢሆን መፍትሔ

አላስገኘም። ጉዳዩ አሁንም በትክክለኛው መንገድ ከታየ የቴክኒክ በመሆኑ ከሦስቱም ሀገሮች አምስት አምስት ብሔራዊ ገለልተኛ ሳይንቲፊክ የጥናት ቡድን (National Independent Scientific Research Group – NISRG) እንዲቋቋምና ጉዳዩን የቴክኒክ ሙያ በሚመራው መንገድ እንዲጠና በዘጠኝዮሹ መድረክ ተወሰነ።

በመሆኑም በሦስቱ ሀገራት ተመርጦ የተመደበው NISRG የመጨረሻ የጋራ የቴክኒክ ጥናት ውጤቱን በአምስት ተከታታይ የጋራ ስብሰባዎች አማካይነት አጠናቅቆ በጋራ የደረሰበትን ውጤት ለውኃ ጉዳይ ሚኒስትሮች እንዲያቀርብ ተወሰነ። በዚሁ መሠረት ከግንቦት እስከ ነሐሴ 2018 ባለው ጊዜ ውስጥ NISRG የጋራ ጥናቱን አጠናቅቆ ለሦስቱ የውኃ ሚኒስትሮች አቅርቧል። በመስከረም ወር 2018 የሦስትዮሽ የውኃ ጉዳይ ሚኒስትሮችና ልዑካኖቻቸው ውይይት አድርገውበታል። የኢትዮጵያና የሱዳን ሚኒስትሮች በተካሄደው የውይይት ምክረ ሀሳብን ጨምሮ በተዘጋጀው ቃለ-ጉባኤ ላይ ሲፈርሙ የግብጹ የውኃ ሚኒስትር አለቆቼን አማክሬ እፈርማለሁ የሚል ሰበብ ፈጥረው ልዑካቸውን ይዘው ወደሀገራቸው ተመልሰዋል።

ከድፍን አንድ ዓመት በኋላ፣ ማለትም በነሐሴ ወር 2019 ላይ የግብፅ ወገን NISRG አጥንቶ ያቀረበውን ምክረ ሀሳብ ወደጎን በመተው አዲስ የስምምነት ሠነድ አቀረበ። ሠነዱ በአንድ ሀገር ብቻ ተረቅቆ የቀረበ ብቻ ሳይሆን የNISRGን የጋራ የቴክኒክ ጥናትና የስምምነት ሀሳብ እስከናካቴው በመተው፤ ግብፅ በጥቅሉም በዝርዝሩም ታሪካዊ የውኃ ባለቤትነት መብቴ የምትለውንና ኢትዮጵያ ልትቀበለው የማትችለውን የስምምነት ሀሳብ ይዛ ብቅ አለች።

ግብፅ ለብቻዋ አርቅቃ ለስምምነት ያቀረበችው ሀሳብ ተቀባይነት ቢያገኝ ኖሮ፤ የመጀመሪያ ነገር፣ ኢትዮጵያ የሕዳሴ ግድቧን መሙላት አትችልም ማለት ነው። ከዚያም አልፎ በግዛቷ ውስጥ የውኃ ልማት ለማካሄድ ባሰበችና ባቀደች ቁጥር ግብፅን ማስፈቀድ ሊኖርባት ነው። ይህ የግብፅ አካሄድ "ዐይናችሁን ጨፍኑ እስኪ ላሞኛችሁ" አይነት የብልጣ ብልጥ ጨዋታ ይመስላል።

የሆነ ሆኖ አዲሱ በግብፅ የቀረበው የስምምነት ረቂቅ በሁለት ቁልፍ ምክንቶች በኢትዮጵያ ወገን ተቀባይነት አጥቷል። የመጀመሪያ ነገር፣ የጋራ ስምምነት የሚደረሰው በሦስትዮሽ ሳይንትፊክ ቡድን ማለትም በNISRG ቀርቦ ውይይት ተደርጎበትና በጥንቃቄ ተበጥሮና ተነቅሶ ነው እንጂ ባንድ ወገን ብቻ ተዘጋጅቶ በሚቀርብና ሀሳብና ሀሳቡንም በሌሎች ሀገሮች ላይ በመጫን አይደለም። በሁለተኛ ደረጃ "አዲስ ስምምነት" ብላ ግብፅ ያቀረበችው የስምምነት ሠነድ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅምና ሉዓላዊ መብት የሚጋፋ በመሆኑ ተቀባይነት አጥቷል። ግብፅ ባቀረበችው የስምምነት ሠነድ መሠረት ከተሄደ ኢትዮጵያ በዓመት 40 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ውኃ ለግብፅ ትለቃለች፣ የኢትዮጵያ የግድብ አሞላልና የውኃ አጠቃቀም የግብፅ አስዋን ግድብ ከባህር ጠለል በላይ ከ165 ሜትር እንዳይጎድል ኃላፊነት

ትወስዳለች፤ የግድቡ ሙሌትም ከ12 እስከ 20 ዓመት መውሰድ ይኖርበታል። አልፎ ተርፎም የግድብ መቆጣጠሪያ የጋራ ጽ/ቤት ሕዳሴ ግድብ በሚገኝበት ስፍራ እንዲሆን ይደረጋል የሚሉ ድንጋጌዎችን የያዘ በመሆኑ በኢትዮጵያ በኩል ጨርሶውኑ ተቀባይነት አጥቷል። ደግነቱ ግብፅ ያቀረበችውን የስምምነት ሀሳብን ሱዳንም አልተቀበለችውም።

## የሕዳሴ ግድብ ድርድር ውስብስቡ ምዕራፍ

ግብፅ ከሦስትዮሽ መድረክ በቀጥታ ድርድር የፈለገችውን ማግኘት የማትችል መሆኑን ተገንዝባለች። በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ግድብ ቀን ተሌት እየተሰራ የመጀመሪያ ሙሌት የሚከናወንበት ጊዜ እየተቃረበ መምጣቱ ለግብፅ ወገን የጉሮሮ አጥንት ሆኖበታል። የግብፅን ሐሳብ ለማስለወጥና ቀጣዩ ውይይት NISRG ባቀረበው ሳይንሳዊ መሠረት ባለው መስመር ለማስኬድ በተደረገው ጥረት፣ ከሴፕቴምበር 15-16 ቀን 2019 በካይሮ፣ ከሴፕቴምበር 30 እስከ ኦክቶበር 5 ቀን 2019 በካርቱም በሦስትዮሽ የውኃ ሀብት ሚኒስትሮች መካከል የሚያስማሙና የማያስማሙ ነጥቦችን ለመለየት የተደረጉ ተጨማሪ ስብሰባዎች ያለውጤት ተጠናቅቀዋል።

ይህ እንዲህ እንዳለ በግብፅ መንግስት አማላይነት የአሜሪካ አስተዳደር “ለመስማማት ስለተቸገራችሁና በመካከላችሁ ግጭት እየሰፋ ሌላ ችግር ከሚፈጥርባችሁ በታዛቢነት በመካከላችሁ ተገኝቼ ጉዳያችሁን በትብብር፣ በመልካም ፈቃድና በመተሳሰብ እንድትፈቱ እንዳግዛችሁ ፍቀዱልኝ” በማለት ጥያቄ አቀረበ። ሱዳንና ኢትዮጵያ የወዳጅነት መንፈስ በሚመስል የቀረበን የአሜሪካ አስተዳደር የራስ ግብዣ ተቀብለው የተቋረጠውን ድርድር ለመቀጠል ተግባቡ። በዚህም መሠረት የዓለም ባንክ ከአሜሪካ አስተዳደር ጋር ተዳብሎ የሁለቱም ተወካዮች በታዛቢነት በተገኙበት አራት ተከታታይ ስብሰባዎች በአዲስ አበባ፣ በካይሮ፣ በካርቱምና እንደገና በአዲስ አበባ ተካሂደዋል። በታዛቢ ፊት የሚደረገው ድርድር ውጤትና አመላካች አቅጣጫው የሦስቱም ሀገሮች የውጭ ጉዳይና የውኃ ሚኒስትሮች በተገኙበት የአሜሪካ ትሬዠሪ ጸሀፊ/ሚኒስትርና የዓለም ባንክ ፕሬዜዳንት በተሳተፉበት በዋሽንግተን በአሜሪካ ትሬዠሪ መስሪያ ቤት በኖቬምበር 6 ቀን 2019፣ በዲሴምበር 9 ቀን 2019 እና በጃንዋሪ 20 ቀን 2020 ስብሰባ በማድረግ ተመዝኗል። በዚህም ሦስቱም ሀገሮች፤ በተለይ ግብፅንና ኢትዮጵያን የማያስማማቸው ጉዳይ እየሰፋ መምጣቱ ግልጽ ሆኗል።

ቀደም ሲል በአሜሪካ ግምጃ ቤት ጸሐፊ/ሚኒስትርና በዓለም ባንክ ፕሬዜዳንት ታዛቢነት በሦስቱ ሀገሮች የውጭ ጉዳይና የውኃ ሚኒስትሮች መካከል በተደረሰው መግባባት መሠረት፣ በአዲስ መልክ በታዛቢ ፊት የሚካሄደው ድርድር እስከ ጃንዋሪ 20 ቀን 2020 በስኬት ካልተቋጨ ጉዳዩ በመርህ መግለጫ ስምምነት አንቀጽ 10 መሠረት ሊቀጥል ይችላል

የሚል ሆኖ ሳለ፤ የአሜሪካ ትሬዠሪ ጸሐፊ/ሚኒስትርና የዓለም ባንክ ፕሬዜዳንት ለጉዳዩ የመጨረሻ ዕድል ለመሞከር በሚል ጃንዋሪ 28 እና 29 ቀን 2020 እዚያው ዋሽንግተን ስብሰባ እንዲካሄድ ለሶስቱም ሀገሮች ሚኒስትሮች ጥሪ አቀረቡ።

በዚህ ስብሰባ ላይ ሦስቱም ሀገሮች በውጭ ጉዳይና በውኃ ሚኒስትሮቻቸው የተወከሉ ሲሆን ተደራዳሪ ባለሙያዎቻቸውን ይዘው ቀርበው ነበር። በመርህ መግለጫ ስምምነት አንቀጽ 10 መሠረት፣ በሀገሮቹ መካከል ክርክር የተነሳ እንደሆነ ለእርቀ-ሰላም፣ ወይም ለአደራዳሪ፣ ወይም ወደ ሦስትዮሽ ሀገራዊ መሪዎች ለውሳኔ እንዲቀርብ በጋራ መወሰን ይቻላል የሚለውን መርህ ወደጎን በመተው የትሬዠሪ ጸሐፊ/ሚኒስትሩና የዓለም ባንክ ፕሬዜዳንት ሦስቱን ሀገሮች በዚህም በዚያም ብለው ለማፈራረም ጥረት ያደርጉ ጀመር።

በዚህ ሂደት ውስጥ ትልቅ ችግር የነበረው፣ በአንደኛ ደረጃ ታዛቢ ተብለው የተሰየሙት የአሜሪካ ትሬዠሪ ጸሐፊ/ሚኒስትርና የዓለም ባንክ ፕሬዜዳንት ራሳቸውን ከታዛቢነት ሚና ወደ ድርድር አመቻችነት (facilitation) እና ከዚያም አልፎ ወደ አደራዳሪነት ደረጃ ያለፈቃድና ጥያቄ አሳድገው ወይም ራሳቸውን ሹመው ተገኙ። በሁለተኛ ደረጃ የመደራደሪያ ሠነዱ ከዚያ በፊት ግብፅ በተደጋጋሚ አቅርባ ኢትዮጵያና ሱዳን ሳይቀበሉት የቀረው ሠነድ ነበር። በዚህ ሂደት ግብፅና በታዛቢነት ገብተው የነበሩት አሜሪካና የዓለም ባንክ ባንድ ወገን ኢትዮጵያ በሌላ ወገን ሲከራከሩ ሁለቱ የስብሰባ ቀናት ያለስምምነት በመባከናቸው፤ ከዕቅድ ውጭ ስብሰባው እስከ ጃንዋሪ 30 እና 31 ቀጥሏል። አሁንም መግባባት የሚያስችል ውጤት ባይገኝበትም በአሜሪካ ወገን በቀረበው ሠነድ ላይ ግብፅ የይሁንታ ፊርማ ስታኖር ኢትዮጵያ ሠነዱንም አካሂዱንም ተቃወመች። ሱዳን የተለመደ የወላዋይነት አቋም በማንጸባረቅ ድርድሩ በጥሩ የተካሄደና 90 በመቶ በስምምነት የተጠናቀቀ ቢሆንም የመጨረሻው ሳይቋጭ ፊርማ አላኖርም በማለት ቆመች።

"የኢትዮጵያ አቋም የአሜሪካንን በጎ አሳቢነት ያላገናዘበ ነው" በማለት የትሬዠሪው ጸሐፊ/ሚኒስትሩ ቅሬታቸውን ቢገልጹም ስብሰባው በእንዲህ ሁኔታ መቆሙ ግድ ሆኗል። ጃንዋሪ 31 ቀን 2020 ስብሰባው አብቅቶ፤ ድርድሩም ቆሞ ተደራዳሪ ወገኖች ወደየሀገራቸው አመሩ።

የድርድሩ ሂደት ከፍ ብሎ በተገለጸው ሁኔታ በተቋረጠ በወሩ የግብፅ፣ የኢትዮጵያና የሱዳን ተደራዳሪዎች ፌብሩዋሪ 28 ቀን 2020 በዋሽንግተን ዲሲ እንደገና ተሰብስበው በቀሩት ጉዳዮች ላይ ስምምነት ተደርሶ እንዲፈራረሙ በማሳሰብ፣ የአሜሪካ ትሬዠሪ ጸሐፊ/ሚኒስትር ጥሪ አስተላልፈው ነበር። የግብፅና የሱዳን ወገኖች በጥሪው መሠረት ዋሽንግተን ሲገኙ፤ የኢትዮጵያ ወገን ጥሪውን ሳይቀበል ቀርቷል። የኢትዮጵያ ወገን ጥሪውን ያልተቀበለበት ምክንያት ግልጽና ቀጥተኛ ነበር። ቀደም ሲል በነበረው የዋሽንግተኑ የድርድር

ሂደት የአሜሪካና የዓለም ባንክ ታዛቢ ባለስልጣናት ከሦስትዮሽ ተደራዳሪ ወገኖች ፈቃድ ሳያገኙ ራሳቸውን ከታዛቢነት ወደ አመቻችነት (facilitation)፣ ከዚያም ወደ አደራዳሪነት ከፍ ከማድረጋቸውም በላይ በግልጽ ሁኔታ ለግብፅ ወገን የማዳላት፣ አልፎ ተርፎም ከግብፅ ወገን ጋር አንድ ልዑክ በሚመስል ደረጃ የኢትዮጵያን ተደራዳሪዎች ሲሞግቱና ጫና ሲያሳድሩባቸው ስለነበረ፣ የኢትዮጵያ ልዑካን እንደገና ወደ ዋሽንግተን መሄድ አስፈላጊም ጠቃሚም ሆኖ አላገኙትም፡፡

የአሜሪካ ትሬዠሪ ጸሐፊ/ሚኒስትሩና የዓለም ባንክ ፕሬዜዳንት የግብፅና የሱዳን ልዑካንን በጽ/ቤታቸው በተናጠል በመሰብሰብ የድርድሩ ውጤት ነው ያሉትን ሠነድ እዚያ ለተገኙት ለሁለቱ ተደራዳሪ ወገኖች በማደል ለፊርማ ጋብዘዋቸው ነበር፡፡ የግብፅ ወገን በትሬዠሪው መ/ቤት በቀረበው ሠነድ ላይ ወዲያው በደስታ ፈንድቆ ሲፈርም፤ የሱዳን ወገን በበኩሉ ድርድሩ ዘጠና በመቶ ስምምነት ያገኘ ቢሆንም የሦስትዮሽ ወገኖቹ ባንድ ላይ ሁነው የቀሩት ጉዳዮችም በተጨማሪ ድርድር ተቋጭተው መፈረም ይሻላል በሚል ፊርማውን ሳያኖር ወደሀገሩ ተመለሰ፡፡ የኢትዮጵያ ወገን በወሰደው አቋም በመበሳጨት የትሬዠሪው ጸሐፊ የኢትዮጵያ አካሄድ ትክክል አለመሆኑን በማስገንዘብ፣ የስምምነት ውጤት ብለው ባዘጋጁት ሠነድ ላይ የኢትዮጵያን ወገን ፊርማውን እንዲያኖር ለኢትዮጵያ የውጭ ጉይ መስሪያ ቤት ሠነዱ ተልኮ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በበኩሉ የተዘጋጀው ሠነድ በአግባቡ ድርድር ያልተደረገበት ከመሆኑም በላይ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም በሚጎዳ መልኩ ለግብፅ ያደላ መሆኑን በማስገንዘብ፣ የኢትዮጵያ ወገን በቀረበው የስምምነት ሠነድ ላይ ለመፈረም ፈቃደኛ አለመሆኑን በማያሻማ ቋንቋ በመግለጽ ፊርማውንም እንደማያሳፍበት አሳወቀ፡፡

ይህ ሁሉ ሲሆን ኢትዮጵያ የሕዳሴ ግድቡን በቀን ሀያ አራት ሠዓት ሙሉ በሦስት ፈረቃ መስራቱን ቀጥላለች፡፡ ቀደም ሲል በታቀደው አካሄድና በመርህ መግለጫ ስምምነቱ አግባብ የግድቡ የመነሻ ውኃ ሙሌት (initial/first stage filling) በሰኔ ወር 2020 መጨረሻ እንደሚፈጸም ኢትዮጵያ አበክራ መግለጹን ቀጥላበታለች፡፡ በዚህ በኢትዮጵያ ቀጥተኛ አቋምና ቁርጠኛ ውሳኔ በመረበሽና በመርበትበት የአሜሪካ አስተዳደር፣ የግብፅ ወገን እንዲሁም የሱዳን ወገን የየበኩላቸውን የምላሽ እርምጃ ማፈላለግ ተያያዙት፡፡ በዚህ መሠረት አንደኛ፣ የአሜሪካ ትሬዠሪ መስሪያ ቤት የሦስትዮሽ ወገን አጠቃላይ ስምምነት ሳይቋጭ ኢትዮጵያ ግድቡን መሙላት አትችልም ሲል መግለጫ አወጣ፡፡ ሁለተኛ፣ የግብፅ ወገን በግንቦት 1 ቀን 2020 "ለመረጃ" ያህል በሚል ሰበብ ኢትዮጵያን የሚወነጅል ደብዳቤ ለዓለም መንግስታት የፀጥታ ጥበቃ ምክር ቤት ሲያስገባ በምክር ቤቱ አማካይነት ሠነዱ ለአባል አገራት እንዲሰራጭ ጠይቋል፡፡ ሦስተኛ፣ የሱዳን ወገን በበኩሉ ቀደም ሲል በግድቡ አሰራርና ጠቀሜታ ለዓመታት ከኢትዮጵያ ጎን ከቆመበት አቋሙ በመንሸራተት ለግብፅ መወገኑን

በሚያጋልጥ መልኩ ለዓለም መንግስታት የፀጥታ ጥበቃ ምክር ቤት በላከው መግለጫ፣ አጠቃላይ ስምምነት (comprehensive agreement) ሳይደረስ ኢትዮጵያ የግድቡን ሙሌት እንዳትጀምር አስጠንቅቋል፡፡

የሆነ ሆኖ፣ የኢትዮጵያ ወገን በበኩሉ ግድቡ በኢትዮጵያ መሬትና ግዛት በኢትዮጵያ አንጡራ ጥሪት የሚገነባ መሆኑን በማብራራት፣ በተጨማሪም ግድቡ የተሰራው የኢትዮጵያን ህብረተሰብ የኢኮኖሚ ልማት ለማገዝና ከድህነት ነጻ ለማውጣት ታስቦና ታቅዶ እየተሰራ ያለ መሆኑን በማስረዳት፣ ድንበር ተሻጋሪ በሆነው ዓባይ ወንዝ ላይ ሚዛናዊና ምክንያታዊ በሆነ መርህ መሠረት በሌሎች የውኃ ተጋሪ ሀገሮች ላይ ጉልህ ጉዳት እንዳይደርስ ጥንቃቄ በመውሰድ የውኃ ልማቷን ማካሄድ የማይገሰስ የኢትዮጵያ መብት መሆኑን አስገንዝቦ፣ የታቀደው የግድቡ የውኃ ሙሌት በመጋቢት 2015 በካርቱም ከተማ በግብፅ፣ በኢትዮጵያና በሱዳን ርዕሳነ መንግስታት በተፈረመው መርህ መግለጫና ዕቅድ መሠረት የመጀመሪያ ደረጃ ሙሌት ልታካሂድ የሚከለክላት አግባብ አለመኖሩን በማስገንዘብ፤ ለዓለም መንግስታት የጸጥታ ጥበቃ ምክር ቤት የይታወቅልኝ መግለጫ አስገብቷል፡፡ የኢትዮጵያ ቁርጠኝነት እየታወቀ በመሄዱና የግብፅ ወገን ስጋት ተጋንኖ በመወራቱ በርካታ ሦስተኛ ወገኖች የሦስትዮሹ ድርድር እንዲቀጥል የሚማጸኑ መግለጫዎችን ያወጡ ጀመር፡፡ በዚህ ረገድ (1) የተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሐፊ (2) የአውሮጳ ህብረት የኮሚሽኑና የካውንስሉ መሪዎች በጥምር (3) የአፍሪቃ ህብረት ኮሚሽን ኮሚሽነር ያወጡት መግለጫዎች የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ይህ እንዲህ እንዳለ የሱዳን ወገን የግብፅንና የኢትዮጵያን ወገኖች በተናጠል በማነጋገር ድርድሩ እንዲቀጥል አዲስ ጥረት ጀመረ፡፡ ይህ አዲሱ የድርድር ጥረት ከሦስት የተለያዩ ግንዛቤዎችና ተግዳሮቶች የሚነሳ መሆኑን በማስተዋል ቀጣዩም ድርድር አልጋ ባልጋ እንደማይሆን መገመት ይቻል ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ የግብፅ ወገን ድርድሩ ተጠናቅቆ ሳለ በኢትዮጵያ ወገን አሻፈረኝነት የተነሳ ብቻ ሳይፈረም ቀርቷል ብሎ ያምናል፡፡ የሱዳን ወገን በበኩሉ ዘጠና በመቶ ድርድሩ ስምምነት ላይ ደርሶ ሳይቋጭ መቅረቱን ይገልጻል፡፡ የኢትዮጵያ ወገን ደግሞ በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ስምምነት ሳይደረስ በታዛቢዎች አድልዎ የተነሳ ድርድሩ የተቋረጠ መሆኑን ያምናል፡፡

ተቋርጦ የነበረው ድርድር ከሰኔ 9 ቀን 2020 ጀምሮ በቪዲዮ ኮንፈረንስ አማካይነት ቀጥሎ ተካሄዷል፡፡ በዚህኛው ድርድር የአውሮጳ ህብረት፣ ደቡብ አፍሪቃና ዩ ኤስ አሜሪካ በታዛቢነት እንዲሰየሙ ሦስትዮሽ ተደራዳሪዎች ተስማምተዋል፡፡ ድርድሩ እስከ ሰኔ 17 ቀን 2020 ቀጥሎ አሁንም በድጋሚ ሳይቋጭ ተቋርጧል፡፡ ሆኖም ሶስቱም ወገኖች የአሁኑ ድርድር መለስተኛ እመርታ ማሳየቱን አልሸሸጉም፡፡ ካወጡት መግለጫዎቻቸው ለመገንዘብ እንደሚቻለው በግብፅ ወገን አስተያየት ድርድሩ በቴክኒክ አንጻር መለስተኛ ስምምነት የተገኘበት ቢሆንም በኢትዮጵያ ግትርነት የተነሳ ከህግ ጉዳዮች አንጻር ውጤት የለውም

ተብሏል። በዚህም የተነሳ አጠቃላይ ስምምነት ሊደረስ አልተቻለም በማለት የግብፅ ወገን ያማርራል።

የሱዳን ወገን በበኩሉ፣ የአሁኑ ድርድር ዘጠና አምስት በመቶ የተጠናቀቀ ቢሆንም በኢትዮጵያ እምቢተኝነት ምክንያት ህግን የተመለከቱ ጉዳዮች በስምምነት ስላልተቋጨ አጠቃላይ ስምምነት ላይ ሊደረስ አልተቻለም በማለት የራሱን መግለጫ አውጥቷል። በኢትዮጵያ ወገን የተሰጠው መግለጫ የሚያሳየው ደግሞ በተደረገው ድርድር፣ በተለይ ቴክኒክን በተመለከተ የተሻለ መቀራረብ የተደረሰበት ቢሆንም፤ የግብፅና የሱዳን ወገኖች የኢትዮጵያን ሉዓላዊ ውኃ የማልማት መብት የሚጥስ ስምምነት ስለሚፈልጉ በህግ ረገድ የተደረገው ድርድር መቋጫ ሊያገኝ አልቻለም የሚል ነው።

ከሰኔ 17 ቀን 2020 ወዲህ በሶስትዮሽ ወገኖች መካከል የሚታየው ሁኔታ የመቀራረብ አዝማሚያ ያለው ቢመስልም በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ስምምነት ያላስገኘ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። የሱዳንና የግብፅ ወገኖች አጠቃላይ ስምምነት ሳይደረስ ኢትዮጵያ ግድቡን መሙላት የለባትም ሲሉ ይደመጣሉ። ኢትዮጵያ በበኩሏ በሐምሌ ወር 2020 ያቀደችው የመጀመሪያ ዓመት የመነሻ ውኃ ሙሌት እንደምትፈጽም አበክራ እየገለጸች ትገኛለች። አፈጻጸሙም መጋቢት 2015 በሦስትዮሽ ሀገራት መሪዎች በተፈረመው የመርህ መግለጫ ስምምነት መሠረት እንደሚሆንና የሥጋት ምንጭ እንደማይሆን አበክራ ታስረዳለች። ይህ የሚጠበቀው የመነሻ የግድቡ ውኃ ሙሌት ግብፅንም ሆነ ሱዳንን በየሀገሮቻቸው ባለው የውኃ አጠቃቀም ጉልህ ጉዳት እንደማያደርስባቸውና ይልቁንም ዘርፈ-ብዙ ጠቀሜታ የሚያስገኝላቸው መሆኑንም የጥናት ማስረጃዎችን በማጣቀስ ኢትዮጵያ ያለመታከት ማብራሪያ በማቅረብ ላይ ትገኛለች።

## ማጠቃለያ

አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ወንዞች ድንበር ተሻጋሪ መሆናቸውና፤ አብዛኞቹ የወንዞች መዳረሻ ሀገሮች ውኃ አጠር በመሆናቸው ተገቢና ዘላቂ አገራዊ የውኃ ፖሊሲ ማውጣትና መተግበር ለነገ የሚባል ጉዳይ አይሆንም። ዓባይን፣ ተከዜን፣ ባሮ-አቆቦን ይዞ አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ወንዞች ወደ ናይል ስለሚፈሱ ልዩ የፖሊሲ ትኩረት ይገባቸዋል። በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ጂዎግራፊያዊ አቀማመጥና የወንዞቿ አገናኝነት ባንድ ላይ ተዳምረው ሀገሪቱን ልዩ በሆነ ጂኦ-ፖለቲካዊ ስፍራ አስቀምጠዋታል። የነዚህን የውኃ ሀብቶች ተፈጥሯዊ ባህሪይ ባለማስተዋል የኢትዮጵያ ወንዞች ተቀባይ ሀገሮች የውኃ ሀብቱን ለመቆጣጠር ሲሉ የሚያደርጉትን ያልተገባ አካሄድ በፖሊሲና በዲፕሎማሲ መከላከል እንዲሁም በተገቢ የውኃ ልማት ስትራቴጂ ማሳለጥ ያስፈልጋል። በሰሜን ምስራቅ አፍሪቃና በመካከለኛ ምስራቅ የኢትዮጵያ የመጪው ዘመን ፖሊሲ ተግዳሮት ወይም ተሰሚነት ዓባይን ጨምሮ በድንበር

ተሻጋሪ ወንዞቿ ጉዳይ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት የኢትዮጵያ ድንበር ተሻጋሪ ውኃ ፖለቲካ ጉዳይ በታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታና ከዚህ ጋር ተያይዞ በተካሄደው ድርድርና የዲፕሎማሲ ውጣ ውረድ በግልጽ የተፈተሸ ነው፡፡ በናይል ተፋሰሱ የትብብር ማዕቀፍ (CFA) ድርድርና በመርህ መግለጫ ስምምነት ሂደትና ውጤት የኢትዮጵያን ተሰሚነት ያጎላ ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱም ወሳኝ አመላካች ነው ለማለት ይቻላል፡፡ የኢትዮጵያ የውኃ ልማት ጉዳይ ቀዳሚ አጀንዳ ሆኖ መቆየቱ አይቀርም፡፡ የውኃ ልማት ፖሊሲና አፈጻጸሙ ለሁሉም የውኃ ተጋሪ ሀገሮች በሚጠቅም መንገድ ለማስኬድ የውኃ ተጋሪ ሀገሮች ትብብር፣ መተሳሰብና መልካም ፈቃድ ሊኖር ይገባል፡፡ የጋራ የውኃ ሀብትን ከብክነትና ከብክለት መጠበቅ፤ ከምንጩ እስከ ጫፉ በእንክብካቤ መያዝ የሁሉም ውኃ ተጋሪ ሀገሮች ግዴታ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይኸንኑ ጉዳይ በቴክኒክ፣ በህግ እና በተቋም በማጽናትና በመምራት የዘላቂ ፖሊሲ አቅጣጫ እንዲሆን ማስቻል ያስፈልጋል፡፡ በዓባይና በናይል ተፋሰስ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ይህን መርህ እንዲያጸና ይጠበቅበታል፡፡

# የናይል ተፋሰስ ተለዋዋጭ የውኃ ፖለቲካና ተቋማዊ ገፅታዎች

**ተስፋዬ ታፈሰ**

*ይህ አጭር ፅሑፍ በናይል ተፋሰስ ተቋማዊና የውኃ ፖለቲካ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ለመንደርደሪያ በሚሆን መግቢያ ይጀምርና ስለ ናይል ተፋሰስ ትብብር ማዕቀፍ* (Nile Basin Cooperative Framework Agreement-CFA) *ፍሬ ነገርና ያጋጠሙት ተግዳሮቶች እንዲሁም ስለ ውኃው ፖለቲካ ሁኔታ አትቶ በማጠቃለያ መልክ አንዳንድ የመፍትሔ ሀሳቦችን ይጠቁማል።*

## መግቢያ

የናይል ተፋሰስ በተለያዩ ጊዜያት ያጋጠሙት ችግሮችና ተግዳሮቶች በአምስት ተከፍለው ሊጠቀሱ ይችላሉ። አንደኛ፡- በላይኛው ተፋሰስ አገሮች በተለይም በኢትዮጵያ የሚታየው የአካባቢ መራቆት፣ የተፋሰስ እንክብካቤ አለመኖር፣ የአፈር መሸርሸር፣ የታችኛው ተፋሰስ አገሮች በደለል መሞላትና የግድቦች ዕድሜ ማጠር፤ ሁለተኛ፡- የአየር ንብረት ለውጥ፣ ድርቅና የውኃ ዕጥረት፤ ሦስተኛ፡- የውኃ ማኔጅመንትና የውኃ ቴክኖሎጂ በተፋሰሱ ደካማ መሆንን በዚህም ሳቢያ የናይል ውኃ አጠቃቀም መዝረክረክ (ለምሳሌ ያህል የጠብታ መስኖ (drip irrigation) በተፋሰሱ ጥቅም ላይ አለመዋል 48% የሚሆነውን ለእርሻ የሚውል ውኃ እንዲባክን አድርጎታል)። አራተኛ፡- በተፋሰሱ እየተመዘገበ ያለው የሕዝብ ዕድገት ካለው የተፈጥሮ ኃብት መጠን ጋር በተለይም ከውኃ መጠን ጋር ያለመመጣጠን (ለመረጃ ያህል የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ከ100 ሚሊዮን ካለፈ ሰንበትበት ሲል የግብፅም ሕዝብ ብዛት እዚህ አሀዝ ላይ እየደረሰ ነው)። አምስተኛ፡- ሁሉም የናይል ተፋሰስ አገራት የተስማሙበት የተፋሰሱ ተቋም አለመኖር ናቸው (ምንም እንኳን እስከዛሬ ሦስት የናይል ተፋሰስ ተቋማት የተፈጠሩ ቢሆንም (ሃይድሮሜት ከ1967-1992፣ ቴኮናይል ከ1992-1999 እና የናይል ተፋሰስ ጅማሮ ከ1999 ጀምሮ እስካሁን)[4] ብዙዎቹ በግብፅ ፊታውራሪነት የተመሠረቱ

[4] በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በተለይ ካልተገለጸ በስተቀር የዘመን አቆጣጠሮቹ በሙሉ እንደ አውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ናቸው።

ስለነበር ሁሉም የናይል ተፋሰስ አገሮች የተስማሙበትና የተፈራረሙበት ሕጋዊና ተቋማዊ ማዕቀፍ እስከዛሬ ሊኖር አልቻለም)።

## የናይል ትብብር ማዕቀፍ ስምምነት (Nile Cooperative Framework Agreement)

ይህንን ሕጋዊና ተቋማዊ ማዕቀፍ (Legal and Institutional Framework) ለማዘጋጀትና ለውይይት ለማቅረብ ወደ አስር ዓመታት ፈጅቷል (1997-2007)። የማዕቀፉ ዓላማ የናይል ወንዝ እንደሌሎች ድንበር ዘለል ወይንም አገር አቋራጭ ወንዞች (ለምሳሌ ሚኮንግ፣ ሴኔጋል፣ ኮሎራዶ፣ ራይን ወዘተ) የራሱ የሆነ መተዳደሪያ ወይንም ሕጋዊና ተቋማዊ ማዕቀፍ ኖሮት ቋሚ የሆነ የናይል ተፋሰስ ኮሚሽን (Nile River Basic Commission) ለማቋቋም ነው። ረቂቅ ሠነዱ የተዘጋጀው በተለያዩ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ላይ ከተደረጉ ተመሳሳይ ስምምነቶች ልምድ በመነሳትና እና በተባበሩት መንግስታት የ1997 የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ኮንቬንሽን (UN Convention on the Law of the Non-Navigational Uses of International Water Courses) ላይ በመንተራስ ነው።

የስምምነቱ ዋናው ዓላማ ፍትሐዊ የውኃ ክፍፍልን እና (equitable entitlement) በሌላ የተፋሰስ አገር ላይ ጉዳት አለማድረስን (no-harm rule) ጎን ለጎንና ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ነው። በዚህ ረገድ የሠነዱ አንቀፅ 4.1. ስለፍትሐዊና ሚዛናዊ የውኃ አጠቃቀም ሲያትት፤ አንቀፅ 5.1 ደግሞ አንድ ተፋሰስ አገር በሌላ የተፋሰሱ አገር ላይ ጉዳት አለማድረስን ይጠቅሳል። ጠቅለል ባለ መልኩ ማዕቀፉ የናይል ውኃን እንክብካቤ፣ አጠቃቀም፣ ቁጠባና ዕድገትን ተግባራዊ ለማድረግ የተነደፈ ነው። ይህ ሠነድ ብዙ ከተተቸበት በኂላ (ፀጉር ስንጠቃንም ጨምሮ) ተጠናቅቆ ወደ ፊርማና ብሎም ወደ ማፅደቅ (ratification) ሊደርስ ሲል የታችኛው ተፋሰስ አገሮች አንዱን ንዑስ አንቀፅ (14 ‹‹ለ››ን) መዝዘው በማውጣት ይህ ካልተለወጠ ወይንም እኛ በፈለግነው መንገድ ካልተስተካከለ ሠነዱን ለመፈረም ዝግጁ አይደለንም ብለው በይፋ ገለፁ። በእነርሱ ሀሳብ መሠረት ሠነዱ ላይ የተቀመጠውን ንዑስ አንቀፅ 14 ‹‹ለ›› ‹‹not to cause significant harm to the water security of any other Nile basin countries›› (በማንኛውም የተፋስሱ አገሮች ላይ የውኃ ዋስትናን የሚፈታተን ጉዳት አለማድረስ) የሚለው ሐረግ ‹‹not to adversely affect the water security of current users and the rights of any other Nile Basin countries›› (በአሁኑ ጊዜ የውኃው ተጠቃሚ የሆኑትን የተፋሰሱ አገሮችና ሌሎቹንም ጨምሮ የተጠቃሚ መብታቸውንና የውኃ ዋስትናቸው ላይ ጉዳት አለማድረስ) በሚል እንዲተካ ነው አገራቱ የጠየቁት። ይህንን በማድረግ ሁለቱ የታችኛው ተፋሰስ አገሮች ማለትም ግብፅና ሱዳን ሁለት መሠረተ ሀሳቦችን ማለትም የውኃ ደህንነት መጠበቅና ቀደምት የናይል ስምምነቶች 1902፣ 1929፣ 1959) እንዲከበሩላቸው ነው የፈለጉት። ይህንን የሐረግ ለውጥ ጥያቄ ሁሉም የላይኛው ተፋሰስ አገሮች በአንድ ድምፅ

ተቃውመውታል። እንደዚያም ሆኖ ማለት ልዩነቶቹ እንዳሉ ሆነው ሠነዱ ግንቦት 2010 ጀምሮ የአንድ ዓመት የፊርማ ጊዜ ተሰጥቶት ዑጋንዳ እንቴቤ በሚገኘው የናይል ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት ተቀምጧል። እስካሁን ስድስት የላይኛው ተፋሰስ አገሮች የሆኑት ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ዑጋንዳ፣ ሩዋንዳ፣ ቡሩንዲ እና ታንዛንያ የፈረሙት ሲሆን፤ ከነዚህም ውስጥ የመጀመርያዎቹ ሦስቱ ለፓርላማዎቻቸው አቅርበው አፅድቀውታል። ምንም እንኳን በሕጉ መሠረት ሁለት ሦስተኛ አገሮች ከፈረሙት ሠነዱ የሚጸድቅ ቢሆንም የናይል ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት የሌሎቹን ተፋሰስ አገሮች መፈረም በትዕግስት እየተጠባበቀ የሚገኝ ይመስላል። የቀሩት ሦስቱ የተፋሰሱ አገሮች ለፓርላማዎቻቸው አቅርበው ካፀደቁ ቁጥራቸው ወደ ስድስት ስለሚያድግ ሠነዱ በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ፀድቆ ተግባራዊ መሆን ይችላል።

ግብፅ ይህንን ህጋዊና ተቋማዊ ማዕቀፍ ለመፈረም ያልፈለገችባቸውን ምክንያቶችን በሦስት ከፍሎ ማየት ይቻላል። አንደኛው ሠነዱ የማይነካ ድርሻዬን (acquired/natural/ historical right) እንደገና እንዲታይ/እንዲከለስ ሊያደርግብኝ ይችላል ከሚል ስጋት የመነጨ ሲሆን፣ ሁለተኛው ምንም እኳን በሕግ የተደገፈ ባይሆንም ግብፅ ለብዙ ዘመናት በተፋሰሱ ስትተገብረው የቆየችውን የማገጃ ድምፅ ወይንም ቃልን በቃል የመሻር መብት (veto right) ይቀንስብኛል ከሚል ፍርሀት የተፈጠረ ነው። ሦስተኛው ምክንያት ማንኛውም በናይል ወንዝ ላይ የሚደረግ የልማት ሥራና እንቅስቃሴ የቅድሚያ ማሳወቂያ (prior notification) ምልክት ሳይሰጠኝ እንዲሁም የጉዳት አለማድረስ (no harm rule) ሳይተገበር መከናወን የለበትም የሚል አቋም ስላላት ነው ብሎ ማሰብ ይቻላል።

ከታች ወረድ ብለን እንደምናየው የሱዳን ሠነዱን አልፈርምም ማለት ለሕዳሴው ግድብ ግንባታ ድጋፍ ከመስጠቷ ጋር ስለሚጣረስ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሠነዱን ልትፈርም ትችላለች የሚለው ዕሳቤ ሚዛን የሚደፋ ይመስላል። በዚህ ፀሐፊ አስተያየት በቅርቡ የመንግሥት ለውጥ የተካሄደባት ሱዳን በናይል የውኃ ፖለቲካ የሚኖራትን የወደፊት አቋም ከወዲሁ ለመገመት ያስቸግራል። ያለው ምርጫ ሁኔታዎችንና ሂደቶችን በጥሞና መከታተል ነው።

## የናይል ተፋሰስ ተለዋዋጭ የውኃ ፖለቲካ ሁኔታ

ለዘመናት የቆየው የናይል ተፋሰስ ነባራዊ ሁኔታ (status quo) በአጭር ጊዜያት ማለትም ባለፉት አስር ዓመታት ያልተጠበቀ ለውጥ አሳይቷል። ይህንን ለውጥ ካመጡት መካከል ዋና ዋና የሚባሉትን ስድስት ክስተቶች መጥቀስ ይቻላል።

ሀ. የሕዳሴው ግድብ ግንባታ በተፋሰሱ ውስጥ ያለውን የውኃ ፖለቲካ አቅጣጫ በከፍተኛ ሁኔታ ማስለውጥ፤

ለ. የላይኛው ተፋሰስ አገሮች ከመቼውም ጊዜ በላይ መተባበርና አንድ ዓይነት አቋም መያዝ፤

ሐ. የላይኛው ተፋሰስ አገሮች የፖለቲካና ኢኮኖሚ አቅማቸውና ተሰሚነታቸው በአንፃራዊ መልክ መጎልበቱ፤

መ. የላይኛው ተፋሰስ አገሮች የተለመዱትን/የታወቁትን ዓለም አቀፍ ገንዘብ አበዳሪ ድርጅቶችን (ለምሳሌ የዓለም ባንክ፣ የአፍሪካ ልማት ባንክ፣ የተባበሩት መንግሥታት የልማት ድርጅት ወዘተ) ወደጎን በመተው ሌሎች አማራጮችን (ለምሳሌ ቻይናን፣ ብሪክስንና የሁለትዮሽ ስምምነቶችን) መጠቀም መጀመራቸው፤

ሠ. የሱዳን ባልተጠበቀና ባልታሰበ ሁኔታ የሕዳሴውን ግድብ ግንባታ ምንም እንኳን ለራስዋ ጥቅም ብላ ቢሆንም በማያወላውል ሁኔታ መደገፏ፤

ረ. የግብፅ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጡንቻዎች መላላትና ላለፉት አስር ዓመታት በፖለቲካ ውጥረት ውስጥ መገኘት፤ እንዲሁም ከዚህ ጋር ተያይዞ በዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት ላይ ያላት ተፅዕኖ መቀነስ ናቸው።

ከላይ ከተጠቀሱት ስድስት ነጥቦች ውስጥ አንዱና ዋነኛ ጥያቄ ሊሆን የሚችለው የሱዳን ባልታሰበና ባልተጠበቀ ሁኔታ የሕዳሴ ግድቡን ግንባታ የመደገፏን ምክንያቶች ማወቅ ነው። ለዚህ ጥያቄ መልስ ሊሆኑ የሚችሉ ሰባት ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል። እነዚህም፡-

1ኛ. ከሕዳሴው ግድብ በስተጀርባ የሚታቀረው ውኃ በፊት ከነበረው የናይል ፍሰት ተጨማሪ ውኃ ለሱዳንና ለግብፅ ማድረስ ስለሚችል፣

2ኛ. የማይዋዥቅና የተመጣጠነ አስተማማኝ ውኃ (regulated water) ሱዳን ማግኘት ስለምትችል ሲሆን ይህንን ለማስረዳት ከግድቡ ግንባታ በፊት የነበረውንና አሁን ከግንባታው በኋላ የሚኖረውን የውኃ ፍሰት በማስረጃነት መጥቀስ ይቻላል። ከግድቡ ግንባታ በፊት የነበረውን 200 ኪዩቢክ ሜትር ውኃ በሰከንድ ፍሰት (ዝናብ በሌለ ወቅት) እና 6,500 ኪዩቢክ ሜትር ውኃ በሰከንድ (በዝናብ ወቅት) ወደ 3,600-3,800 ኪዩቢክ ሜትር ውኃ በሰከንድ በአማካይ በሁሉም ወቅቶች እንዲፈስ ያደርገዋል።

3ኛ. የህዳሴው ግድብ አፈሩንና ዝቃጭ ቅሪት-አካልን ግድቡ አካባቢ በማስቀረት የሱዳን ግድቦችን (ለምሳሌ ያህል ሮዜርስና ሴናር ግድቦችን) ከጥቅም ውጭ እያደረጋቸው የነበረውን ደለል ያስቀርላቸዋል። ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ሱዳን በየዓመቱ

ከግድቦቿ ደለል ለማስጠረግ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዶላሮች እንደምታወጣ መጥቀሱ በቂ ማስረጃ ሊሆን ይችላል።

4ኛ. ካርቱምንና ሌሎችንም በናይል ተፋሰስ አካባቢ የሚገኙ ከተሞችንና የገጠር አካባቢዎችን በከፍተኛ ሁኔታ ያጠቃ የነበረው ጎርፍ ከሕዳሴው ግድብ ግንባታ በኋላ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ ወይንም ጨርሶ እንዳይኖር ያደርገዋል።

5ኛ. ሱዳን ከሕዳሴው ግድብ የሚመነጨውን የኤሌክትሪክ ኃይል ከራሷ ከሜሮዌ ግድብ ታገኝ ከነበረው 25% ዋጋ ብቻ በመክፈል ታገኛለች።

6ኛ. ሱዳን የሕዳሴውን ግድብ መገንባት እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም በ1929 እና በ1959 ከግብፅ ጋር የተደረገውን የናይል ውኃ አጠቃቀም ስምምነቶች ተጎጂ መሆኗን በማሳየት ሌላ ድርድርና ስምምነት እንዲኖር ፍላጎቷን ለማሳየት ትጠቀምበታለች።

የሕዳሴው ግድብ መገንባት ግብፆች እንኳን በውናቸው በሕልማቸውም ያላሰቡት ጉዳይ ሆኖባቸዋል። ለዚህም ነው በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ አሰናካይ ምክንያቶችንና አፍራሽ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚዳዳቸው። ይህንንም ለማስረዳት አራት የሚሆኑ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል። አንደኛ የጣሊያን የግንባታ ድርጅት የሆነውን ሳሊኒን የግድቡን ግንባታ እንዲያቋርጥ በጣሊያን መንግሥት በኩል ሙከራ አድርገዋል። ሁለተኛ የአውሮፓ ህብረትን፣ አሜሪካንን፣ ቻይናን፣ ሳውዲ አረቢያን፣ ጃፓንና ሌሎች አገሮችን በማነጋገር የግብፅን ፀረ-ሕዳሴ ግድብ ግንባታ እንዲደግፉላቸውና ኢትዮጵያ ላይ ተፅዕኖ እንዲያደርጉ በተደጋጋሚ ጥረት አድርገዋል። ሦስተኛ የግድቡን ጉዳይ ለዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት (International Court of Justice) እና ለተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት (UN Security Council) ለማቅረብ ላይ ታች ሲሉ ነበር። በመጨረሻም ፕሬዚደንት ሞሐመድ ሞርሲ ስልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜና አሁንም በአዲሱ ፕሬዚደንት አብደል ፋታህ አል ሲሲ ዘመን አልፎ አልፎ ጦር-አጫሪ የሆኑ ማስፈራሪያዎችና ዛቻዎችን በኢትየጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ ሰንዝረዋል፤ አሁንም በመሰንዘር ላይ ይገኛሉ።

ነገሮች ባሁኑ ጊዜ መካረር የጀመሩትና አሁን እየታየ ያለው የጋለ የውኃ ፖለቲካ ሊከሰት የቻለው የዓባይ ወንዝ ተፈጥሯዊ መፍሰሻውን ለግንባታ ሲባል ወደሰው ሰራሽ ቦይ የዛሬ ሦስት ዓመት ገደማ እንዲዞር ከተደረገ ጊዜ ጀምሮ ነው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የነበሩት አጨቃጫቂ ሁኔታዎች ባሁኑ ጊዜ የበለጠ የተካረሩት ከግድቡ ጀርባ የሚጠራቀመው ውኃ በምን ያህል ጊዜ ይሁን የሚለው ሠሌዳ ላይና ግድቡ ካለቀ በኋላ ምን ያህል ውኃ ይለቀቅ በሚሉት ጥያቄዎች ላይ መስማማት ስላልተደረሰ ነው። በሌላ አነጋገር የሕዳሴው ግድብ ወሳኝ ደረጃ ላይ መድረሱ ግብፆች ጉዳዩን በማጦዝ አሜሪካኖችን አማልዱን እስከማለት

አድርሷቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ዕቅድ የግድቡ ውኃ ማከማቻ (reservoir) ከ3 እስከ 4 ዓመታት ባለው ጊዜ ውስጥ ማለቅ አለበት የሚል ሲሆን ግብጾች ደግሞ የውኃ አሞላሉ ቢያንስ ከ7 እስከ 10 ዓመታት ባለው ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት ይላሉ፡፡ እንዲያውም በኢትዮጵያ መንግሥት ዕቅድ መሠረት ውኃ ማከማቸቱ በመጪው ክረምት (2012 ዓ.ም) ተጀምሮ ከሦስት ወራት በኋላ በታህሣሥ ወር 2013 ዓ.ም ከአሥራ ሦስቱ የህዳሴው ግድብ የኃይል ማመንጫ ተርባይኖች መካከል ሁለቱ ኃይል ማምረት እንደሚጀምሩ ነው፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎን ሁለቱ አገሮች የማይስማሙበት ሌላው ጉዳይ ግድቡ ከሞላ በኋላ ውኃ አለቃቀቅን በሚመለከት ነው፡፡ እንደ ግብፆች ዕሳቤ ኢትዮጵያ ከግድቡ ቢያንስ 40 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውኃ በዓመት መልቀቅ ይኖርባታል፡፡ እንዲሁም አስዋን ግድብ ላይ የውኃ መጠኑ ከ165 ሜትር ከባሕር ወለል በላይ ዝቅ ካለ ኢትዮጵያ በአስቸኳይ ውኃ በመልቀቅ መጠኑን ማስተካከል አለባት የሚል ሀሳብ ያቀርባሉ፡፡ እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች ኢትዮጵያ ላይ በመጫን አገሪቷ ያልተሳተፈችባቸውንና ያልተቀበለቻቸውን የቅኝ ግዛት ዘመን የናይል ስምምነቶችንና (1902 እና 1929) ከዚያም በኋላ የነበረውን የናይል ስምምነት (1959) እጅ በመጠምዘዝ እንድትቀበል ለማድረግ ሙከራ እያደረጉ ነው ብሎ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ቅድመ-ሁኔታዎች አንድ ፀሐፊ እንዳለው “by so doing, the Egyptians like to make the Grand Ethiopian Renaissance Dam (GERD) hostage to the High Aswan Daam (HAD)” (‹‹ግብፆች ቅድመ-ሁኔታዎቹን በማስቀመጥ የሕዳሴው ግድብ የታላቁ አስዋን ግድብ ታጋች እንዲሆን ይፈልጋሉ››)፡፡ ከዚህም አልፎ ግብፆች ዑጋንዳ በሚገኘው ኦወን ፎልስ ግድብ (Owen Falls Dam) ላይ ሲያደረጉ የቆዩትን ሁኔታ በኢትዮጵያ ላይም ለመድገም ይፈልጋሉ፡፡ ይኸውም የሕዳሴ ግድቡ አልቆ ኃይል ማመንጨት ሲጀምር አንድ ግብፃዊ መሐንዲስ ግድቡ ያለበት ቦታ፣ ማለትም ጉባ ላይ፣ ቢሮ ተሰጥቶት የግድቡን ውኃ አሞላልና አለቃቀቅ እንዲቆጣጠር የሚያስችል ሁኔታ እንዲኖር ሀሳብ አቅርበዋል፡፡ በግብፅ በኩል የተሰነዘሩት ቅድመ-ሁኔታዎች ባጠቃላይ በኢትዮጵያ በኩል ምንም አይነት ሕጋዊም ሆነ ሞራላዊ ተቀባይነት ሊያገኙ አይችሉም፤ ሊችሉም አይገባም፡፡

እንደሚታወቀው ከ20 በላይ ስብሰባዎችን ያደረጉት የሦስቱ አገራት የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት እስከዛሬ ስምምነት ላይ መድረስ ስላልቻሉ በግብፅ ውትወታ አሜሪካኖች ጣልቃ በመግባት ጉዳዩ ወደ ዋሺንግተን ዲሲ አቅንቶ ባለፈው ጥቅምት 2012 ዓ.ም መጨረሻ ላይ፤ አሁን ደግሞ በቅርቡ በታህሣሥ ወር 2012 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ የሦስቱም የተፋሰሱ አገራት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች እና የተወሰኑ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት፣ የዓለም ባንክና የአሜሪካ ገንዘብ ሚኒስቴር ተወካዮች ታዛቢ በሆኑበት ተገናኝተው እንዲወያዩ ተደርጓል፡፡ በዚህ ስብሰባ

ላይ የተስማሙት እስከ መጪው ጃንዋሪ 2020 አጋማሽ ድረስ አንድ ስምምነት ላይ ለመድረስ ጥረት ማድረግ፤ ይህም ካልተሳካ ጉዳዩ በዓለም አቀፍ ሸማጋዮች አማካይነት እንዲታይ ነው።

የአሜሪካኖቹ ጣልቃ መግባት ብዙ ጥያቄዎችን ከመጫሩ በተጨማሪ የተለያዩ ሰዎች የተለያዩ የሴራ ፖለቲካዎችን (conspiracy theories) እንዲያጠነጥኑ አስገድዷቸዋል። የሴራ ፖለቲካዎቹን ለጊዜው ወደኋላ በመተው አንዳንድ የሚታዩ ጥያቄዎችን ማንሳቱ ጠቃሚ ይመስለኛል። ከነዚህም መካከል (ሀ) አሜሪካኖቹና ግብፅ ጉዳዩን ወደ ዋሺንግተን ዲሲ ሲወስዱት ምን አስበው ነው? ምን ዓይነትስ ሤራ ጠንስሰዋል? (ለ) ኢትዮጵያ ለምን፣ እንዴትና በምን ሁኔታ ነው የአሜሪካንን ጣልቃገብነት እና ስብሰባዎች በአሜሪካ እንዲካሄዱ የተስማማችው? (ሐ) በዚህ ጉዳይ የሚያገባው የአሜሪካኖቹ ስቴት ዴፓርትሜንት (በኛ አገር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴሪ ማለት ነው) መሆን ሲገባው ለምን ትሬዠሪ ሴክሬታሪ (በኛ አገር የገንዘብ ሚኒስቴሪ ማለት ነው) ሆነ? ይህ የሆነው ነገሩን በገንዘብ ለመሸንገል ታስቦ ይሆን? (መ) በአሜሪካኖች የሚዘወረው የዓለም ባንክ ተጋብዞ እንዴት ታዛቢ ሊሆን ቻለ? (ሠ) ከዚሁ ጋር በተያያዘ ምናልባት ‹‹ሐ›› እና ‹‹መ››ን ብናቀናጅ ሌላ ጥያቄ ሊያጭር ይችላል። ይኸውም በትሬዠሪ ሴክሬታሪው በኩል ገንዘብ፤ በዓለም ባንክ በኩል ደግሞ ዕርዳታና ብድር ለኢትዮጵያ በመስጠት የሕዳሴው ግድብ ውኃ አሞላል ግብፆች በሚፈልጉት የጊዜ መጠን እንዲዘገይ ታስቦ ቢሆንስ? ይህ ጭፍን መላ-ምት ሳይሆን አንዳንድ ፀሐፊዎች ባደረጉት ጥቆማ አሜሪካኖቹ፣ የአሜሪካ ገንዘብ ሚኒስቴርና የዓለም ባንክ ኢትዮጵያ ቶሎ ግድቡን ባለመጨረስ ልታጣ የምትችለውን በዓመት ከ1 እስከ 1.5 ቢሊዮን ዶላር ለመካስ ተዘጋጅተው ቢሆንስ? ይህ ከተሳካላቸው ኢትዮጵያ የሕዳሴ ግድቡን የውኃ ማከማቻ ለመሙላት ከአስር ዓመታት በላይ እንድታዘገይላቸው ትስማማላቸው ይሆን? ይህንን ፕሮፖዛል ከጃንዋሪ 15 ቀን 2020 በፊት ያቀርቡታል የሚል ከፍተኛ ጭምጭምታ አለ።

ይህንን ሁኔታ ለማሳካት በሚመስል መልኩ ግብፆች በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ የተለያዩ አቋሞችን በመያዝ፣ ባለፈው የተስማሙበትን በሚቀጥለው ስብሰባ ላይ በመሰረዝ እንዲሁም ኢትዮጵያ በፍፁም ልትስማማባቸው የማትችላቸውን ጉዳዮች በማንሳት (ለምሳሌ የቀድሞ ስምምነቶችን ተቀበሉ፣ ይህን ያህል ውኃ ትለቃላችሁ ወዘተ በማለት) ጉዳዩን እንዲጓተትና ስምምነት ላይ እንዳይደረስ ጥረት እያደረጉ ነው ብሎ መገመት የሚቻል ይመስላል። እነዚህና የመሳሰሉት ሁኔታዎች በሚቀጥሉት ወራት ውስጥ ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ በእርግጠኝነት መተንበይ አስቸጋሪ ስለሚሆን ውጤቱን በትዕግስት ከመጠበቅ ሌላ ምንም አማራጭ ያለን አይመስለኝም። እንደዚያም ሆኖ ከላይ እንደጠቆምኩት ጥልቅና አሳሳቢ የሆኑ ጥያቄዎችን ማንሳት ተገቢና ወቅታዊ ነው የሚል ዕምነት አለኝ።

## ማጠቃለያ

የናይል ትብብር ማዕቀፍ (CFA) አለመፅደቅ እንዲሁም የናይል ተፋሰስ ኮሚሽን (NRBC) አለመመስረት ተፋሰሱን በሕግና በስርዓት ለማስተዳደር እንቅፋት ሆኗል፡፡ ሰማንያ ስድስት በመቶ የሚሆነውን የናይል ውኃን እያበረከተች ሰባ በመቶ የሚሆነው ሕዝቧ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ያልሆነባት ኢትዮጵያ ታላቁን የሕዳሴ ግድብ በመገንባት ወደ 6,400 ሜጋ ዋት አቅም ያለው ኃይል ለማመንጨት ማሰቧ ሲያንስባት እንጂ የሚበዛባት አይመስለኝም፡፡ በኔ ግምትና አስተያየት ባሁኑ ወቅት በተፋሰሱ ውስጥ የሚታዩት ችግሮችም ሆነ መፍትሔዎቹ እየተንከባለሉ ያሉት በግብፅ ሜዳ ላይ ነው፡፡ በሌላም በኩል ከቁመቱ ጋር (6,825 ኪ.ሜ) ፍፁም የማይመጣጠን አነስተኛ ውኃ በሆዱ የያዘው የናይል ወንዝ (በአማካይ 74 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር በዓመት) እንዲሁም አሥራ አንድ የተፋሰሱ አገሮች በተለያየ ደረጃ ሊጠቀሙበት የሚፈልጉት የናይል ውኃ ላይ ብቻ ከማተኮር የተለያዩ አማራጮችን ማየቱ ለግብፅም ሆነ ለሌሎቹ የናይል ተፋሰስ አገሮች ጠቃሚ ይመስለኛል፡፡ ለራስ ብቻ ከማሰብ ይልቅ የናይል ውኃ የጋራ ሀብት መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በፍትሐዊነት፣ በምክንያታዊነት እና በቀናነት መርሆዎች ላይ የተመሠረተ የውኃ አጠቃቅምን ሁሉም የተፋሰሱ አገሮች ቢያምኑበትና ስራ ላይ ቢያውሉት መፍትሔዎቹ ሩቅ አይሆኑም፡፡ በዚህ ረገድ የሚከተሉትን በምሳሌነት ማንሳት ይቻላል፡-

ሀ. ግብፅ አዳዲስ የውኃ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ለእርሻ የምታውለውን ውኃ ልትቆጥብ ትችላለች፡፡ ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት ግብፅ የጠብታ መስኖ ቴክኖሎጂ (drip irrigation) በመጠቀም ለእርሻ የምታውለውን ውኃ በ48% ልትቀንስ ትችላለች፤

ለ. የዋጋው ውድነት እንዳለ ሆኖ ግብፅ ከቀይ ባሕርና ከሜዲትራንያን ባሕር ውኃ በመጨለፍ ጨው አልባ ውኃ የማምረት (desalination) አቅሙም ሆነ ሀብቱ ከሌሎቹ የተፋሰሱ አገሮች በተሻለ ሁኔታ አላትና ይህንንም መጠቀም ትችላለች፣

ሐ. ግብፆች በመጠኑ እየተጠቀሙበት ያለውን ውኃ አጣርቶ እንደገና መጠቀም (recycling) አጠናክረው በመቀጠል ተጨማሪ ውኃ ማግኘትን እንደሌላ አማራጭ ሊይዙት ይችላሉ፣

መ. በግብፅና አካባቢው ባሉ አገሮች በስፋትና በብዛት የሚገኘውን የከርሰ-ምድር ውኃን (aquifer) ጥቅም ላይ ማዋል ሌላው ተጨማሪ አማራጭ ነው፣

ሠ. አንድ ጥናት እንደጠቆመው ነጭ ናይልንና የኮንጎ ወንዝን በማገናኘት የኮንጎ ወንዝን ውኃ በቦይ ወደ ግብፅ እንዲፈስ በማድረግ በአሁኑ ወቅት ከናይል ወንዝ ከሚገኘው

ውኃ በተጨማሪ 95 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውኃ በዓመት ግብፅ እንድታገኝ ማድረግ ይቻላል:: ጥናቱ እንደሚያመለክተው የኮንጎ ወንዝ በዓመት 1,000 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር የሚደርስ ውኃ ምንም ጥቅም ላይ ሳይውል ወደ አትላንቲክ ውቅያኖስ ይፈሳል:: ይህንን ውኃ 600 ኪ.ሜ ርዝመት ያለው ቦይ በመስራት የውኃውን አቅጣጫ አስቀይሮ በ200 ሜትር ከፍታ ከነጭ ናይል ጋር በማገናኘት ወደ ደቡብ ሱዳን፣ ሱዳንና ግብፅ እንዲፈስ ማድረግ ይቻላል:: ይህንን ፕሮጀክት ለማጠናቀቅ የ2 ዓመታት ጊዜ፣ የ4 ፓምፒንግ ጣቢያዎች ግንባታ፣ እና 8 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ያስፈልጋል:: ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ለማድረግ የተወሰኑ ተግዳሮቶችንም መቋቋምን ይጠይቃል:: ከነዚህም መካከል ስምንት ቢሊዮን ዶላር ከየትና እንዴት ይገኛል? ወደ 800 ኪሎሜትር ርዝመት ያለው ቦይ ሲቆፈር ደቡብ ሱዳን የሚገኘው ሱድ የተባለው ሰፊ ረግረግ (Sudd Swamp) ውስጥ የሚገኙት አዕዋፋት፣ ሕይወትና ከባቢ አየር እንዴት ሊሆኑ ይችላሉ? እንዲሁም የኮንጎ ወንዝ ተፋሰስ አገሮች (ካሜሩን፣ ጊኒ እና መካከለኛው አፍሪቃ ሪፑብሊክ) ፕሮጀክቱን ይደግፉታል ወይ? የሚሉት ከወዲሁ ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው፣

ረ. ግብፆች አሁን ለተፈጠረው የሪዘርቫየር ውኃ ሙሌት ጊዜና ግድቡ ካለቀ በኂላ ለሚኖረው የውኃ አለቃቀቅ መጠን አለመግባባት ፖለቲካዊ መፍትሔ ላይ ከማተኮር ይልቅ ወደ ቴክኒካል መፍትሔ ቢያዘነብሉ ለራሣቸውም ሆነ ለተፋሰሱ አገሮች የተሻለ አማራጭ ይሆናል፤

ሠ. ሌላው ለተፋሰሱ አገሮች በሙሉ ይበጃል ብዬ የማምነው ግብፅ አጨቃጫቂ የሆኑትን ቀደምት የናይል ተፋሰስ ስምምነቶችን (የ1902፣ 1927 እና 1959 ስምምነቶችን) በመሻር (abrogate በማድረግ) አዲስ የናይል ተፋሰስ ስምምነት እንዲፈረም ብታደርግ ይህ አሁን እያየነው ያለውን መፋጠጥና አጨቃጫቂ የውኃ ፖለቲካ ሁኔታ እስከወዲያኛው ሊቋጨው ይችላል የሚል ግምት አለኝ:: ይህንን ለማድረግ መፍትሔው ሕጋዊና ተቋማዊ ማዕቀፉን (legal and institutional framework ወይንም CFAውን) ከመፈረም ሌላ የተሻለ አማራጭ ያለ አይመስለኝም:: ማዕቀፉ ከፀደቀ ቀደምት የናይል ውኃ ስምምነቶችን ሙሉ በሙሉ ይተካቸዋል:: ለነገሩ ባንድ በኩል የቀድሞ ስምምነቶች አይነኩም እያሉ በሌላ በኩል ስለሕዳሴው ግድብ አሞላልና አለቃቀቅ እንወያይ ማለት ሁለት የሚጣረሱ ሀሳቦች ናቸው::

ሸ. የአረብ አገሮች ፓርላማ ኀብረት የኢትዮጵያ መንግሥት የግብፅን ታሪካዊ የውኃ ድርሻ ሊያከብር ይገባል ብሎ መግለጫ ከማውጣት ይልቅ ትብብርን ሊያጎለብቱ

የሚችሉ ሀሳቦችን መስንዘር ይጠበቅበት ነበር (ለምሳሌ ከላይ የተጠቀሱትን ቴክኒካዊ መፍትሔዎች ተግባራዊ ለማድረግ ግብዖችን በፋይናንስ መርዳት)፡፡

ለማጠቃለል ያህል ከፍተኛ ጥንቃቄና ሀገራዊ ሀላፊነት የሚጠይቁ የድርድር ሒደቶች እየተካሄዱ ባሉበት ሁኔታ በመስኩ ጥናት ያደረጉ ሁሉ ሐሳቦቻቸውን በንቃትና አገርን በሚጠቅም መልኩ ማንሸራሸር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ ሕብረተሰቡ በድርድሩ ሂደቶችና ውጤቶች ላይ ግልፅ መረጃ እንዲያገኝ መደረግ ይኖርበታል፡፡

# የመወያያ ፅሁፎቹን ያቀረቡ ምሁራን



**ዶ/ር አስናቀ ከፋለ** ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በፖለቲካ ሳይንስና አለም አቀፍ ግንኙነት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን እንዲሁም ጃፓን አገር ከሚገኘው ኢንተርናሽናል ዩኒቨርስቲ ኦፍ ጃፓን በዓለም አቀፍ ግንኙነት የትምሕርት ዘርፍ የማስተርስ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። በመቀጠልም ከላይደን ዩኒቨርስቲ (ኔዘርላንድስ) የዶክተሬት ዲግሪያቸውን ተቀብለዋል። ዶ/ር አስናቀ በአስተዳደር፣ ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ግጭትን ጨምሮ በተለያ ርዕሶት ላይ ብዛት ያላቸው የጥናትና ምርምር ስራዎችን በተለያዩ የአካዳሚ ጆርናሎች እና መፃሕፍት ላይ ለሕትመት አብቅተዋል። በአሁኑ ጊዜ ዶ/ር አስናቀ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት የትምሕርት ክፍል በተባባሪ ፕሮፌሠርነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ።



**አምባሳደር ህሩይ አማኑኤል** በሙያቸው ጋዜጠኛና ዲፕሎማት ሲሆኑ በኢትዮጵያ፣ ኢጋድ፣ እና በተ.መ.ድ ውስጥ በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ለረጅም ዓመታት አገልግለዋል። ፈረንሳይንና ጀርመንን ጨምሮ በተለያዩ አገራት የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆነው ያገለገሉ ሲሆን፤ በኢጋድ ውስጥ ቀጣናዊ ደህንነት ፕሮግራም ኃላፊ በመሆንም ሠርተዋል። በአሁኑ ጊዜ የተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ ቢሮ ከፍተኛ አማካሪ (Senior Advisor in the UN Office of Special Envoy for Horn of Africa) ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ። አምባሳደር ኅሩይ አሜሪካን አገር ከሚገኘው ሲራከስ ዩኒቨርስቲ (Syracuse University) በማስ ኮሙኒኬሽን የትምሕርት ዘርፍ የማስተርስ ዲግሪ አግኝተዋል።



**ዶ/ር ያቆብ አርሳኖ** በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኦሃዮ ዩኒቨርሲቲና በዙሪክ ዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን የተከታተሉ ሲሆን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካል ሳይንስ እና ዓለምአቀፍ ግንኙነት ተባባሪ ፕሮፌሰር ናቸው። የሶሻል ሳይንስ ኮሌጅ ዲን፣ የዩኒቨርሲቲው ፕሬስ ዳይሬክተርና የፖለቲካል ሳይንስ ት/ክፍል ሊቀመንበር ሆነው አገልግለዋል። በአሁኑ ወቅት ከማስተማር ስራቸው በተጨማሪ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ብሔራዊ ኤክስፐርቶች ፓናል ም/ሊቀመንበር፣ የግድቡ ሕዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ብሔራዊ ምክር ቤት አባል በመሆን እንዲሁም በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ጉዳይ ድርድር ለኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ለውኃ ሀብት ሚኒስቴር አማካሪ በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ።



**ፕሮፌሰር ተስፋዬ ታፈሰ** የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ጀርመን አገር ከሚገኘው ኦስናብሩክ ዩኒቨርሲቲ በጂአግራፊና በማህበረሰብ ጂአግራፊ ያገኙ ኢሆን ለሶስት አስርተ አመታት ጂኦግራፊ ፣ልማት ነክ ጉዮች አፍሪካ እና የመካካለኛው ምስራቅ ጥናቶች ላይ ሲያስተምሩ ቆይተዋል። አሁንም በሙሉ ፕሮፌሰርነት የትምህርት ክፍሉን እያገለገሉ ይገኛሉ። 5 መፅሀፍቶችን፣7 የሚሆኑ የመፅሀፍ ምዕራፎችን እንዲሁም በርከት ያሉ አርቲክሎችን ለህትመት አብቅተዋል።

Print @ Eclipse +251-115-572222/23